# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት/ 2009 ዓ.ም.

<u>አዲስ አበባ</u>

# መግለጫ

**ክፍል አንድ** ........ 1
**መግቢያ** ........ 1
የባለስልጣኑ አመሰራረት ........ 1
የባለስልጣኑ ራዕይ ........ 2
የባለስልጣኑ ዓላማ ........ 2
የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር ........ 2
የባለስልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል ........ 3
የፋይናንስ ምንጭ ........ 4
የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን የአሰራር ሥርዓት መግለጫ ........ 4
/system description/ ........ 4
ኦዲቱ ዓላማ ........ 8
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 8
ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ........ 9
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 9
የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች ........ 10
**ክፍል ሁለት** ........ 11
**የኦዲት ግኝቶች** ........ 11
2.1 ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት ፡ መኖ ፣ የሕክምና መሣሪያዎችና መገልገያዎችን ጥራትና ደህንነት ለማስጠበቅ እንዲያስችል ምዝገባ በማከናወንና ፈቃድና ደረጃ በመስጠት ኢኮኖሚያዊ ፡ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 11
የባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥን በተመለከተ፣ ........ 11
ባለስልጣኑ ባለሙያ በሌለበት የእንስሳት መድኃኒት ቤት ንግድ እንዳይካሄድ እንዲሁም የመኖና መኖ ንጥረ ነገሮች ወይም ግብዓቶች ፣ አስመጪ እና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች የመኖ ባለሙያዎችን ስለመቅጠራቸው መቆጣጠሩን በተመለከተ፤ .14
ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኙ በዘርፉ ላይ እንዳይሰማሩ ለመቆጣጠር የሚስችል የአሰራር ስርዓት በባለስልጣኑ ስለመዘርጋቱና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ........ 17
ባለስልጣኑ ደንብ እና መመሪያዎችን በተላለፉ ድርጅቶች/ግለሰቦች ........ 19
ላይ አስተዳደራዊ እና የቅጣት እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ፤ ........ 19
ባለስልጣኑ በደንብ ቁጥር 325/2006 በወጣው ተመን መሰረትድርጅቶች በወቅቱ የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈፅሙ ማድረጉን በተመለከተ፣ ........ 22
የእንስሳት መድኃኒቶችንና የህክምና መሳሪያዎች ፣ ንጥረ ነገሮችንና ውህዶችን እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ገምግሞ ስለመመዝገቡ፣ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማደሱ፣ እና በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ምዝገባውን ስለማገዱና ስለመሰረዙ በተመለከተ፣ ........ 24
ባለስልጣኑ ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝርን ........ 28
ስለመዘጋጀቱና መዘርዝሩንም በየጊዜው መከለሱን በተመለከተ፣ ........ 28
2.2. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒት፣ መኖ ፣ ሕክምና መሣሪያዎችና መገልገያዎች ዙሪያ ከሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ተዋህዶ ለመስራት እንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን ብቃት ባለው መልኩ ለማስተዳደር የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 30
ባለስልጣኑ በዘርፉ ለተሰማሩ ተቋማት ስልጠና መስጠቱን በተመለከተ፤ ........ 30
ባለስልጣኑ በዘርፉ ከተሰማሩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን በተመለከተ፣ ........ 31

ባለስልጣኑ በሀገር ውስጥ የተመረተም ሆነ ከውጭ ሀገር የገባ የእንስሳት መድኃኒቶች ላይ የጥራትና የፈዋሽነት ግምገማ በማካሄድ ስራ ላይ እንዲውል ስለማድረጉ በተመለከተ፣ ..... 33

ባለስልጣኑ የላብራቶሪና የክሊኒካል ጥናት በማደረግ የባህላዊ መደኃኒቶችን ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንድውሉ ስለማድረጉ በተመለከተ፣ ..... 40

ባለስልጣኑ የድህረ-ገበያ ቅኝት በማድረግ በውጤቱ መሰረት እርምጃ ስለመውሰዱ፣ ..... 42

ባለስልጣኑ የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የሚያስችል እና ያለመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶችን ዝርዝር መመሪያዎች ማዘጋጀቱን በተመለከተ፣ ..... 43

ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶች፣ መኖዎች ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮች የአወጋገድ መመሪያ ማውጣቱን በተመለከተ፣ ..... 45

2.3. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶች ደህንነታቸውና ፈዋሽነታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ እንዲሁም የእንስሳት መኖ ደህንነት በተዘጋጀው የምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ መመዘኛ መስፈርት መሰረት እየተሰራ ስለመሆኑ የድጋፍ ፡ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ ..... 47

ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን ፈዋሽነት እና የእንስሳት መኖና የመኖተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኃንነትና ጥራት ደረጃዎች በማዘጋጀትና በማፀደቅ ስራ ላይ ስለማዋሉ በተመለከተ፣ ..... 47

ባለስልጣኑ ወደ ውጭ ሀገር ለሚላክ መኖ የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠቱን በተመለከተ፣ ..... 49

ባለስልጣኑ የዘርፉን የመረጃ አያያዝ፣ልወውጥ እና አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ስለማድረጉ በተመለከተ፣ ..... 50

የክልል አካላት ስለሰጧቸው፣ ስላገዷቸውና ስለሰረዟቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች እና የሙያ ፈቃዶች ለባለስልጣኑ መረጃ መተላለፉን በተመለከተ፣ ..... 52

ባለስልጣኑ በናርኮቲክና በሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፣ ..... 53

ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር ዘርፉን አስመልክቶ የመግባቢያ ሰነድ (MOU) ስለመፈራረሙ በተመለከተ፣ ..... 54

ባለስልጣኑ በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን ሊያግዙ የሚያስችል የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት ተግባራዊ ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ፣ ..... 55

ባለስልጣኑ መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት ስለመመረቱ፣ ስለመከማቸቱና ስለመጓጓዙ በተመለከተ ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፣ ..... 56

ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ለሚያመርቱ፣ በሀገር ውስጥም ሆነ ወደ ውጭ ሀገር የሚልኩ ድርጅቶችን የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎችን ስለመከታተሉ በተመለከተ፣ ..... 60

**ክፍል ሦስት** ..... 62

***የመደምደሚያ ሃሳቦች*** ..... 62

**ክፍል አራት** ..... 69

***የማሻሻያ ሃሳቦች*** ..... 69

አባሪ1፡ ..... i

አባሪ 2፡ ..... iii

አባሪ 3፡ ..... iv

አባሪ 4 ..... vii

አባሪ 5- ..... ix

አባሪ 6 ..... xi

አባሪ 7 ..... xii

አባሪ 8፡ ..... xiii

አባሪ 9 ..... xv

# <u>የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ/ድርሞ/</u>

## <u>Excutive summary</u>


የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ ሲሆን፤ ይህንን ስራ ለመከታተል ስልጣን የተሰጠው የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ሃላፊነቱን በአግባቡ መወጣቱን እና የእንስሳት መድኃኒትና መኖን በተመለከተ ምዝገባ በማካሄድና የቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ደህንነቱና ጥራቱን የጠበቀ መኖ እንዲሁም ጥራቱ፣ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒቶች ለተጠቃሚው እንዲደርሱ እንዲሁም ለእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ እና ለመኖ አምራቾች፣ ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስመጪዎች፣ ላኪዎች፣ አከፋፋዮች ድጋፍ ማድረጉን ለማረጋገጥ ሲሆን ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

በዚህም መሰረት በኦዲቱ የተገኙት ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ✓ በእንስሳት መድኃኒት ወይም በመኖ ንግድ ስራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች ወይም ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ቢሰጥም፤ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት በወቅቱ የምስክር ወረቀታቸውን ባለማደሱ፣ ባለማገዱ እና ባለመሰረዙ 3 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች በወቅቱ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ የተገኙ ሲሆኑ፣ 6ቱ ደግሞ በቅጣት እድሳት የሚፈፅሙበት ጊዜ ያለፈ ቢሆንም ባለስልጣኑ እድሳት የፈፀመላቸው መሆኑ ፣
- ✓ 7 መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጭ ድርጅቶች ፈቃድ እድሳት ክፍያ አለማከናወናቸውና 3ቱ የእንስሳት መኖ ድርጅቶች ደግሞ ፈቃድ ያወጡበትን የአገልግሎት ክፍያ አለመፈፀማቸው ሌሎች 3 የእንስሳት መኖ አምራች ድርጅቶች እና 5 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ደግሞ እድሳት እንዳላከናወኑና ባለማሳደሳቸውም እንደተሰረዙ ይቆጠራሉ በማለት ባለስልጣኑ የወሰደው እርምጃ አለመኖሩ ፡፡ ከነዚህ ድርጅቶች ውስጥ በኦዲቱ ወቅት ሲሰራ የተገኘ ድርጅት መኖሩ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ሌላ 3 የእንስሳት መኖ አምራች / ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የማምረት አቅማቸው ከፍተኛ ቢሆንም ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ እንዳልወሰዱ እንዲሁም ከ3 የመድኃኒትና የክትባት አምራች ድርጅቶች ውስጥ 2ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይሰጣቸው እየሰሩ መሆኑ፤
- ✓ ባለስልጣኑ የሙያ ፈቃድ የተሰጠው የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በሌለበት የእንስሳት መድኃኒት ቤት ንግድ እንዳይካሄድ በተሟላ መልኩ እንዳልተቆጣጠረ እና በቁጥጥሩም ወቅት በታዩት ክፍተቶች ላይ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፤
- ✓ በኦዲቱ ወቅት ከታዩ 8 የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጪ እና የመኖ ማቀነባበሪያ ድርጅቶች ውስጥ 8ቱም ከባለስልጣኑ ፈቃድ የወሰዱ ድርጅቶች በሙሉ ከመመሪያ ውጭ እንደሚሰሩ እና ባለስልጣኑም በዚህ ዙሪያ ያልጠየቃቸው መሆኑ ፡፡ ከነዚህ ውስጥ 2ቱ በመድኃኒት ባለሙያዎች ስራውን እንደሚያከናውኑና እስካሁን ድረስ ቅጥር ያልፈፀሙ ሲሆን ፣ አንድ ድርጅት

ደግሞ የባለሙያዎችን የቅጥር ደብደቤያቸውን ከብቃት ማረጋገጫ ሰሪትፊኬት ጋር በማያያዝ ለባለስልጣኑ አለማቅረቡ እንዲሁም 5ቱ  የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩት የድርጅቱ ባለሙያዎች ከባለስልጣኑ የተሰጠ ጊዜያዊ የሙያ ፈቃድ ሰርተፍኬት እንደሌላቸው  ሲሆን ባለስለጣኑም ኢንዲያወጡ አለመጠየቁንና ለማውጣት ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አለማድረጋቸው ታውቋል፡፡

- ✓ ባለስልጣኑ ማንኛውም  የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ህክምና መሳሪያ አስመጪ ወይም ላኪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው  በዘርፉ እንዳይሰማራ ለመቆጣጠር የሚስችል የአሰራር ስርዓት ቢዘረጋም  በተሟላ መልኩ ተቆጣጥሮ ተግባራዊ  ያላደረገ መሆኑ፤
- ✓ በተጨማሪም ከ2006-2008 ዓ.ም ከባለስልጣኑ አዋጅ፣ደንቦችና መመሪያዎች ውጭ ሲሰሩ የተገኙ ድርጅቶች ቢኖሩም ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 728/2004 ወይም ለአዋጁ አፈፃፀም የወጣውን ደንብ ቁጥር 272/2005 ወይም መመሪያዎች በመተላለፍ ሲሰሩ የተገኙትን ድርጅቶች የምስክር ወረቀታቸውን ወይም የሙያ ፈቃዳቸውን አግዶም ሆነ ሰርዞ የማያውቅ መሆኑ፤
- ✓ በኦዲቱ ወቅት 3 ድርጅቶች የመኖ ንጥረ ነገሮችን ወይም ግብዓቶችን ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኙ መኖ፣የመኖ ንጥረ ነገሮች ወይም የመኖ ግብዓቶች ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቡ ድርጅቶች መኖራቸው እንዲሁም 8 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ፣3 የመድኃኒት አምራች  2 የመኖ አምራች ድርጅቶች ፈቃድ ለሌለው ሰው መድኃኒት ወይም መኖ አከፋፍለው ቢገኙም ባለስልጣኑ እርምጃ አለመውሰዱ በተጨማሪም አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው ከ2006-2008ዓ.ም በእንስሳት መድኃኒት ወይም በመኖ ንግድ ስራ ላይ ሲሰማሩ የተገኙ ድርጅቶች ቢገኙም ባለስልጣኑ የንግድ ተቋሞቹን በማሸግ ተገቢውን እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፤
- ✓ ባለሰልጣኑ ለእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሳሪያዎች ፤ ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተቋማት ምዝገባና ፈቃድ ለመስጠት እንዲሁም በውጭ አገር አምራች ኩባንያዎች ለእንስሳት መድኃኒት የመልካም አመራረት ተሞክሮ ምልከታ ለማድረግ በደንብ ቁጥር 325/2006 በወጣው ተመን መሰረት በተሟላ መልኩ በወቅቱ የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈፅሙ ያላደረገ መሆኑ፤
- ✓ ባለስልጣኑ ለእንሰስሳት ለውጭ ጥገኛ ህክምና ወይም ለእንስሳት በሽታ አስተላላፊ ተባዮች መቆጣጠሪያ አገልግሎት የሚውሉ ንጥረ ነገሮችንና ውህዶችን በተማሏ መልኩ በመመዝገብ እንደማይቆጣጠር እንዲሁም  በአገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎች በከፊል ገምግሞ ቢመዘግብም ነገር ግን የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ሙሉ በሙሉ ገምግሞ እንዳልመዘገበ እንዲሁም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ምዝገባውን እንደማያድስ፣ እንደማያግድና እንደማይሰርዝ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት ከታዩት 3 የእንስሳት መድኃኒት አምራች ድርጅቶች ውስጥ 3ቱም

አስገምግመው ሳያስመዘግቡ አምርተው የሚሸጡ መሆኑ፤ እንዲሁም በአንድ አስመጪ እና በአንድ ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ያልተመዘገበ መድኃኒት ሲሸጥ የተገኘ መሆኑ፤

- ✓ በተጨማሪም በ 3 የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ድርጅቶች ውስጥ በተደረገው ድንገተኛ ኢንስፔክሽን በባለስልጣን መስሪያቤቱ ያልተመዘገበ መድኃኒት የተገኘ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ 5 ድርጅቶች በባለስልጣኑ የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮችን ሳያስመዘግቡ ከውጭ ሀገር ያስመጡ ቢሆንም በድርጅቶቹ ላይ ምንም ዓይነት የፈቃድ እገዳ ወይም ስረዛ አለመደረጉ፤
- ✓ ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ የምስክር ወረቀት በክፊል በየ5ዓመቱ ቢያድስም በራሱ የምዝገባ መስፈርት በማዘጋጀትና አፀድቆ እየሰራበት አለመሆኑ እና በቀድሞ ጊዜ በኢትዮጵያ ምግብ፣መድኃኒትና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት የሚሰራ ቢሆንም በተሟላ መልኩ በምዝገባው መስፈርቶች መሰረት የማይሰራ መሆኑ፤
- ✓ ከባለስልጣን መ/ቤቱ በእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ አስመጪነት ፈቃድ ከወሰዱ እና እስከ መስከረም 30/2009 ዓ.ም በባለስልጣኑ ዝርዝር ማስረጃ ውስጥ ከተካተቱ 30 ከሚሆኑ ድርጅቶች ውስጥ 16 የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ አስመጪ ድርጅቶች የመድኃኒት ሴሪትፍኬት ጊዜያቸው አብቅቶ ለዕድሳት በሂደት ላይ ያሉ 57 ዓይነት መድኃኒቶች ያሏቸው ሲሆን እነዚህም መድኃኒቶች የሴሪትፊኬት ጊዜያቸው ካበቃ ከ 5 ወር እስከ 6 ዓመት ቢሆንም ጊዜያዊ ሴሪትፍኬት እስኪሰጠቸው ድረስ መድኃኒቶቹን ከውጭ ሀገር አስገብተው በመሸጥ ላይ እንደነበሩ እና በኦዲቱ ወቅትም በመሸጥ ላይ መሆናቸውና ሎሎች ደግሞ እድሳት ቢያደርጉም የመድኃኒቶቹ ናሙና በላብራቶሪ የማይታይ መሆኑ፤
- ✓ ባለስልጣኑ ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝርን ያላዘጋጀ እንዲሁም መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በየዓይነታቸው ያልመደበ መሆኑ፤
- ✓ ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ አግባብ ላላቸው አካላት በተሟላ መልኩ ስልጠና አለመስጠቱን በኦዲቱ ወቅት ከታዩ 12 የመድኃኒት አስመጪ፣6 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች እና 3 የመድኃኒት አምራች ድርጅቶች ውስጥ ለ7 መድኃኒት አስመጪ፣ ለ1 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች እና ለ 3 የመድኃኒት አምራች ድርጅቶች በመድኃኒት አያያዝ ፣አከመቻቸት እና አጓጓዝ ዙሪያ ስልጠና እንዳልተሰጣቸው በተጨማሪም በናሙና ለታዩ ለ 5 መኖ አምራች እና ለ2 የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጪና ላኪ ድርጅቶች በእንስሳት መድኃኒት እና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ስልጠና አለመሰጠቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተሟላ መልኩ በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ ፡
- ✓ ባለስልጣኑ ከውጭ ሀገር መድኃኒት ለሚያስገቡ ለ21 እንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ በላብራቶሪ ሳይገመገምና ሳይረጋገጥ ለ280 ዓይነት መድኃኒቶች

ጊዜያዊ ፈቃድ በመስጠት ጥቅም ላይ እንዲውሉ መድረጉና ይሄ ሁኔታ ኦዲቱ እስከተጠነቀቀበት ጊዜ ድረስ የቀጠለ መሆኑ:

- ✓ እንዲሁም ባለስልጣኑ የላብራቶሪና የክሊኒካል ጥናት በማደረግ የባህላዊ መደኃኒቶችን ደህንነት፤ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንድውሉ አለማድረጉ፡
- ✓ ባለስልጣኑ የተመዘገበ የእንስሳት መድኃኒት ከተሰራጨ በኂላ ያስገኘውን ጠቀሜታና ያስከተለውን ጉዳት ለማወቅ የድህረ-ገበያ ቅኝት አድርጎ የማያውቅ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 15 የመድኃኒት አስመጪና አምራች ድርጅቶች ውስጥ 15ቱም ድርጅቶች የእንስሳት መድኃኒት ያስመዘገቡ ቢሆንም ባለስልጣኑ መድኃኒቶቹ ከተሰራጩ በኃላ የድህረ ገበያ ጥናት በመድኃኒቶቹ ላይ ማስደረግ ቢገባውም የድህረ ገበያ ጥናት አድርጎ የማያውቅ መሆኑ እና ድርጅቶቹም የፋርማኮቪጅላንስ ማስረጃም ለባለስልጣኑ አቅርበው የማያውቁና ባለስልጣኑም ጠይቋቸው የማያቅ መሆኑ፡
- ✓ ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒትን ጥቅም ላይ ለማዋል እና የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር መመሪያዎችን ያላወጣ መሆኑ ፣ በኦዲቱ ወቅት ከታዩ ድርጅቶች ውስጥ 6 የመድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ፣ 5 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች እና አንድ አምራች ድርጅት ባለስልጣኑ የእንስሳት መድሃኒቶች ጥቅም ላይ ለማዋል ያወጣው መመሪያ እንደሌለ ፣ የእንስሳት መድኃኒት ጥቅም ላይ መዋሉን እንደማይከታተል እንዲሁም መመሪያ በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ስለማዋል ያከናወነው ተግባር አለመኖሩ እንዲሁም ከእንስሳት ሀኪም በተጨማሪ በሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ትዕዛዝ እና ያለመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶችን ዝርዝር በመመሪያ ያልወሰነ መሆኑ:
- ✓ ባለስልጣኑ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸውን የእንስሳት መድኃኒቶች፤ መኖዎች ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮች አወጋገድን በተመለከተ መመርያ አለማውጣቱ እንዲሁም በመመሪያው ምክንያት አከባቢን በማይበክል መንገድ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን መቆጣጠር ያልጀመረ ሲሆን፣ በኦዲቱ ወቅት 5 የእንስሳት መድኃኒቶች አስመጪ፣ 1 ጅምላ አከፋፋይ እና 2 አምራች ድርጅቶች መጋዘኖቻቸው ውስጥ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ጊዜ ያለፈባቸው የእንስሳት መድኃኒቶች ያሉ መሆኑ የባለስልጣኑም ባለሙያዎች በቁጥጥር ጊዜ ያዩ ና ፎርም ቀርፀው በዝርዝር እንዲያሳዉቋቸው ያደረጉ ቢሆንም የአወጋገድ መመሪያ እስኪያወጣ ድረስ ተለይተው እንዲቀመጡ ከማድረግ ውጭ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ አለመደረጉ እንዲሁም ፡ በኦዲቱ ወቅት ከታዩት 7 የመኖ አምራች እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪድርጅቶች ውስጥ 3ቱ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው የመኖ ንጥረ-ነገር እና መኖ ያላቸው ሲሆኑ እንዲሁም 4 ድርጅቶች ያስወገዱበት ሁኔታ ቢኖርም በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን ባለስልጣኑ ያልተቆጣጠረ መሆኑ ፡

- ✓ ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ደረጃዎች እና የእንስሳት መኖና የመኖተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኅንነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብና ተከታትሎ በማፀደቅ ስራ ላይ እንዲውል አለማድረጉ:
- ✓ እንዲሁም ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ አውጥተውና ሳያወጡ  በተደጋጋሚ መኖና የመኖ ግብዓት ወደ ውጭ ሀገር የሚልኩ ድርጅቶች ቢኖሩም ባለስልጣኑ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ወደ ውጭ ሀገር ለሚላኩ ለእንስሳት መኖዎች የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት ያልጀመረ መሆኑ:
- ✓ ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ የመረጃ አያያዝ፣ልወውጥ እና አጠቃቀም ስርዓት ያልዘረጋ ፣ መረጃዎቹን በዳታ ቤዝ አጠናክሮ የማይዝ  እና ወቅታዊ የሆኑ የእንስሳት መዲኃኒትና መኖ መረጃዎችን በመደበኛነት ለባለሙያዎችና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የማያስተላልፍ መሆኑ  በኦዲቱ ወቅት ከታዩ 12 መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች፣  6 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች፣  3 አምራች ድርጅቶች ውስጥ  6 መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች 3 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ከባለስልጣን መ/ቤቱ  ጋር የእንስሳት መድኃኒትን እና የህክምና መሳሪያዎችን በተመለከተ  ወቅታዊ መረጃዎች የሚለዋወጥበት ስርዓት አለመኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ ባለስልጣኑ አግባብ ያላቸው የክልል አካላት ስለሰጧቸው፤ ስላገዷቸውና ስለሰረዟቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች እና የሙያ ፈቃዶች እንዲሁም መድኃኒትን በተመለከተ  በተሟላ መልኩ እንደማይከታተልና መኖን በተመለከተ ደግሞ ሙሉ በሙሉ መረጃ መተላለፉን የማይከታተል መሆኑ:
- ✓ ባለስልጣኑ ለእንስሳት ህክምና ጥቅም ላይ የሚውሉ ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ሪፖርት የማያደርግ መሆኑ:
- ✓ ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመሆን በክልል ተሻጋሪ የመድኃኒትና መኖ አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይ ባለፈቃዶች እና በችርቻሮ ንግድ እንዲሁም በህገ-ወጥ መድኃኒትና የመኖ ዝውውር ላይ የመግባቢያ ሰነድ (MOU) የሌለው መሆኑ እንዲሁም በእንስሳት መድኃኒትና  መኖ አምራችነት፣ጅምላ አከፋፋይነት፣ላኪነትና አስመጪነት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን  ውጤታማ ለማድረግ እና በስራዎቻቸው ላይ የሚኖሩ የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶችን ለመፍታት የሚያስችል የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት በመመሪያ ደረጃ በማዘጋጀት እየሰራ አለመሆኑ ታውቋል፡፡
- ✓ ባለስልጣኑ የእንስሳት መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፤ መከማቸቱንና መጓጓዙን በተሟላ መልኩ እየተቆጣጠረ አለመሆኑ:

- ✓ በኦዲቱ ወቅት የታዩት ሁሉም የመኖ አምራች ድርጅቶች መኖን ለማምረት የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ የመኖ ግብዓቶች ከተገኘበት ቦታ ሁሉ በመግዛት መሆኑ:
- ✓ ባለስልጣኑ የመኖ ደህንነትንና ጥራትን ለማስጠበቅ እንዲያስችል አምራቾች ጥራቱን የጠበቀ የመኖ ግብዓት ስለመጠቀማቸው እንዲሁም የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች/ግለሰቦች/ ደህንነቱ የተጠበቀ ግብዓት ስለማቅረባቸው እና የመኖ አምራች ድርጅቶችም ደህንነቱ የተጠበቀ ግብዓት ከታወቀ ድርጅት ስለመግዛታቸው ክትትል ያላደረገ በመሆኑ የኢትዮጵያ የምግብ መድኃኒት ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ከባለስልጣኑ ጋር በጋራ የተጠና ሲሆን የጥናቱ ሪፖርት የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነት ከግብዓት አቅራቢዎች ጀምሮ ወጥነትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ባለመስራቱ መነሻው ፈንገስ ወይም ሻጋታ የሆነ አፍላቶክሲን የተባለ መርዛማ ኬሚካል በወተት ላይ እንደተፈጠረ ማሳየቱን እና ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር በማያያዝ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ዙሪያ በበቂ ሁኔታ ስራውን መስራት ባለመቻሉ ይህ አፍላቶክሲን የተባለው መርዛማ ኬሚካል ሊከሰት የቻለ መሆኑን፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መኖ እና የወተት ናሙና ተወስዶ ሁሉም ናሙናዎች በአፍላቶክስን እንደተጠቁ ጥናቱ እንደሚያሳይ በተለይ ደግሞ የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ላይ ችግሩ እንደከፋና ወተት ላይ የታየውም ምንጩ የሚመገቡት መኖ እንደሆነ በጥቅምት/2008ዓ.ም ለባለስልጣኑ ያሳወቀ መሆኑ፣
- ✓ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 12 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች፣ 6 ጅምላ አከፋፋዮች፣3 መድሀኒት አምራች ድርጅቶች እንዲሁም 6 መኖ አምራች ድርጅቶች እና 2 የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪና ላኪ ድርጅቶች ውስጥ ፦ 10 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ፣ 2 የመድኃኒት አምራቾች 6 የመኖ አምራች ድርጅቶችና 2 የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች አስመጪና ላኪ ድርጅቶች
- ✓ ባለስልጣኑ ቁጥጥር የሚያደርገው በየዓመቱ ለቅድመ ፈቃድ እድሳት እንደሆነና አልፎ አልፎም የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በራሳቸው ፕሮግራም ሳያሳውቁ ድርጅቶቹ ድረስ በመሄድ ክትትልና ቁጥጥር ቢያደርጉም መደበኛ በሆነ መልኩ የማያደርግ እና ለድርጅቶቹ ተገቢውን ግብረ መልስ በማዘጋጀት እንዲያውቁት የማያደርግ መሆኑ ታውቋል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

### የባለስልጣኑ አመሰራረት

1. የእንስሳት ሀብት  አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ እንዲሁም የሀገሪቱ አርሶ አደር በኢኮኖሚው ላይ ያላቸው ጉልህ ድርሻ ተገቢውን ትኩረት ሳያገኝ የቆየ ቢሆንም አሁን ግን በተለይም የእንስሳት ጥራትና ደህንነት ለገበያ መር ስርዓት እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ምርቶች ግብዓትነት የሚኖረውን አስተዋፅኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት የእንስሳት ጤንነትን ለመጠበቅና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገሮች ተመርተው የሚገቡ መድኃኒቶች፣ የህክምና መሳሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶችን እንዲሁም የእንስሳት መኖ አመራረት ፣ አቅርቦትና አጠቃቀም የሚፈለገውን ጥራትና ደረጃ አሟልተው ለተጠቃሚው እንዲደርሱ በማድረግ ሀገሪቱ ከንዑስ ዘርፉ በበለጠ ተጠቃሚ እንዲትሆን ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ጥራት ደረጃ ቁጥጥር ማድረግ ፣ ጥራቱ ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ መድኃኒት ለህብረተሰቡ በማቅረብ የእንስሳትን ምርታማነትና የምርት ጥራትን ለማሻሻል የሚደረገውን ትግል ከማገዝ ባሻገር እጅግ አሳሳቢ እየሆነ የመጣውን የበሽታ አምጪ  ተዋህስያንና የመድሃኒት መላመድ አደጋ በቁጥጥር ስር በማዋል ከእንስሳት መድሃኒትና ሌሎች መርዛማ ቅሪቶች ነፃ የሆነ ጥራትና ደህንነቱ የተረጋገጠ ምርት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዲቀርብና የህብረተሰቡን ጤና ከመጠበቅ አንፃር ቀጥተኛ ያልሆነ አስተዋፅኦ የሚያደርግ ነው፡፡
2. ይህም የቁጥጥር ተግባር ቀደም ስል በተለያየ አካላት ማለትም የመድኃኒት ቁጥጥርን በሚመለከት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር  በምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የነበረ ሲሆን፤ የመኖ ቁጥጥር ስራንም በሚመለከት በተሟላ መልክ ባይሆንም በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና እፅዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥር በዳይሬክቶሬት ደረጃ ሲከናወን የነበረ በመሆኑ ይህንን ችግር ለመቅረፍ በሚያስችል ሁኔታ የአስተዳደርና የቁጥጥር ተግባራት ቀደም ብሎ በተለያዩ አካላት ይደረግ የነበረውን ወጥ በሆነ ሁኔታ በአንድ ተቋም አደራጅቶ ማከናወን አስፈላጊ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 728/2004ዓ.ም እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 272/2005ዓ.ም የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በመባል የተቋቋመ የፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤት እንዲሆን ተደንግጓል፡፡
3. ባለስልጣኑ በዋናነት የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አመራረት፣ አቅርቦትና አጠቃቀም ቁጥጥርን በማሻሻል የእንስሳት ሀብት ልማትንና ጤንነት አጠባበቅን ማሳደግ ሲሆን የእንስሳት

መድኃኒትና መኖ ህገ-ወጥ ምርትና ስርጭትን በመከላከልና በመቆጣጠር የአስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት የባለስልጣኑ ዋነኛ ኃላፊነት እንዲሆን ተደርጓል፡፡

4. ባለስልጣኑ ቀደም ሲል በግብርና ሚኒስቴር ስር የነበረ ቢሆንም በአዲሱ አደረጃጀት ግን ተጠሪነቱ ለእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር እንዲሆን ተደርጓል፡፡

## የባለስልጣኑ ራዕይ

5. የእንስሳት መድኃኒትና መኖ የጥራት ደረጃና ደህንነት በመቆጣጠር ዓለማቀፋዊ ተቀባይነት ያለው ተቋም ሆኖ መገኘት፡፡

## የባለስልጣኑ ዓላማ

6. የእንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግና ጤናማ የእንስሳት ምርት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዲቀርብ ማስቻል ነው፡፡

## የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

7. ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   - የእንስሳት መድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት እንዲሁም የመኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኅንነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያቀርባል፣ ሲጸድቁም በተግባር ላይ መዋላቸውንና መከበራቸውን ይከታተላል፤
   - በእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ንግድ ሥራ ለሚሰማሩ ሰዎች የብቃት መመዘኛ ያዘጋጃል፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (2)/ለ/ ለተመለከቱት የብቃት ማረጋ ገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የምስክር ወረቀቱን ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤
   - አገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ አገር የሚመጡ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ገምግሞ ይመዘግባል፣ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ምዝገባውን ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤
   - የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝር ያዘጋጃል፣ መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በየዓይነታቸው ይመድባል፣ መዘርዝሩንም እንደአስፈ ላጊነቱ በየጊዜው ይከልሳል፤
   - የእንስሳት መድኃኒቶችንና መኖን በተመለከተ የፖሊሲ ሀሳብ ያመነጫል፣ ረቂቅ ሕጎችን ያዘጋጃል፣ በመንግሥት ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

- የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ዘርፉን ለማጠናከርና ለማስፋፋት በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚደረጉ ሳይንሳዊ ግኝቶችን በመከታተል ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣሙ ያደርጋል፤
- የላቦራቶርና የክሊኒካል ጥናት በማድረግ የባህላዊ መድኃኒቶቹን ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ያረጋግጣል፣ በእንስሳት ጤና አገልግሎት ውስጥ ገብተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይፈቅዳል፤
- ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣ እንደአስፈላጊነቱ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ መረጃዎችን ለባለሙያዎችና ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ ያስተላልፋል፣ መረጃ የሚያስተላልፉ ሰዎች መረጃ ትክክለኛነትና አግባብነት ያረጋግጣል፣ አሻሚ ወይም ትክክለኛ ያልሆኑ መረጃዎች እንዳይሰራጩም ያደርጋል፤
- በእንስሳት መድኃኒቶች ላይ የክሊኒካል ሙከራ እንዲደረግ ፈቃድ ይሰጣል፣ ሂደቱን ይከታተላል፤
- በእንስሳት ሕክምና ጥቅም ላይ የሚውሉ ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን በተመ ለከተ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ሪፖርት ያደርጋል፤
- ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የጥራት ምርመራ ላቦራቶሪዎችን ያደራጃል፤
- እንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ አግባብ ላላቸው አካላት ስልጠና ይሰጣል፤
- በአዋጁ አንቀጽ 2(2) መሠረት ለእንስሳት የውጭ ጥገኛ ህክምና ወይም ለእንስሳት በሽታ አስተላላፊ ተባዮች መቆጣጠሪያ አገልግሎት የሚውሉ ንጥረ ነገሮችንና ውህዶችን ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል ይህንንም አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 6) እና 4//2ሺ.2 ስልጣን ለተሰጠው አካል ያሳውቃል፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## የባለስልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል

8. የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ተጠሪነቱ ለእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር ሆኖ በአንድ ዋና ዳይሬክተር እና በሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ተዋቅሯል:: በዋና ዳይሬክተር ስር አስር ዳይሬክቶሬቶች ያሉ ሲሆን የተቀሩት ሁለት ዳይሬክቶሬቶች በሁለቱ ም/ዋና ዳይሬክተሮች እንዲመሩ ተደርጉ የተዋቀረ ነው፡፡ ለባለስልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላው 284 የሰው ሀይል የተፈቀደ ሲሆን ከዚህም ውስጥ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቀጥጥር ዙሪያ ላሉት 5 ዳይሬክቶሬቶች የተፈቀደው 129(45%) የሰው ሀይል ነው፡፡ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተሩን ጨምሮ በባለስልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ

በስራ ላይ ያለው የሰው ሀይል እስከ ሚያዚያ/2008 ዓ.ም 124 ሰራተኞች ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 62 (50%) ሴቶችና 62(50%) ወንዶች ናቸው፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ በኤም.ኤስ.ሲ/ኤም.ኤ ደረጃ ያሉ 21(17%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 54(43.5%)፣ ኮሌጅ ዲፕሎማ10(8% )፣ /10+2/10+1 ያላቸው 8(6.5%)፣ እንዲሁም የቀለም ትምህርት ያላቸው ሰራተኞች 31 (25%) የሚይዝ መሆኑን ከሰው ሀብት ልማት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ከተሰበሰበ መረጃ ለማውቅ ተችሏል፡፡

### የፋይናንስ ምንጭ

9. የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ሥራውን የሚያንቀሳቅሰው ከመንግሥት በሚመደብለት መደበኛ በጀት ሲሆን በ2006፣ በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመታት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ እንደቅደም ተከተላቸው ብር 9,267,080.00፣ ብር 16,010,710.00 እና ብር 43,679,450.00 በድምሩ ብር 68,957,240 ከመንግሥት ፀድቆ ለሚተገብሯቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የተመደበለት ሲሆን ከተመደበለት በጀት ውስጥ በ2006 ዓ.ም ብር 8,074,080.00፣ በ2007 ዓ.ም. ብር 14,906,129.57 እና በ2008 ዓ.ም. ብር 39,761,336.56 በድምሩ ብር 62,741,546.13 ጥቅም ላይ አውሏል፡፡

## የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን የአሰራር ሥርዓት መግለጫ/system description/

### የእንስሳት መድኃኒት ጥራትና ደረጃ ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት

10. ጥራታቸውን የጠበቁ የእንስሳት መድኃኒቶችና ህክምና መሳሪያዎች ለተጠቃሚ እንዲደርሱ ለማድረግ እንዲያስችል የእንስሳት መድኃኒቶች፣ የሕክምና መሣሪያዎችና መገልገያዎችን ጥራትና ደህንነትን በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት ስራው መከናወኑን በማረጋገጥና ምርታቸውን ለማስመዝገብ በሚያመለክቱና ምርታቸውን ባስመዘገቡ የውጭ እና የአገር ውስጥ የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች አምራች ኩባንያዎች ላይ የመልካም አመራረት ስርዓትን (Good manufacturing practice/GMP) ተከትለው ማምረታቸውን ያረጋግጣል፡፡እንዲሁም ስለተመዘገቡ የእንስሳት መድኃኒቶች፣ የሕክምና መገልገያዎችና መሣሪያዎች ሣይንሳዊ መረጃዎች እንዲዘጋጁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ የሀገር ውስጥ የመድኃኒት፣ የሕክምና መገልገያዎችና መሣሪያዎች አምራች ኩባንያዎች አቅማቸውን ለማጐልበት የሥልጠና ኘሮግራሞች እንዲወጡ ያደርጋል፣አዳዲስ አሰራሮችና ማሻሻያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የእንስሳት መድሃኒትንና የህክምና መሳሪያዎችን አስመልክቶ

የሚዘጋጁ፤ ተዘጋጅና የሚከለሱ ደረጃዎችን አስመልክቶ የሚካሄደውን እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፡፡

## የእንስሳት መኖ ጥራትና ደረጃ ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት

11. ሀገር ውስጥ በተመረቱና ወደሀገር በሚገቡ መኖና የመኖ ውጤቶች ላይ ከጥራት ጉድለት ጋር ተያያዥ ስጋቶችን ለመቅረፍ ሳይንሳዊና አደጋ ተኮር የጥራትና ደህንነት መስፈርትን ያካተተ የመኖ ጥራት ዳሰሳና የቅሪት መጠን ምርመራ ያደራጃል፡፡ እንዲሁም በሳይንሳዊ መረጃና ስጋት ትንተና ላይ የተመሰረቱና በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን ፍላጎት መነሻ ያደረጉ የመኖ አመራረት ሂደት መመሪያዎችን ያዘጋጃል፡፡ የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነትን ለማረጋገጥ የድህረ ግብይት ናሙና በማሰባሰብ ለቀጣይ የላቦራቶሪ ምርመራ ያቀርባል፤በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት አመራርና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣል" ያድሳል" ያግዳል" ይከለክላል"በማምረት፣ ማቀነባበሪያና ማዘጋጃ ተቋማት የጥራትና ደህንነት አስተዳደር ጽንሰ-ሃሳብ (HACCP) ተግባራዊ እንዲሆን ያበረታታል" ክትትል ያደርጋል"ከመኖ አምራች ተቋማት የሚወጡ የብክለት ምንጮችና ብክለትን በመመርመር ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፤የመኖ ማሽኒያና የመጠቅለያ ቁሶች ፍተሻ ያደርጋል ትክክለኛነቱን ያረጋግጣል አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፤ለተገልጋይ ጥያቄና ቅሬታ ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም በመኖ ጥራት መስፈርትና በጥራት አጠባበቅ ስርዓት ላይ ሙያዊ ስልጠና ያደራጃል፣ ይሰጣል፡፡ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ይጠብቃል፣ ያሰራጫል::

## የእንስሳት መኖ እና መድኃኒት ጥራት ደረጃዎች ኢንስቴክሽን ዳይራክቶሬት

12. ጥራትና ደኅንነቱ የተጠበቀ መኖ አቅርቦትን ለማረጋገጥ ፖሊሲዎችን ያመነጫል፣ ይቀርጻል፣ ሲፀድቅም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል" የፖሊሲውንና የአሰራር ኢንስፔክሽን ቡድን ስራ በሚቀርጸው ፕሮግራም መሰረት መከናወኑን ለመከታተል እንዲያስችል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ብሄራዊ የመኖ ጥራትና ደረጃዎች እንዲሁም የደህንነት ቁጥጥር ማስፈጸሚያ መመሪያዎችንና የአሠራር ሂደቶችን ያዘጋጃል" የክትትልና ቁጥጥር ሥራውንም በቅርበት በማስተባበር መኖን በማምረት፣ በማቀነባበር፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝ ለተሰማሩ አካላት በተዘጋጀው የቁጥጥር ደንብ መሠረት መሥራታቸውን ይከታተላል" ይቆጣጠራል እንዲሁም የመኖ እና ምግብ-ወለድ አደጋን ለመቆጣጣርና ለመከላከል ተቀባይነት ያለውን የስጋት መጠን ለማረጋገጥ የስጋት ፍተሻና ትንተና ያካሄዳል፣ ያስተባብራል፣ በመኖ ማምረቻ፣ ማቀነባበሪያ፣ ማከማቻና ማከፋፈያ ተቋማት የጥራትና ደህንነት አስተዳደር ጽንሰ-ሃሳብ (HACCP) ተግባራዊ እንዲሆን ያበረታታል፡፡ እንስሳት እና የእንስሳት ውጤት ተመጋቢዎችን

ከበሽታ አምጪ ጀርሞች፣ ከፀረ-ተባይ ቅሪቶች፣ ያለአግባብ ጥቅም ላይ ከዋሉ የመኖ ተጨማሪዎች፣ ኬሚካላዊ ብክለቶች፣ ስነ-ህይወታዊ መራከች ዘረመላቸው የተቀየረ ህዋሳት፤ የሰውነት አስቆጪ ንጥረ-ነገሮች፤የእንስሳት መዲኃኒት ቅሪቶችና ማሳደጊያ ቅመሞች ጋር ከተያያዙ መኖ ወይም ምግብ-ወለድ አደጋዎች ለመከላከል የሚያስችል ስልት በማዘጋጀት በየጊዜው የሚደረጉ ጥናቶቸን የተሻሻሉ ተሞክሮዎችን፤ የደንበኞችን አስተያየት መሰረት በማድረግ የስራ ሂደቱ ቀልጣፋና ውጤታማ የሚሆንበትነ አሰራር ይቀይሳል፡፡

13. በተጨማሪም መድኃኒቶች ደህንነታቸውና ፈዋሽነታቸው ተጠብቆ እንዲቆይና በተዘጋጀው የብቃት ማረጋገጫ መመዘኛ መሰረት እተሰራ ስለመሆኑ ለመቆጣጠር በሚያስችል መልኩ መዲኃኒቶችን እንዲሁም የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ፕሪከርሰር ኬሚካሎች በማስመጣት በመላክና ጅምላ በማከፋፈል ስራ የተሰማሩትን የመድኃኒት ጥራት ለማረጋገጥ በኢንስፔክሽን ቅኝት ቡድን የሚከናወነውን የክትትል ኢንፔክሽን ስራዎች ያቅዳል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡ ቡድኑ የኢንስፔሽን ስራው በፕሮግራም መሰረት እንዲያከናውኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ያደርጋል፡፡

14. ያልተመዘገቡ የተጭበረበሩ የጥራት ደረጃቸውን ያልጠበቁና በህገ-ወጥ መንገድ የተገኙ የእንስሳት መኖ እና የመኖ ንጥረ-ነገሮች እንዲሁም መዲኃኒት የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ገበያ ላይ እንዳይውሉና ህብረተሰቡ ላይ ጉዳት እነዳያደርግ ፕሮገራም ይነድፋል፡፡ እንዳስፈላጊነቱም የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡ በመድኃኒት አጠቃቀም ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳይ ከእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ጋር የፖሊሲ የህገ ደንብና መመሪያ ዝግጅቶች ላይ ይሳተፋል፡፡ ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉ የእንስሳተ መኖ፤ የመኖ ንጥረ ነገሮችና የማምረቻ መሳሪያዎች እንዲሁም መድኃኒቶች እንዲሁም ናርኮቲከና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ሲወገዱ በመመሪያው መሰረት በአከባቢና በእንስሳት ላይ ጉዳት የማይፈጥር መሆኑን ያረጋግጣል፤ ይከታተላል፡፡

## የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት

15. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ብሔራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ጥራትና ደኅንነት ቁጥጥር ፖሊሲዎችን፣ የአሠራር ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና የኢንስፔክሽን ስራ ፕሮግራም በመቅረጽ በስሩ የሚገኙት የቅርንጫፍና የመግቢያና መውጫ ኬላዎች የኢንስፔክሽን ባለሙያዎችም በግልጽ እንዲያውቁትና እንዲተገብሩት በማድረግ ወደ ሀገር የሚገባና ከሀገር የሚወጣ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ፣ እንዲሁም ግብዓቶችና የማምረቻ መሣሪያዎች ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላት ተገቢውን የዝውውርና ይለፍ ፈቃድ ማሟላታቸውን በኢንስፔክሽን አሠራር ሂደት መሠረት ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ የእንስሳት

መድኃኒትና መኖ አቅርቦትን በተዘጋጀው የቁጥጥር ደንብ መሠረት መሥራታቸውን በመቆጣጠር የእንስሳሳ መድኃኒትና መኖ ህገ-ወጥ ዝውውርን በመከታተልና በመቆጣጠር ያልተመዘገቡ የተጭበረበሩ የጥራት ደረጃቸውን ያልጠበቁ የእንሰሳት መድኃኒትና መኖ እንዲሁም የተለያዩ ግብዓቶች ገበያ ላይ እንዳይውሉና ህብረተሰቡ ላይ የጤና ጉዳት እንዳያደርሱ የቁጥጥር ፕሮግራም ይነድፋል፡፡ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤ ጉድለቶች ሲኖሩ እርምት እንዲደረግ የማስተካከያ፣ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

16. የእንስሳት መድኃኒትና መኖ፤ ሌሎች ግብአቶችን እንዲሁም የማሽኒያ ዕቃዎችን ጥራትና ለአገልግሎት ተስማሚ ስለመሆናቸው ጥርጣሬ ሲፈጠር ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት ናሙና በማስወሰድ ጥራታቸውን በላብራቶሪ እንዲመረመር ያስደርጋል፤ የኢንሰፔክሽን ቅኝት ተግባራትን ለማጠናከር የሚረዱ፤ የሚቆጣጠራቸው ተቋሞች ለመወጣት የሚያስችሉ፤ የባለስልጣኑ ቅርጫፍ ጽ/ቤቶችና ሌሎች ባለስልጣኑ የሚወክላቸው አካላት የኢንስፔክሽንና ቅኝት ስራ በትክክል እንዲያከናውኑና በማስተባበሪያው ጸ/ቤት ውስጥ ያሉ ባለሙያዎችን ክህሎትና እውቀት ለማዳበር የሚረዱ ልዩ ልዩ ስልጠናዎች፤ ሴሚናሮችና አውደጥናቶች እንዲካሄዱ ፕሮጀክቶችን መቅረፅ ስራ ላይ ቴክኒካዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በተለያየ ምንያት ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ እንዲሁም ግብዓቶች የማምረቻ መሳሪያዎች አወጋገድ መመሪያ መሰረት መወገዳቸውን ይከታተላል፡፡ የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና የመግቢያ ኬላዎች የኢንስፔክሽን ቅኝት አገልግሎት አሰጣጥን በትክክል እንዲያከናውኑ አዳዲስ የአሰራር ዘዴዎችን ይቀይሰል፡፡

## የእንስሳት መድኃኒቶች፣ውጤቶችና የመኖ ጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪ ማዕከል

17. በሀገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ የእንስሳት መኖዎች፣የእንስሳት ውጤቶችና ተዋፅዎች እና የእንስሳት መmድኃኒቶች ላይ ተገቢውን የኬሚካልና መድኃኒት ቅሪት((chemical and drug residue)) ወይም ብክለት፣የማይክሮባዮሎጂካል፣የምግብ ንጥረ ነገር ይዘት ባዮሎጂካሎች፣ኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች እንዳለው እንዲሁም የእንስሳት የመኖ ተጨማሪዎች(feed additives and premixes) ላይ ተገቢውን ዓይነት(type)፣ ይዘት፣ መጠንና መሰል ምርመራዎች በማድረግ በተጨማሪም ከሚመmለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት እንደ አስፈላጊነቱ በመድኃነቶችና ክትባቶች ላይ የመስክ ምርመራ(field trial) በማድረግ ደህንነቱና ፍቱንነታቸውን ለማረጋገጥ እንዲያስችል እንዲሁም ለታለመላቸው ዓላማ ብቁ መሆናቸውንና ለአካባቢ፣ ለእንስሳትና ሰው ደህንነት ጎጅ አለመሆናቸውን ተገቢውን የላቦራቶሪ ምርመራ በማድረግ ደህንነትና ጥራታቸውን ያረጋግጣል፡፡

## ኦዲቱ ዓላማ

18. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን ለመገምገም ይህንን ስራ ለመከታተል ስልጣን የተሰጠው የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ሃላፊነቱን በአግባቡ መወጣቱን እና የእንስሳት መድኃኒትና መኖን በተመለከተ ምዝገባ በማካሄድና የቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ደህንነቱና ጥራቱን የጠበቀ መኖ እንዲሁም ጥራቱ፣ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ለእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ እና ለመኖ አምራቾች፣ ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስመጪዎች፣ ላኪዎች፣ አከፋፋዮች ድጋፍ ማድረጉን ለማረጋገጥ ሲሆን ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

19. ኦዲቱ የሚከናወነው በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ሦስት የበጀት ዓመታት ማለትም ከ2006 በጀት ዓመት እስከ 2008 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ የተሰራውን ሥራ ነው፡፡ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ሲሆን፣ የተለያዩ አግባብነት ያላቸው መረጃዎች በመከለስ፣ ለሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣በተመረጡ ባለድርሻ አካላት በናሙና መርጠ የተለያዩ የኦዲት መረጃዎችን በመሰብሰብና ማስረጃዎችን በመከለስ ፣ ለስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና አሰራሩን በአካል ተገኝቶ በማየት ነው፡፡

20. በዚህም መሠረት ከ28 የእንስሳት መድኃኒት ጅምላ አከፋፋይ፣ 43አስመጪና ከ3 አምራች እንዲሁም ከ1 የእንስሳት መኖ ጅምላ አከፋፋይ፣ ከ12 የመኖ ንጥረ ነገር አስመጪና ከ1 ላኪና ከ11 የመኖ አምራች ድርጅቶች ውስጥ ለ12 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ፣ለ6 የእንስሳት መድኃኒት ጅምላ አከፋፋይ፣ ለ3 ለእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ እንዲሁም ለ2 የመኖ ንጥረ ነገር አስመጪና ለ1 ላኪና ለ9 የመኖ አምራች ድርጅቶች በተጨማሪም ለስድስት ባለድርሻ አካላት (ለኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ፣ለኢትዮጵያ ምግብ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ ለእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር፣ለኢትዩጵያ ምግብና መጠጥ

ኢንሲቲትዩት እና ለእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር) እንዲሁም በባለስልጣኑ ከሚገኘው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ለ3 ቅርንጫፍ መ/ቤቶች በአጠቃላይ ለ41 መ/ቤቶች፣ የኦዲት ቡድኑ በአካል በመገኘት የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስና በመሰብሰብ፣ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር አፈፃፀምን ዙሪያ በአካል ተገኝቶ በማየት ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

21. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ፣ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

22. ከላይ በተለየው የኦዲት አካባቢ ሥር ሦስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱም

1. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት ፡ መኖ ፣ የሕክምና መሣሪያዎችና መገልገያዎችን ጥራትና ደህንነት ለማስጠበቅ እንዲያስችል ምዝገባ በማከናወንና ፈቃድና ደረጃ በመስጠት ኢኮኖሚያዊ፡ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡
2. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒት ፡ መኖ ፣ ሕክምና መሣሪያዎችና መገልገያዎች ዙሪያ ከሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ተዋህዶ ለመስራት እንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን ብቃት ባለው መልኩ ለማስተዳደር የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤
3. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶች ደህንነታቸውና ፈዋሽነታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ እንዲሁም የእንስሳት መኖ ደህንነት በተዘጋጀው የምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ መመዘኛ መስፈርት መሰረት እየተሰራ ስለመሆኑ የድጋፍ ፡ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

### የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች

23. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሶስት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 33 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን የማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 728/2004፣ ደንብ ቁጥር 272/2005ና 325/2006፣ የእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሳሪያዎች አስመጪ፣ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 1/2006 እና የእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሳሪያዎች ችርቻሮ ንግድ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 2/2007 እንዲሁም የመኖ አምራች፣አስመጪ፣ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የምዝገባና የስራ ፈቃድ መስጫ አሰራር መመሪያ ቁጥር 03/2006 እና የዜጎች ቻርተር በተጨማሪም መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 7 ተያይዘዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## 2.1 ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት ፡ መኖ ፣ የሕክምና መሣሪያዎችና መገልገያዎችን ጥራትና ደህንነት ለማስጠበቅ እንዲያስችል ምዝገባ በማከናወንና ፈቃድና ደረጃ በመስጠት ኢኮኖሚያዊ ፡ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤

**<u>የባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥን በተመለከተ፣</u>**

24. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ንግድ ስራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች ወይም ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊያዘጋጅና ሊሰጥ፤ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት በወቅቱ የምስክር ወረቀቱን ሊያድስ፣ ሊያግድና ሊሰርዝ ይገባል፡፡

25. በባለስልጣኑ በመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪነት ፈቃድ ከተሰጣቸው 71 ባለፈቃዶች መካከል በኦዲቱ ወቅት 36 ባለፈቃዶች ፋይላቸው ታይቶ ከባለስልጣኑ ከእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ-አንቀፅ 3,4 እና 5 ውጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀታቸውን የበጀት ዓመቱ በገባ በመጀመሪያዎቹ 2 ተከታታይ ወራት ማለትም በሐምሌና ነሃሴ በተጨማሪም በመስከረምና በጥቅምት የእድሳት ክፍያ ዋጋ 50 በመቶ ቅጣት በመክፈል በወቅቱ ሳያሳድሱ እንዲሁም የፈቃድ እገዳ ወይም ስረዛ ሳይደረግባቸው 3 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች(ዳዊት ያዕቆብ፣ ነዋይ እና ሴፍ) የተገኙ ሲሆኑ፣እንዲሁም 6 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች(የኀብለል ዘርኩ፣ ኤች.ኤች.አር፣ ሳምራዊት፣ ዳምቲት ፔት ፋርማ የሶስት ዓመት፣ በአለማ ፋርምስ እና ማርቆስ) ደግሞ በቅጣት እድሳት የሚፈፅሙበት ጊዜ ያለፈ ቢሆንም ባለስልጣኑ እድሳት የፈፀመላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

26. በሌላ መልኩ አንድ የመኖ ጅምላ አከፋፋይ(አለማየሁ ዘውዴ) እና አንድ የመኖ ንጥረ ነገር አስመጪና ላኪ(ሜሩና) ድርጅቶች በመመሪያው መሰረት መስፈርቱን እንደማያሟሉ እየታወቀ እንዲሁም እንዲያሟሉ የተጠየቀውን መሰረታዊ መስፈርቶች ማሟላታቸው ሳይረጋገጥ ባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፈቃድ የሰጣቸው መሆኑ፣ በ2006

በጀት ዓመት መስፈርት ለሚያሟሉ የመኖ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማዘጋጀትና ለመስጠት የታቀደው በቁጥር 30 ቢሆንም አፈፃፀሙ የእቅዱ 6.66 % ብቻ የተከናወነ መሆኑ እንዲሁም በ2007ዓ.ም ለእንስሳት መድኃኒት ተቋማት የዕድሳት አገልግሎት ለማከናወን 35 ታቅዶ ስለመከናወኑ ያልተገለፀ መሆኑ፣ ከ2006-2008 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 3 የእንስሳት መኖ አምራችና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች (ፔካና፣ ፀሐይ ረዳ እና አለማየሁ ዘውዴ) እንዲሁም በ2008 ዓ.ም 5 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች (ዛከርማ፣ አዳልፕ፣ ዳዊት ያዕቆብ፣ ፓራቬትና ሴፍ) እድሳት እንዳላከናወኑ እና ባለማሳደሳቸውም እንደተሰረዙ ይቆጠራሉ በማለት የወሰደው እርምጃ እንደሌለ የባስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች የገለፁ መሆኑ፣

27. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በአካል የታዩት አንድ(ፒካና) የእንስሳት መኖ አምራች ድርጅት በ2008 ዓ.ም ዕድሳት ያላደረገ መሆኑና ለሌኛው ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ በሲ.ኤም.ሲ ማከፋፈያ ቅርንጫፍ ቢኖረውም ለቅርንጫፉ ህጋዊ የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ያላወጣ ሲሆን፤ 3ቱ ደግሞ ማለትም አዲስ አለም/ሞጆ የእንስሳት መኖ አምራች ድርጅት፣አስኳል የመኖ ማቀነባበሪያ ድርጅት እንደሁም ፍሬንድ ሽፕ አግሮ ኢንዱስትሪ ትልልቅ ድርጅቶች እና የማምረት አቅማቸው ከፍተኛ ቢሆንም ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ያልወሰዱ መሆኑ እንዲሁም 2 የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪ ድርጅቶች( ኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ እና ኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ) ውስጥ ኢኳቶሪያል ከባለስልጣኑ ፈቃድ በመውሰድ በየጊዜው እድሳት ፈፅመናል ቢሉም የ2006 ፈቃድ እድሳት የተፈፀመበት ማስረጃ ያልተገኘ ሲሆን ሁለተኛው ድርጅት ደግሞ ከ2006 ዓ.ም በፊትም ከውጭ ሀገር የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር እያስገባ የነበረ ቢሆንም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያወጣው በ2008 ዓ.ም መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት እድሳት ለማድረግ ባለስልጣኑ ኢንስፔክት ባለማድረጉ መሆኑንና የባለስልጣኑም የመመዘኛ መስፈርቶች ለማሟላት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት በመጠየቁ በተጨማሪም ፈቃድ የሌላቸው ድርጅቶች ፈቃድ እንዲያወጡ ግንዛቤ ባለመስጠቱ እንደሆነ የስራ ኃላፊዎቹ ገልፀዋል፡፡

28. ከዚህም በተጨማሪ ከ3 የመድኃኒትና የክትባት አምራች ድርጅቶች ውስጥ አዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ማምረቻ ከባለስልጣኑ የመድኃኒት ሰርትፊኬት ቢኖረውም ድርጅቱ የተቋቋመው በአዋጅ ነው በሚል ምክንያት ከባለስለጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይሰጣቸው ሲሰሩ እንደነበረ እና የብቃት ማረጋገጫ ለማገኘትም በ 04/12/2008 ያመለከቱ መሆኑ እንዲሁም ብሔራዊ ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት ባለስልጣኑ የGMP ሰርተፍኬት ሰጥቷቸው ለእንስሳት በሽታ መከላከያ የሚውሉ ክትባቶችን እያመረተ ቢሆንም

ከባለስልጣኑ መደኃኒት/ክትባት/ ለማምረት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዳላወጡ የስራ ኃላፊዎቹ ገልፀዋል፡፡

29. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በእድሳት ዙሪያ በቅጣትም ቢሆን የሚያድሱ ድርጅቶች እንዳሉ ነገር ግን አንዳንድ ድርጅቶች ማሳደሱን ረስተው ጥቅምት 30 ካለፈ በኋላ ወይም ከገቢዎችና ጉሙሩክ ጋር በተያያዘ መንገድ ለዚያ ጉዳይ ሲፈልጉ ብቻ እንደሚመጡ ፣ 3ቱ የመድኃኒት አስመጭዎችን በተመለከተ ለዕድሳት ባለስልጣኑን እንዳልጠየቁ ነገር ግን ለወደፊት ከኢንስፔክሽን ክፍል ጋር ተከታትለው እርምጃ እንደሚወስዱ፣ 6ቱ አስመጭዎችን በተመለከተ ደግሞ ከገቢዎችና ጉሙሩክ ጋር የተያያዘ መሆኑና እነዚህ ድርጅቶችም በዚሁ ዘርፍ የቆዩ በመሆናቸው እንዲሁም የመመሪያ ክፍተት እንዳለ ዋና ዳይሬክተሩም በመረዳት በዚያ መሰረት እድሳት እንደፈፀሙ ፤ ሆኖም ግን ሳያሳድሱ የሚሰሩ ድርጅቶች እንዳሉና ይሄንንም ለመቆጣጠር የአሰራር ክፍተት ያለ መሆኑን ፤

30. በተጨማሪ የመኖ ንግድ ስራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች ወይም ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በወቅቱ እድሳት አለመፈጸማቸውን በተመለከተ የመኖ ጉዳይ እንደሌላው ጉዳይ በሁለት እግሩ ያልቆመና በምክር ወደ ራስ ማምጣት ነው የሚለውን አማራጭ መንገድ ወስደን በዚህ መንገድ እየሰራን ነው ማለታቸው፡፡ ይሁን እንጂ ፕሪኮኔክስ የተባለው ድርጅት በባለስልጣኑ እውቅና የሌለው ሲሆን፤ ፀሃይ ረዳ የተባለ ድርጅትም ለባለስልጣኑ ማመልከቻ ያስገባ ቢሆንም ፈቃድ ወስዶ ወደ ስራ ያልገባ መሆኑን፣ ኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕም ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተፅፎለት ንግድ ፈቃዱ እንዲነሳ ወደ እርምጃ እየገቡ መሆኑን፡ አዲስ አለም ፣ ፍሬንድሽፕ አግሮ ኢንደስትሪ እና አስኳል የመኖ አምራች ድርጅቶችን በተመለከተ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ለመውሰድ እንዳልጠየቁ፤ እንዲሁም ፔካናን በተመለከተ እድሳት ለማከናወን ማሟላት ያለበትን መስፈርት ባለማሟላቱ ዕድሳት እንዳልተደረገለት ገልፀዋል፡፡

31. ይህንን በተመለከተ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የ2007ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ በ2007ዓ.ም ሁለተኛ ሩብ ዓመት አፈፃፀም ላይ የተከናወነው ስራ እንደተካተተ ፤እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ሆነው የፈቃድ እገዳ ወይም ስረዛ ሳይደረግባቸው የፈቃድ ጊዜው አልፎ ሲሰሩ የተገኙትን በተጨማሪም እድሳት ሳያከናውኑ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ድርጅቶችን በተመለከተ በወቅቱ እድሳት ባለማድረጋቸው እንደተሰረዙ እንደሚቆጠሩ፣የብቃት ማረጋገጫ ባለመታደሱ ምክንያት ንግድ ፈቃዳቸውም ሊታደስላቸው እንደማይችል፡፡ ሆኖም 6ቱ ድርጅቶች የዕድሳት ማመልከቻ ያቀረቡበት ጊዜ መመሪያው በሚፈቅደው የዕድሳት ወቅት ቢሆንም ድርጅቶቹ ሟሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች በወቅቱ

ባለሚሟላታቸው እና የባለስልጣኑ የኢንስፔክሽን ሪፖርት በሚፈለገው ጊዜ ባለመድረሱ ምክንያት ዕድሳቱ ሊዘገይ እንደቻለ ፣ብሄራዊ የእንስሳት ጤና ኢንስትቲዩት በ2007ዓ.ም የብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቶት በየዓመቱ ዕድሳት እየተደረገለት እንደሚገኝ እና አዳሚቱሉ በ2009ዓ.ም የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ክፍተቱን ሙሉ በሙሉ አሟልቶ በ3ኛው ሩብ ዓመት እንዲያገኝ እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

32. ይሁን እንጂ 6ቱ ድርጅቶች ማመልከቻ ያቀረቡበት ጊዜ በቅጣት ጊዜ መሆኑንና ብሄራዊ የእንስሳት ጤና ኢንስትቲዩት የብቃት ማረጋገጫንም በሚመለከት በኦዲቱ ወቅት ከባለስልጣኑም ሆነ ከድርጅቱ ማስረጃው ተጠይቆ አለመቅረቡ እንዲሁም በፈቃድ ዕድሳትና በእርምጃ አወሳሰድ ዙሪያ በባለስልጣኑ ወጥ የሆነ አሰራር እንደሌለ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ባለስልጣኑ ባለሙያ በሌለበት የእንስሳት መድኃኒት ቤት ንግድ እንዳይካሄድ እንዲሁም የመኖና መኖ ንጥረ ነገሮች ወይም ግብዓቶች ፣ አስመጪ እና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች የመኖ ባለሙያዎችን ስለመቅጠራቸው መቆጣጠሩን በተመለከተ፣

33. ባለስልጣኑ ማንኛውም ሰው የሙያ ፈቃድ የተሰጠው የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በሌለበት የእንስሳት መድኃኒት ቤት ንግድ እንዳይካሄድ ሊቆጣጠር እንዲሁም ማንኛውም የመኖ ማምረቻ ድርጅት ቢያንስ የምርት ክፍል ዋና ኃላፊ እና የጥራት ቁጥጥር ክፍል ኃላፊነት እንዲሁም የመኖ ወይም መኖ ንጥረ ነገሮች ወይም ግብዓቶች አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ቢያንስ የመኖ ሽያጭ ክፍል ኃላፊ ወይም የመጋዘን ሰራተኛ  መስፈርት የሚያሟሉ የመኖ ባለሙያዎችን በመቅጠር  የቅጥር ደብዳቤውን ከብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

34. የእንስሳት መድኃኒት የህክምና መሳሪያዎች አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይነትና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ቁጥጥር መመሪያ ቁ1/2006 ክፍል 4 የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያን በተመለከተ የእንስሳት መድኃኒትና የእንስሳት የህክምና መሳሪያ ንግድ ድርጅት የሙያ ፈቃድ የተሰጠው የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በሌለበት ስራው መካሄድ አይችልም ቢልም  እንዲሁም  ትምህርት ዝግጅቱና ስራ ልምዱ በመመሪያው በተቀመጠው መሰረት መሆን እንዳለበት ቢገለጽም ባለስልጣኑ ማንኛውም ሰው የሙያ ፈቃድ የተሰጠው የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በሌለበት የእንስሳት መድኃኒት ቤት ንግድ እንዳይካሄድ በከፊል ቢቆጣጠርም የተቆጣጠረውም ላይ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፣

35. በኦዲቱ ወቅት በአካል ከታዩት ከ 3 መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ውስጥ እየሰሩ የሚገኙት ባለሙያዎች ከባለስልጣኑ የተሰጠ ጊዜያዊ የሙያ ፈቃድ ሰርተፍኬት እንደሌላቸው ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ከ3ቱ ውስጥ አንደኛው አስመጪ ድርጅት የእንስሳት መድኃኒት ቤቱ ረ/የቴክኒክ ባለሙያ በተደጋጋሚ ያለመኖሩና የመድኃኒት ገቢና ወጪ ሰነድ ላይም ፊርማቸው እንደለሌ ከቁጥጥር ሪፖርት ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በዚህ ዙሪያ ባለስልጣኑ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ፣ ሁለተኛው የእንስሳት መድኃኒት አቅራቢ ድርጅት ረዳት የመጋዘን ባለሙያው የትምህርት ዝግጅቱ በመመሪው መሰረት የማያሟላ መሆኑና ቋሚ የመንግስት ሰራተኛ ማባረር ከህግ አንጻር አስቸጋሪ መሆኑ እና የባለስልጣኑ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት መቀጠሩን ሆኖም ግን ሰራተኛው በገዛ ፈቃዱ ስራውን ሲሰናበት በአዲሱ መመሪያ መሰረት አዲስ ሰራተኛ መቅጠር እንደሚችሉ እና ድርጅቱ ለአርብቶ አደሩና ለሌሎች ተጠቃሚ ደንበኞች በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያቀርብ የመንግስት የልማት ድርጅት በመሆኑ የ2008 ዓ.ም ፈቃድ ዕድሳት በልዩ ሁኔታ ታይቶ እንዲታደስላቸው ባለስልጣኑን ትብብር በጠየቁት መሰረት ዕድሳት መደረጉ፤ እንዲሁም የሶስተኛው ድርጅት የቴክኒክ ኃላፊ በኢንስፔክሽን ወቅት አንድም ቀን ባለመገኘታቸው እና የዴሊቨሪው ሰነድ ላይም የቴክኒክ ሰራተኛ ፊርማ አለመገኘቱን የባለስልጣኑ ኢንስፔክተሮች ጠቅሰው የብቃት ማረጋገጫ እድሳት እንደማይደግፉ ቢገልጹም ድርጅቱ ቅሬታውን ለበላይ አመራር አቅርቦ ወደፊት ያለባቸውን ችግር እንዲያስተካክሉ በማለት መተማመን ላይ በመድረስ ብቻ ፈቃዳቸውን እንዲያድሱ መደረጉ ታውቋል፡፡

36. ከዚህም በተጨማሪ መድኃኒት እና ክትባት ከሚያመርቱ ድርጅቶች ውስጥ በ3ቱም ማለትም በኢስት አፍሪካ የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ እየሰሩ ያሉት ባለሙያዎች የሰው መድኃኒት ባለሙያ እንጂ የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ እንዳልሆኑ እና ከባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት የሙያ ፈቃድ ሳይሰጣቸው እየሰሩ መሆኑን እንዲሁም በዚህ ዙሪያ ባለስልጣኑም እንዳልጠየቃቸውና የባለስልጣኑም መመሪያ መድኃኒት ለመቀመም እና ለማምረት የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ባለመጠየቁ መሆኑን ከስራ ኃላፊዎቹ በቃለ መጠይቅ ወቅት ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣ በሁለተኛው የፀረ ተባይ ማዘጋጃ አክስዩን ማህበር በአሁን ሰዓት እየሰራ የሚገኝ የእንስሳት ባለሙያ እንዳላቸው ቢገልጹም ከባለስልጣኑ ግን የሙያ ፈቃድ እንዳላወጡ እና ይህም የሆነው በባለስልጣኑ ፈቃድ ለማውጣት አስገዳጅ የሆነ ነገር አለመኖሩን የገለፁ ሲሆን፤ በሶስተኛው የእንስሳት ክትባት አምራች ድርጅት የተቀጠረው ደግሞ ከባለስልጣኑ የሙያ ፈቃድ ማውጣት ቢጠበቅበትም በድርጅቱ እየሰሩ የሚገኙት የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያዎች ከባለስልጣኑ የሙያ ፈቃድ ያላወጡ መሆኑን የስራ ኃላፊዎቹ ገልፀዋል፡፡

37. ከዚህም ሌላ በመኖ አምራች ፣አስመጪ ፣ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የምዝገባና የስራ ፈቃድ መመሪያ ቁ. 03/2007 ማንኛውም የመኖ ማምረቻ ድርጅት ቢያንስ የምርት ክፍል ዋና ኃላፊ እና የጥራት ቁጥጥር ክፍል ኃላፊነት እንዲሁም የመኖ ወይም መኖ ንጥረ ነገሮች ወይም ግብዓቶች አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ቢያንስ የመኖ ሽያጭ ክፍል ኃላፊ ወይም መጋዘን ሰራተኛ መስፈርት የሚያሟሉ መኖ ባለሙያዎችን በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤውን ከብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይጠበቅበታል ቢልም በኦዲቱ ወቅት ከባለስልጣኑ ፈቃድ የወሰዱ ድርጅቶች በሙሉ ከመመሪያ ውጭ እንደሚሰሩ እና ባለስልጣኑም በዚህ ዙሪያ እንዳልጠየቃቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡እንዲሁም በመኖ አምራች ፣አስመጪ ፣ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የምዝገባና የስራ ፈቃድ መመሪያ ቁ. 03/2007 መሰረት 5 የእንስሳት መኖ ማደራጃ ድርጅቶች እና የመኖ ንጥረ ነገር አስመጪ ድርጅቶች የባለሙያዎች የቅጥር ደብዳቤ ሳያቀርቡ ፈቃድ የተሰጣቸው ሲሆን እንዲሁም መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ ያወጡትም ድርጅቶች እንዲያሟሉ አለመደረጉና ማስረጃው በማህደራቸውም ውስጥ ያልተገኘ መሆኑ፣

38. በኦዲቱ ወቅት ከታዩ 8 የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጪ እና የመኖ ማቀነባበሪያ ድርጅቶች ውስጥ 8ቱም ከባለስልጣኑ ፈቃድ የወሰዱ ድርጅቶች በሙሉ ከመመሪያ ውጭ እንደሚሰሩ እና ባለስልጣኑም በዚህ ዙሪያ እንዳልጠየቃቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ አንደኛው ድርጅት በመድኃኒት ባለሙያዎች ስራውን እንደሚያከናውን፣ ሁለተኛው ድርጅት እስካሁን ድረስ ባለሙያ አለመቅጠሩ እና ሶስተኛው ድርጅት ደግሞ የባለሙያዎችን የቅጥር ደብደቤያቸውን ከብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ጋር በማያያዝ ለባለስልጣኑ አለማቅረቡ እንዲሁም 5ቱ የእንስሳት መኖ ማቀነባባሪያ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩት የድርጅቱ ባለሙያዎች ከባለስልጣኑ የተሰጠ ጊዜያዊ የሙያ ፈቃድ ሰርተፍኬት እንደሌላቸው በተጨማሪም ባለስልጣኑም ኢንዲያወጡ አለመጠየቁንና ለማውጣት ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አለማድረጋቸው ታውቋል፡፡

39. ስለሁኔታው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በሌለበት የእንስሳት መድኃኒት ቤት ንግድ እንዳይካሄድ መቆጣጠርን በተመለከተ የመድኃኒት አምራቾችን በሚመለከት ባለሙያ ሳይሆን የመልካም አመራረት ሂደትን መከተል እንዳለበት፣ በድርጅቱ የሚሰሩ ባለሙያዎች ተዛማጅ ሙያ ካላቸው መስራት እንደሚችሉ የመልካም አመራረት መመሪያ ላይ የተቀመጠ መሆኑን ሆኖም ግን ማርቆስን

በተመለከተ ረ/ባለሙያ ሳይቀጥር የ3 ወር ክፍተት እንደነበረውና አሁን ባለሙያ መቅጠሩን፤እንዲሁም የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽንን በተመለከተ የሚሰራው ባለሙያ ብቃት ቢኖረውም አዋጁ/መመሪያው/ በሚያስቀምጠው መስፈርት መሰረት አለመሆኑን፡፡ነገር ግን ሌሎች በኦዲት ቡድኑ የቀረቡትን ድርጅቶች ግን ለወደፊት ባለስልጣኑ የሚያጣራ መሆኑን እንዲሁም መስፈርት የሚያሟሉ የመኖ ባለሙያዎችን በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤውን ከብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻ ጋር አያይዞ ማቅረብን በተመለከተ ባለስልጣኑ የመኖ አምራች ተቋማት መስፈርቱን የሚያሟሉ ባለሙያዎችን እንዲቀጥሩ ማድረጉን፡፡ ነገር ግን የሙያ ብቃትን በተመለከተ በሂደት እንዲያወጡ እንደሚያደርግ እና በእንስሳት መኖ ተቋማት ውስጥ ለሚሰሩ ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ እንዲያወጡ በሂደት እንደሚሰራ፤ ይህም የሆነበት ምክንያት ተቋማቶቹ መስፈርቱን የሚያሟሉ የመኖ ባለሙያ ለመቅጠር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እና ባለስልጣኑም እንዲቀጥሩ ግፊት አለማድረጉን፡፡ ለወደፊት ግን ወደዚህ ስራ የሚገቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

40. ይሁንእንጂ ባለስልጣኑ ይህንን በተመለከተ መመሪያ ቢያወጣም መመሪያውን ተግባራዊ አለማድረጉን ለመረዳት ችለናል፡፡

## ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኙ በዘርፉ ላይ እንዳይሰማሩ ለመቆጣጠር የሚስችል የአሰራር ስርዓት በባለስልጣኑ ስለመዘርጋቱና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

41. ባለስልጣኑ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ህክምና መሳሪያ እና መኖ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪ ፣ ላኪ፣ ጅምላ አከፋፋይ ወይም አምራች ድርጅት ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው በዘርፉ እንዳይሰማራ ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግይ ይገባል፡፡

42. ባለስልጣኑ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ህክምና መሳሪያ አስመጪ ወይም ላኪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው በዘርፉ እንዳይሰማራ ለመቆጣጠር የሚስችል የአሰራር ስርዓት ቢዘረጋም በተሟላ መልኩ ተግባራዊ አለማድረጉ እንዲሁም አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው ከ2006-2008ዓ.ም በእንስሳት መድኃኒት ወይም በመኖ ንግድ ስራ ላይ ሲሰማሩ የተገኙ ድርጅቶች ቢገኙም ባለስልጣኑ የንግድ ተቋሙን በማሸግ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰዱ ታውቋል፡፡ ከነዚህም ድርጅቶች ውስጥ በኦዲቱ ወቅት የተገኙት ከ17 ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ የብቃት ማረጋገጫ ለማውጣት የሚያስፈልገውን መስፈርት ሳያሟሉ ወደ ጅምላ አከፋፋይነት ያደጉ ድርጅቶች፣ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው ለ7 ዓመት መኖ ከውጭ በማስመጣት ሲሰራ የቆየ ድርጅት ፣ የጅምላ አከፋፋይነት ፈቃድ

ሳይኖራቸው ለችርቻሮ ድርጅቶች የሚያከፋፍሉ ድርጅቶች መኖራቸው እንዲሁም በመድኃኒት አከፋፋይነትና በመኖ አምራችነት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኙ የተሰማሩ ድርጅቶች ቢኖሩም ባለስልጣኑ እርምጃ ያልወሰደባቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 3 ከሪፖርቱ ጋር ተያይዘዋል፡፡

43. በመሆኑም በኮንትሮባንድ መልክ የእንስሳት መድኃኒት አስመስሎ በማምረት ወይም በማስመጣት የሚያሰራጩ ድርጅቶች እንዲኖሩ ከማድረጉም በላይ ይህ ህገ ወጥ እንቅስቃሴ በመድኃኒት ዋጋ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደረ መሆኑ እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ እና አምራች ድርጅቶች በስራቸውም ላይ እንቅፋት እየፈጠረባቸውና ሀገራዊ ጉዳት እንዳለው፣ በተጨማሪም የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ /ማምረቻ/ ድርጅቶች ገቢ እንዲቀንስ ምክንያት እንደሆነ እና በድርጅቶቹ ላይ ከፍተኛ የመኖ ዋጋ መዛባትና የድርጅቶቹ ተወዳዳሪነት ላይ ጉዳት አስከትሏል፡፡

44. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው በዘርፉ እንዳይሰማሩ ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ በተሟላ መልኩ ተቆጣጥሮ ተግባራዊ አላደረገም የሚለውን በተመለከተ በእንስሳት መድኃኒት ወይም ህክምና መሳሪያ አስመጭ /ላኪ/ ጅምላ አከፋፋይ ዙሪያ እርምጃ ያልተወሰደበት ምክንያት ድርጅቶችን ወደ ስርዓት ለማስገባት ሲሆን፤ አስመጭዎች ለጅምላ አከፋፋይ፤ጅምላ አከፋፋይ ለቸርቻሪዎች የሚለውን የሽያጭ ሰንሰለት በመመሪያ ያወጡበት ምክንያት በጎጃም በረንዳ አካባቢ የሚንቀሳቀሱ የእንስሳት መድኃኒት ቸርቻሪዎችን ወደ መስመሩ ለማስገባት ተብሎ እንደሆነና ስራ ከሚያቋርጡ መስፈርቶችን ዝቅ በማድረግ ባሉበት ሁኔታ እንዲቀጥሉ እንደተደረገ እንዲሁም ዋፍን በተመለከተ በህግ ጉዳይ የተያዘ ቢሆንም የብቃት ማረጋገጫ እንደሚከለከል ባለመታወቁ ባለስልጣኑ እንደሰጠው፤ በተጨማሪም መኖን በተመለከተ ክልል ተሻጋሪ ንግድ የሚያከናውኑ የመኖ አምራቾችን ለመለየት ውስብስብ ስለሆነና ባለስልጣኑም የሚጠበቅበትን ያለመወጣት ክፍተት እንዳለበት፤ ገልፀዋል፡፡

45. በባለስልጣኑ የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ 16 የሚሆኑ ተቋማት በችርቻሮ ፈቃድ አውጥተው ክልል ተሻጋሪ ስራ ቢሰሩም እርምጃ አልተወሰደም ለሚለው በጎጃም በረንዳ አከባቢ የሚገኙትን የችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች ወደ ጅምላ ለመቀየር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ጅምላ የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት እንደተሰጣቸው የመድሃኒት ንግድና ሰንሰለቱን ለማስጠበቅ ከተከናወኑት ውጤታማ ተግባራት መካከል አንዱ እንደሆነ እንዲሁም አስመጪዎች የጅምላ አከፋፋይነት ፈቃድ ሳይኖራቸው ለቸርቻሪ

ድርጅቶች መሸጥን በተመለከተም ሁሉም ህገ ወጥ ስራ እንደሚሰሩ በኢንስፔክሽን ወቅት የታወቀ መሆኑና ችግሩን ለመቅረፍ ለሁሉም በአዋጅ 728/2004 አንቀፅ 26 ላይ የተቀመጠውን ቅጣት ግንዛቤ የመስጠት ስራ ላይ እንደሆኑ እና ቁጥጥሩን እያጠናከሩ እንደሚገኙ በተጨማሪም መቀሌ አከባቢ የሚገኙ ጅምላ አከፋፋዮችን በተመለከተ በክልሎች ውስጥ የሚካሄድ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ንግድ እንቅስቃሴ ማስተዳደርና መቆጣጠር ተግባርና ኃላፊነት በአዋጅ 728/2004ዓ.ም መሰረት የክልሎች እንደሆነና አዳሚ ቱሉ ፀረ-ተባይ ማምረቻ አምራቹ አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ የማምረት ብቃት ማረጋገጫ እንዲወስዱ በተደረገው ውይይት በአሁን ሰዓት በባለስልጣኑ ተመዝግቦ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

## ባለስልጣኑ ደንብ እና መመሪያዎችን በተላለፉ ድርጅቶች/ግለሰቦች ላይ አስተዳደራዊ እና የቅጣት እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ፤

46. ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 728/2004 ወይም ለአዋጁ አፈፃፀም የወጣውን ደንብ ቁጥር 272/2005 ወይም መመሪያዎች በመተላለፍ ሲሰራ የተገኘ ሰውን የምስክር ወረቀቱን ወይም የሙያ ፈቃዱን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ እና ፈቃድ ሳያገኙ መኖ ወይም የመኖ ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ ሊቆጣጠር እንዲሁም አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው በእንስሳት መድኃኒት ወይም በመኖ ንግድ ስራ ላይ ሲሰማሩ ከተገኙና ፈቃድ ለሌለው ሰው መድኃኒት ወይም መኖ ካከፋፈሉ የንግድ ተቋሙን በማሸግ ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
47. ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 728/2008 ወይም ለአዋጅ አፈፃፀም የወጣውን ደንብ ቁጥር 272/2005 ወይም መመሪያዎች በመተላለፍ ሲሰራ የተገኘውን ሰው የምስክር ወረቀቱን ወይም የሙያ ፈቃድ ማገድ ወይም መሰረዝ እንዳለበት በባለስልጣኑ የአሰራር መመሪያ አንቀፅ 24 ንዑስ 1 የተገለፀ ቢሆንም ከ2006-2008 ዓ.ም ከባለስልጣኑ አዋጅ ደንቦችና መመሪያዎች ውጭ ሲሰሩ የተገኙ ድርጅቶች ቢኖሩም የምስክር ወረቀታቸውን ወይም የሙያ ፈቃዳቸውን አግዶም ሆነ ሰርዞ የማያውቅ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ከነዚህም ውስጥ በተመሳሳይ ደረጃ ላሉ ድርጅቶች የመድኃኒት ሽያጭ የፈፀሙ፣የግዥ ፈቃድ ከባለስልጣኑ ሳያገኙ መድኃኒት ግዥ የፈፀሙ፣ የመኖ ማከፋፈያ ኮንቴነር ውስጥ በቂ የአየር ዝውውር ሳይኖር ሲሰሩ የተገኙ እንዲሁም ከመድኃኒት ጋር የሚላክ ሊፍሌት ሳይኖር መድኃኒት ያስገቡ በተጨማሪም በእንስሳት ህክምና መሳሪያ ላይ ያለው ሌብል እና አስተሻሸግ ላይ ለእንስሳት አገልግሎት ብቻ የሚል ፁሑፍ ሳይኖረው እና ጥንቃቄ ባልተወሰደበት መኖና ኬሚካል በአንድ ኮንቴነር ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቡ ድርጅቶች ተገኝቷል፡፡በአባሪ1 ተያይዟል፡፡

48. በኦዲቱ ወቅት የተገኙት 3 ድርጅቶች የመኖ አስመጪ ድርጅት ማሟላት የሚገባው 10 መስፈርቶች በመመሪያ ላይ የተቀመጡ ቢሆንም ይሄንን በመተላለፍ ሲሰሩ ተገኝተዋል፡፡ከነዚህም ውስጥ አንድ የመኖ ላኪና የመኖ ንጥረ ነገር አስመጪ ድርጅት ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳያወጣ በባለስልጣኑ ለራስ ፍጆታ መጠኑ ባልታወቀበት ሁኔታ በአንድ ጊዜ ብቻ እስከ 167600 ኪ.ግ ወይም 167.6 ቶን ለራስ ፍጆታ ብቻ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባና የተጠቀመ መሆኑ እንዲሁም የእንስሳት ተጨማሪ ምግብ/Feed additive/ ማለትም ለጫጩት የሚሆን choline chloride 60%፣Profish supper protex 4%፣Mono calcium phosipate፣Vitamine & Mineral premix፣Avatek Monansin and Zincbacintrcin ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ባለስልጣኑን የግዥ ትዕዛዝ በመጠየቅ 1.6 ቶን ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያወጣ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ መሆኑን በ2008ዓ.ም ከባለስልጣኑ በተሰጠው የግዥ ትዕዛዝ ፈቃድ እና በኦዲቱ ጊዜ በተሰጠው መግለጫ የታወቀ መሆኑ፤

49. ሁለተኛው ድርጅት ደግሞ የእንስሳት መኖ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው ለ7 ዓመታት ሲሰራ የቆየ እና ከውጭ ሀገር የድመትና ውሻ መኖ ማስገባቱ እየታወቀ በይቅርታ ደብዳቤ ብቻ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ኮሜት ኬላ የተያዘበትን መኖ እንዲለቀቅለት በባለስልጣኑ ባለሙያዎች የተወሰነ መሆኑ፣ እንዲሁም ሶስተኛው አስመጪና ላኪ የሆነ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው የእንስሳት መኖ ከውጭ ሀገር በማስመጣት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ ቢሆንም ባለስልጣኑ ካለምንም እርምጃ ድርጊቱ የተፈፀመው በቸልተኝነት ያልሆነ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ምርቱ ተፈትሾ እንዲለቀቅላቸው በማለት በድጋሚ ይሄ ድርጊት ከተፈፀመ ግን ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ እንደሚገደዱ ገልፀው የለቀቁላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

50. እንዲሁም ማንኛውም የእንሰሳት መድኃኒት ወይም መኖ አምራች፣አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ፈቃድ ለሌለው ሰው መድኃኒት ወይም መኖ ካከፋፈለ ባለስልጣኑ እርምጃ ሊወስድ ይገባል ቢልም በኦዲቱ ወቅት በአካል የታዩት ፈቃድ ለሌለላቸው ግለሰቦች፣ ለ የመንግስት ድርጅቶች፣ ለዩኒቨርሲቲዎች እና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች(NGO's) መድኃኒት ወይም መኖ አከፋፍለው የተገኙ 8 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ቢኖሩም ባለስልጣኑ ምንም ዓይነት እርምጃ አለመውሰዱን ለማወቅ ተችሏል፡፡የእነዚህ ድርጅቶች ዝርዝር በሠንጠረዥ 1 ከሪፖርቱ ጋር በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

51. የመኖ አምራች፣አስመጪ፣ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የምዝገባና የስራ ፈቃድ መስጫ የአሰራር መመሪያ 03/2007 ማንኛውም የመኖ ንጥረ ነገሮች ወይም ግብዓቶች ንግድ ድርጅት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ መኖ ወይም የመኖ ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ

ሊቆጣጠር ይገባል ቢልም ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኙ የመኖ ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቡ ድርጅቶች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

52. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የባለስልጣኑ የቅርንጫፍ ፅ/ቤት በቅርብ ጊዜ ስለተቋቋመ የእርምጃ አወሳሰድ መመሪያ በወቅቱ እንዳልተዘጋጀ፡፡ በዚህም የተነሳ የአሰራር ክፍተቶች ሊፈጠሩ እንደቻሉ፤ መመሪያውን ካወጡ በኋላም ወደ እርምጃ አወሳሰድ ያልተገባበት ምክንያት በቅድሚያ የማስተማርና የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎችን በመስራት በመጠመዳቸው መሆኑንና ይህም ድርጅቶችን ለማበረታታትና ከገበያ እንዳይወጡ ለማድረግ በማሰብ እንደሆነ፡፡ ሆኖም ግን መመሪያው በአሁን ወቅት ቢዘጋጅም እስካሁን ድረስ ያልፀደቀና በሂደት ላይ የሚገኝ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት እርምጃ ለመውሰድ ምቹ ሁኔታ አለመፈጠሩንና ከበላይ አመራር ጋር በመመካከር እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን በተጨማሪም በአሁን ወቅት በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ለመድኃኒቶች የግዥ ትዕዛዝ ሳይጠየቅባቸው ወደ ሀገር ውስጥ እንደማይገቡ እና ወደ እርምጃ አወሳሰድም እንደገቡና የማስጠንቀቂያ ደብዳቤም ለህገ ወጦች መስጠት እንደጀመሩ ገልጿል፡፡

53. በተጨማሪም እርምጃ ለመውሰድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሙአቸው ከዋና ዳይሬክተሩ ጋር በመነጋገር እርምጃ እየወሰዱ መሆኑንና ፈቃድ ሳያገኙ መኖ ወይም የመኖ ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ መቆጣጠርን በተመለከተ 3ቱም ድርጅቶች በቀድሞ ጊዜ ከኢትዮጵያ ምግብ፣ መድኃኒት እና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ፈቃድ የተሰጣቸው ስለሆነ በአሁኑ ወቅት ፈቃድ መስጠት ያለበት አካል ማን እንደሆነ አናውቅም በማለት ኬላ ላይ ሲያስገቡ የተያዙበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን፤

54. በሌላ በኩል የግል ፍጆታን በሚመለከት በአዋጅም ሆነ በመመሪያ ላይ በግልጽ ያልተቀመጠ ቢሆንም እነዚህ ድርጅቶች ግን ከአስመጭዎች መግዛት እንደሚኖርባቸው እንደሚታወቅ፤ እንዲሁም ባምቢስን በተመለከተ በማኔጅመንት ተወያይተውበት ህገ ወጥ ስራ ሰርቶ እያለ ባለስልጣኑ እንዲለቀቅለት ማድረጉ ተገቢ እንዳልሆነ በአጠቃላይ ክፍተቶች እንዳለባቸው ፤ ፈቃድ ለሌለው ሰው መድኃኒት ወይም መኖ አከፋፍለው የተገኙ ድርጅቶች ላይም እርምጃ መውሰድን በተመለከተ የኢስት አፍሪካ ሀገራዊ ጉዳቱ ያመዝናል በሚል የተመሰረተበት ክስ በፍትህ ሚኒስተር በኩል እንዲነሳ መደረጉን፣ የግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽንን በተመለከተ ግን ከባለስልጣኑ አሰራር ስርዓት ውጭ እየሰራ እንደሚገኝና አካሄዱም ትክክል እንዳልሆነ ቢገነዘቡም እርምጃ ያልወሰዱበት ምክንያት የመድኃኒቱ ጥራትና ደህንነት ላይ ብቻ ትኩረት በመደረጉ እንደሆነ፡ ከነዚህ ድርጅቶች ውጭ በኦዲት ጊዜ የቀረቡት ድርጅቶች ላይ የባለስልጣኑ የኢንስፔክሽን ቡድንም ይህንን ጉዳይ አይተናል ብሎ እስካሁን ያቀረበ ባለመኖሩና ባለስልጣኑም የኦዲት ቡድኑ በሂደው አካሄድ ባለመሄዱ የተፈጠረ መሆኑ፤

55. በተጨማሪም ከባለስልጣኑ የአሰራር መመሪያ ውጭ በህገ ወጥ መልክ የሚሰሩ ድርጅቶችን ወይም ግለሰቦችን ለመቆጣጠር የሚያስችል አቅም፣ የቁሳቁስና የትራንስፖርት አቅርቦት ችግር በመኖሩም ጭምር ስራውን በተገቢው ሁኔታ ለመስራት አለማስቻሉን አብራርተዋል፡፡ ከዚህም ሌላ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው በእንስሳት መድኃኒት ወይም በመኖ ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው በተገኙ ድርጅቶች ባለስልጣኑ የንግድ ተቋሙን በማሸግ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰዱን በተመለከተ የንግድ ተቋሙን በማሸግ እርምጃ ያልወሰደው አንዳንድ ጉዳዮችም በማኔጅመንት በመወሰኑ ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

56. ይህንን በተመለከተ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ከባለስልጣኑ አዋጅ፣ደንቦችና መመሪያዎች ውጭ ሲሰሩ የተገኙ ድርጅቶችን በተመለከተ ቀደም ሲል የነበረ አሰራር አስመጪ ለቸርቻሪ፣ ቸርቻሪዎች ደግሞ እንደ ጅምላ አከፋፋይ ሲሰሩ የነበረ ቢሆንም ግንዛቤ በመፍጠርና የማስተካከያ እርምጃዎችን በመውሰድ እንደተስተካከለ በተጨማሪም ባለስልጣኑ አዲስ ከመሆኑ የተነሳ የግንዛቤ ስራ እየሰጠ መቆየቱንና አሁን ወደ መስመር እንደገቡ እንዲሁም ፈቃድ ለሌለው ሰው መድኃኒት ወይም መኖ ላከፋፈለ ድርጅት እርምጃ መውሰድን በተመለከተ ለመንግስት ድርጅቶች፣ ለዩኒቨርሲቲዮች እና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች መድኃኒትና መኖ አከፋፍለዋል ለሚለው እነዚህ ድርጅቶች ንግድ የማያካሂዱና ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ስለሆኑ የብቃት ማረጋገጫ እንደማያስፈልጋቸው በተጨማሪም የመኖ አምራች ድርጅቶች በሂደት ጅምላ አካፋፋዮችና ቸርቻሮ ድርጅቶች ሲደራጁ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደሚኖራቸው እስከዛ ግን ድርጅቶቻቸው መዘጋት ስለሌለበት ሽያጭ እንደሚያካሂዱ ተገልጿል፡፡

57. ይሁን እንጂ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መመሪያው ፀድቆ ተፈፃሚ እንዳልሆነ እንዲሁም ህገወጥ የሆኑ ድርጅቶች ቢኖሩም እርምጃ አወሳሰድንም በተመለከተ በባለስልጣኑ አዋጅና መመሪያዎች መሰረት ወጥ የሆነ የእርምጃ አወሳሰድ ስርዓት አለመኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ባለስልጣኑ በደንብ ቁጥር 325/2006 በወጣው ተመን መሰረትድርጅቶች በወቅቱ የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈፅሙ ማድረጉን በተመለከተ፣

58. ባለሰልጣኑ ለእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሳሪያዎች፣ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ ባለሙያዎች፣ ለንግድ ማስታወቂያ፣ ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተቋማት ምዝገባና ፈቃድ ለመስጠት እንዲሁም በውጭ አገር አምራች ኩባንያዎች ለእንስሳት መድኃኒት የመልካም አመራረት ተሞክሮ ምልከታ ለማድረግ በደንብ ቁጥር 325/2006 በወጣው ተመን መሰረት በወቅቱ የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈፀም ሊያደርግ ይገባል፡፡

59. ባለሰልጣኑ በደንብ ቁጥር 325/2006 በወጣው ተመን መሰረት ከህዳር 12/2007 ዓ.ም ጀምሮ እንዲያስፈፅም የተደነገገ ሲሆን ክፍያ እንዲሰበሰብ የተደረገው 7 ወራቶችን በመዘግየት በሐምሌ 3/2007 ዓ.ም ማስታወቂያ የወጣ መሆኑና ባለስልጣኑም ይህንን ስራ ለመስራት አቅዶ እንዳላከናወነ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት በወጣው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ያልፈፀሙ የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና አምራች እንዲሁም የመኖ አምራች፣ የመኖ ንጥረ ነገር አስመጪ ድርጅቶች ያሉ መሆኑ፣

60. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው 7 የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ እና የመኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጭ ድርጅቶች ከ2005-2007 ዓ.ም ፈቃድ እድሳት ክፍያ አለማከናወናቸው እና ሌሎች 3 የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጭ ድርጅቶች ውስጥ ደግሞ 2ቱ የ2005 ና አንዱ የ2007 ፈቃድ ያወጡበትን ክፍያ ያልፈፀሙ ሲሆን፤ እንዲሁም ሁለት የእንስሳት መድኃኒት አስመጪና አከፋፋይ ድርጅቶች በ2007ዓ.ም ከባለስልጣኑ ፈቃድ ያገኙ ቢሆንም በወጣው ተመን መሰረት እስከ ሰኔ/2008 ዓ.ም ድረስ ያለውን እና አንድ  የመኖ ጅምላ ንግድ ድርጅት  የአገልግሎት ክፍያ አለመፈፀማቸው፤ በተጨማሪም አንድ የመኖ አስመጪና ላኪ ድርጅት የአስመጪነት ፈቃድ በ2008 ዓ.ም የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ፈቃድ እንዳወጣ የድርጅቱ የስራ ኃላፊዎች ቢገልፁም በኦዲቱ ወቅት ክፍያ የተፈፀመበት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑና ሌላ አንድ የእንስሳት መኖ ማደራጃ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ድርጅት ደግሞ ለባለስልጣኑ የአገልግሎትም ሆነ  የዕድሳት ክፍያ ከፍሎም ሆነ ባለስልጣኑም ጠይቆ እንደማያውቅ የታወቀ መሆኑ፣

61. ከዚህ በተጨማሪም ባለስልጣኑ የላብራቶሪ የምርመራ አገልግሎት አሰጣጥና የክፍያ አሰባሰብ ተመንን በተመለከተ ህጋዊ ሰነድ በማዘጋጀትና በበላይ አካል እንዲጸድቁ በማድረግ ተፈፃሚ ለማድረግ አቅዶ ያላከናወነ ሲሆን ከዚህም ሌላ በብር 200,000 የአገልግሎት ክፍያ በመሰብሰብ ገቢን ለማሳደግ አቅዶ ስለመከናወኑ ያልተገለፀ መሆኑ እንዲሁም ኢስት አፍሪካን ፋርማሲውቲካል ኃ.የተ.ድርጅት ባለስልጣኑ የዳግም ምዝገባ ክፍያ የመ/ቤቱ ክፍያ ተመን አፀድቆ በስራ ላይ ሲያውል የሁለት ጊዜ እንደሚከፍሉ እንዲሁም የለውጥ/variation/ ክፍያ ፣የፓኬጅንግ እና የextension of life የሚከፍሉ መሆኑን አሳውቆ በግንቦት/2007 ዓ.ም የሰጣቸው ቢሆንም የኢንቬስትመንት አዋጅ ለውጭ ሀገር ኢንቬስተሮች ይፈቅዳል በማለት የኢንቬስትመንት አዋጅና ደንብ ውጭ ካለምንም ክፍያ እንዲጠቀሙ በባለስልጣኑ የተፈቀደ መሆኑ ታውቋል፡፡

62. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ባለስልጣኑ በ2005 ዓ.ም ስራውን ሲጀምር የአገልግሎት ክፍያ ደንብ አፀድቆ የአገልግሎት ክፍያ ለመሰብሰብ አለመቻሉን ነገርግን ተቋማትን የውዴታ ግዴታ በማስገባት ፈቃድ ሲሰጥ እንደቆየ፡፡ ሆኖም ግን ደንቡ ፀድቆ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ወደኋላ ተመልሰው ለድርጅቶቹ ደብዳቤ ፅፈው ያለባቸውን ውዝፍ ክፍያ

እንዲከፍሉ መደረጉን፡፡ ይሁን እንጂ በመድኃኒት ዘርፍ ክፍያ አልከፈሉም ተብለው የተጠቀሱትን ድርጅቶች ስለመክፈላቸውም ይሁን ስላለመክፈላቸው መረጃውን ለወደፊት እንደሚያጣሩትና ኢስት አፍሪካ የመድኃኒት አምራች ድርጅትን በተመለከተ በቀድሞው ጊዜ ለኢትዮጵያ የምግብና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ክፍያ የማይፈፅም በመሆኑ በነበረው ልምድ ባለስልጣኑም ክፍያ እንዳላስከፈላቸው በተጨማሪም የባለስልጣኑም የክፍያ ማስፈፀሚያ ደንብ የሀገር ውስጥ አምራቾችን የመድኃኒት ምዝገባ እንዳላካተተ፡፡እንዲሁም በመኖ ዘርፍ የፈቃድ እድሳት ክፍያ ሳይፈፅሙ እድሳት የተከናወነላቸው ድርጅቶች አለመኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

63. በደንብ ቁጥር 325/2006 በወጣው ተመን መሰረት በወቅቱ የአገልግሎት ክፍያ መሰብሰብን በተመለከተ ባለስልጣኑ ለሚሰጣቸው ግልጋሎቶች ክፍያ እንደሚሰበስብና ከነዚህም መካከል የሰነድ ምዝገባ አንዱ እንደሆነና በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመት ገቢ እንደተሰበሰበ በእንስሳት መድኃኒት ዳይሬክቶሬት የተገለፀ ሲሆን በእንስሳት መኖ ዳይሬክቶሬት ደግሞ የመኖ ንግድ ተቋማትን በተመለከተ ደንቡ በሚኒስቴሮች ም/ቤት የፀደቀው ህዳር12/2007 በመሆኑ ወደ ኋላ ተመልሶ ማስከፈል አግባብነት የሌለው አሰራር ከመሆኑም በላይ ከሀምሌ1/2007 ጀምሮ ግን ክፍያ የተፈፀመበትን ከባለስልጣኑ ፋይናንስ መረጃ ማሰባሰብ እንደሚቻል እንዲሁም ከህዳር ወር በኋላም እስከ ሰኔ 30/2007 ድረስ የሰነዶችና የፋይናንስ ዝግጅት ጊዜ የነበረ መሆኑ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ተገልጿል፡፡

64. ይሁን እንጂ ደንቡ ከመፅደቁም በፊት በባለስልጣኑ መመሪያ ማለትም በእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 1/2006 ገፅ 33 ላይም የተገለፀ ሲሆን፣በወቅቱ ሳይሰበሰብ የቀረው ገንዘብ እንደተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በፋይናንስ መመሪያ የመንግስትን ገንዘብ ወደ ኋላ ተመልሶ አለማስከፈል አግባብነት የሌለው አሰራር ሆኖ ተገኝቷል ፡፡

## የእንስሳት መድኃኒቶችንና የህክምና መሳሪያዎች ፣ ንጥረ ነገሮችንና ውህዶችን እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ገምግሞ ስለመመዝገቡ፣ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማደሱ፣ እና በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ምዝገባውን ስለማገዱና ስለመሰረዙ በተመለከተ፣

65. ባለስልጣኑ ለእንሰስሳት ለውጭ ጥገኛ ህክምና ወይም ለእንስሳት በሽታ አስተላላፊ ተባዮች መቆጣጠሪያ አገልግሎት የሚውሉ ንጥረ ነገሮችንና ውህዶችን ሊመዘግብ እና ሊቆጣጠር፣በአገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎች ፣ እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ገምግሞ ሊመዘግብ፣ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ምዝገባውን ሊዲያድስ፣ ሊያግድና ሊሰርዝ እንዲሁም

የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ የምስክር ወረቀት በምዝገባው መስፈርቶች መሰረት በየ5 ዓመቱ ሊያዲስ ይገባል፡፡

66. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከታዩት የአዳሜቱሉ የእንስሳት ፀረ-ተባይ ማምረቻ ድርጅት ለእንስሳት መድኃኒት የሚውል VETAZINON 60% (Diazinon) /pesticides for use in veterinary/ የሚያመርት ቢሆንም በባለስልጣኑ በአምራችነት ያልተመዘገበ መሆኑና ፋብሪካውም ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ለማውጣት የሚያስችለውን መስፈርት የማያሟላ መሆኑ በባለስልጣኑ የክትትል ሪፖርት እና ለዋና ዳይሬክተር በተላለፈው ማስረጃ የታወቀ መሆኑ፣ በተጨማሪም ለውጭ ጥገኛ ህክምና ወይም ለእንስሳት በሽታ አስተላላፊ ተባዮች መቆጣጠሪያ አገልግሎት የሚውሉ ንጥረ ነገሮችንና ውህዶችን ማለትም Ethiomiraze 12.5 Ec lit panch የተባለ ከባለስልጣኑ የመድኃኒት የምዝገባ ሴርተፍኬት ከማግኘቱ በፊት እያመረተ ይሸጥ እንደነበር መታወቁ፤ እንዲሁም ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ከባለስልጣኑ ጋር በጋራ ባለመሰራቱ የተነሳ ዲያዚኖን የተባለ ፀረ-ተባይ መድኃኒት ለእንስሳት መድኃኒትነትና ለእፅዋት ፀረ-ተባይ(አረም) ማጥፊያነት እየዋለ እንደሚገኝ እና በመመሪያ የተለየበት ሁኔታ አለመኖሩን ከዚህም በተጨማሪ መጠኑ ባልተለየበት ሁኔታ ለአረም እና ለእንስሳት አገልግሎት እንዲውል በመደረግ ላይ መሆኑ ታውቋል፡፡

67. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ የምስክር ወረቀት በከፊል በየ 5 ዓመቱ ቢያድስም በራሱ የምዝገባ መስፈርት በማዘጋጀትና አፀድቆ እየሰራበት አለመሆኑ እና በቀድሞ ጊዜ በኢትዮጵያ ምግብ፣መድኃኒትና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት የሚሰራ ቢሆንም በተሟላ መልኩ በምዝገባው መስፈርቶች መሰረት እንደማይሰራ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 728/2004 ክፍል 2 አንቀፅ 5/3 ላይ የመድኃኒት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማብቃቱ ከ3ወራት በፊት መቅረብ ይኖርበታል ቢልም ከባለስልጣን መ/ቤቱ በእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ አስመጪነት ፈቃድ ከወሰዱ እና እስከ መስከረም 30/2009 ዓ.ም በባለስልጣኑ ዝርዝር ማስረጃ ውስጥ ከተካተቱ ወደ 30 ከሚሆኑ ድርጅቶች ውስጥ 16 የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ አስመጪ ድርጅቶች የመድኃኒት ሴርተፍኬት ጊዜያቸው አብቅቶ ለዕድሳት በሂደት ላይ ያሉ 63 ዓይነት መድኃኒቶች ያሉ ሲሆን እነዚህም መድኃኒቶች የሴርተፍኬት ጊዜያቸው ካበቃ ከ5ወር እስከ 6ዓመት ቢሆንም ጊዜያዊ ሴርተፍኬት እስኪሰጣቸው ድረስ መድኃኒቱን ከውጭ ሀገር አስገብተው በመሸጥ ላይ እንደነበሩ እና በኦዲቱ ወቅትም በመሸጥ ላይ መሆናቸውና ሌሎች ደግሞ እድሳት ቢያደርጉም የመድኃኒቶቹ ናሙና በላብራቶሪ ታይቶ እንዳልሆነ ለማወቅ

ተችሏል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በኦዲቱ ወቅት በአካል የታዩት ድርጅቶች በአባሪ 4 ተያይዘዋል፡፡

68. እንዲሁም ባለስልጣኑ በአገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎች በከፊል ገምግሞ ቢመዘግብም ፣ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ሙሉ በሙሉ ገምግሞ እንዳልመዘገበ እንዲሁም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ምዝገባውን አለማደሱ፣ አለማገዱ እና አለመሰረዙ ታውቋል፡፡በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት ማስረጃዎችና በናሙና ከታዩት ድርጅቶች መካከል በባለስልጣኑ ሳያስመዘግቡ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎች እንዲሁም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች ይዘው የተገኙ ድርጅቶች ዝርዝር በአባሪ 5 ተያይዘዋል፡፡

69. በመሆኑም ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የእንስሳት መድኃኒቶችና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎች ፣የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች ወቅቱን ጠብቀው በላብራቶሪ ታይተው እንዳይመዘገቡ እና በባለስልጣኑ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት በዘርፉ የሚከናወኑ ስራዎች ተግባራዊ እንዳይሆኑ ከማድረጉም በላይ ህገ ወጥ አሰራሮችም እንዲበራከቱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

70. ይህንንም በተመለከተ ባለስልጣኑ በአገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎችን እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን መዘርዝር የያዘ መመሪያ እስካሁን አለማዘጋጀቱንና መረጃም እንደሌለው፣ በዚህም ምክንያት እንዳልመዘገበ በቃለ መጠይቅና የመኖ ጥራት ደረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሰጡት በመግለጫ የገለፁ ሲሆን፡ ከዚህም ሌላ መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎችን ለመመዝገብ ሶስት የግምገማ መስፈርቶች ያሉት መሆናቸውን፡- አንደኛ የመድኃኒት ሰነድ ግምገማ፣ ሁለተኛ የመልካም አመራረት ምልከታ(GMP) እና ሶስተኛው የላብራቶሪ ጥራት ፍተሻ ናቸው፣

71. ይሁን እንጂ ባለስልጣኑ በአገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎች ገምግሞ ለመመዝገብ፣ የሚያስችል መመሪያ ማውጣትን በተመለከተ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ለእንስሳት መድኃኒት ምዝገባ ሰነድ ግምገማ የወጣውን መመሪያን መሰረት በማድረግ ለሰነድ ግምገማ እንደሚጠቀሙ እና ባለስልጣኑ ስራውን ከጀመረ በኃላ ቅድሚያ መዘጋጀት ያለባቸውን የተለያዩ የአሰራር መመሪያዎችን እንዳወጣና ከመድኃኒት ምዝገባ ጋር ተያይዞ ከዚህ በፊት ያለው መመሪያ መድኃኒት ሰነድ ገመግሞ ለመመዝገብ ስለሚያስችልና በአሰራርም ላይ የጎላ ችግር እስካሁን እንዳልገጠማቸው ነገር ግን መመሪያው ከተዘጋጀ ረጅም ጊዜ በመሆኑ ለማሻሻል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር ጥረት መጀመሩን፣የመልካም አመራረት ምልከታን(GMP) በተመለከተ በዓለም

አቀፍ ደረጃ በተቀመጠው አሰራር መሰረት ከሚመለከታቸው የስራ ሂደቶች ጋር በቅንጅት ምልከታ ተካሂዶ ውሳኔ እንደሚሰዋ በተጨማሪም ጥራቱን ማረጋገዋን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ምግብ፣መድኃኒትና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን በሚመጣው የጥራት ውጤት መሰረት እንደሚከናወን የእንስሳት መድኃኒት ጥራት ደረጃ፣ ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክረቶሬት ዳይሬክተር በሰጡት መግለጫ ገልፀዋል፡፡

72. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ባለስልጣኑ ለእንሰስሳት ለውጭ ጥገኛ ህክምና ወይም ለእንስሳት በሽታ አስተላላፊ ተባዮች መቆጣጠሪያ አገልግሎት የሚውሉ ንጥረ ነገሮችንና ውህዶችን በተሟሏ መልኩ በመመዝገብ አለመቆጣጠሩን በተመለከተ አዳሚ ቱሉ በቀድሞው ጊዜ በነበረው ባለስልጣን ስር ስለነበር በባለስልጣኑ ሳይመዘገብ ጥቅም ላይ የዋለ መድኃኒት ስለመኖሩ እንደማያውቁትና: መረጃም እንደሌላቸው ነገር ግን ዲያዚኖን የተባለውን መድኃኒት ለእንስሳትና ፀረ-ተባይ ማከሚያነት እና ለፀረ-አረም መጠቀም ቢቻልም ለቬተርናሪ አገልግሎት የሚውል ብቻ የሚል ፅሁፍ ሊኖረው እንደሚገባ፡ ይሁን እንጂ በዚህ ዙሪያ ለተጠቃሚው ግንዛቤ እንዳልሰጡ የገለፁ መሆኑ፤

73. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ የምስክር ወረቀት በተሟላ መልኩ በየ5 ዓመቱ አለማደሱንና በራሱ የምዝገባ መስፈርት በማዘጋጀትና አፀድቆ እየሰራበት አለመሆኑን በተመለከተ፡-

74. ባለስልጣኑ ከምግብ፣ ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ስራውን ተረክቦ ማስቀጠል ስለ ነበረበት በዚህ ልምድ መሰረት በቀድሞ ጊዜ በባለስልጣኑ ወጥቶ ሲሰራበት በነበረው ጋይድ ላይን/መመሪያ/ መሰረት በማድርግ እየሰራ ሲሆን ፤ መመሪያውም ያሰራ ስለነበረ ትኩረት የተደረገው ሌሎች መመሪያዎችን ወደ ማውጣት ስለነበረ ይህንንም መመሪያ ለማዘጋጀት ጊዜ ያልነበራቸው እና የአቅም ክፍተትም ስለነበረና የመድኃኒት ምዝገባ በራሱ ሂደት ስለሆነ የዕድሳት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶችም እንዳሉ፡፡ ይህም አዲስ እና ነባር መድኃኒቶችን ለማስመዝገብ ወይም ዕድሳት ለማከናወን ስጋቱ አንድ አለመሆኑን፤ አዳዲስ መድኃኒቶች ላይ የበለጠ ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩበት ሁኔታ ያለ ሲሆን ነገር ግን ነባሮችን በተመለከተ ጥራታቸውንና ደህንነታቸው ከዚህ በፊት በነበረው ተቋም/EFMHACA/ ስለሚታወቅ ያለ ላብራቶሪ ፍተሻ ዕድሳት የሚከናወንበት ሁኔታ እንዳለ፤ ይሁን እንጂ ጊዜያዊ ሰርትፊኬት እስኪሰጣቸው ከውጭ ሀገር አስገብተው እንዲሸጡ የተደረገውም የባለስልጣኑ ላብራቶሪ ስራ ባለመጀመሩ እና የቀድሞው ባለስልጣን አናስተናግድም በማለቱ በማኔጅመንት ተወስኖ እንዲሰሩ መደረጉን በዚህም የተነሳ ባለ ፈቃዶች ሳያመለክቱ ጊዜ የሄደባቸው መሆኑንና እስከ 2 ዓመትና ከዚያ በላይ የቆዩበት ሁኔታ የነበረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

75. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በየ5ዓመቱ የሚታደሰውን የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ ምስክር ወረቀትን በሚመለከት ባለስልጣኑ በተቀመጠው የዓለም አቀፍ መመዘኛዎች መሰረት መድኃኒት ምዝገባ እያካሄደ እንደሚገኝና ለምዝገባም የሚጠቀመው መመሪያ የኢትዮጵያ ምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን ለእንስሳት መድኃኒት ይጠቀም የነበረውን ሲሆን መመሪያውም ያልተከለሰበት ምክንያት የሚያሰራ በመሆኑ ታሳቢ በመደረጉ እንደሆነ እንዲሁም ከባለስልጣኑ እስከ መስከረም 2009 ተብሎ የተሰጠው መረጃ ላይ ከተዘረዘሩት ድርጅቶች ውስጥ 4 ድርጅቶች በዳግም ምዝገባ ሂደት ላይ ያለ መድኃኒት እንዳልነበራቸው እና የመድኃኒቶችም ቁጥር 46 እንደሆነ በእነዚህ መድኃኒቶች ላይ የጥራት የመፈወስም ሆነ የደህንነት ሁኔታቸውን ከዚህ በፊት ስለተረጋገጠ እና ችግር አለባቸው የሚል ጥቆማ ከተጠቃሚው ህብረተሰብ ያልቀረበ መሆኑና በቀድሞ ባለስልጣን መ/ቤትም የሚሰራበት አሰራር ስለማይከለክል ለዳግም ምዝገባ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ማስገቢያ ፈቃድ እንደሚሰጥና የዘገየበትም ምክንያት የምዝገባ ስራ በመቋረጡ እና ከቀድሞው ባለስልጣን ፋይሎችን ለማምጣት ጊዜ በመውሰዱ እንደሆነ ሆኖም ግን የራሱ የሆነ የምዝገባ መስፈርት የለውም ለሚለው የባለስልጣኑ አደረጃጀትና መዋቅሩ ከቀድሞው ባለስልጣን ቢለይም የመድኃኒትን ጥራትና ፈዋሽነት ለማስጠበቅ የሚፈለገው ሳይንሳዊ የምዝገባ ስልት ለሰውም ሆነ ለስንስሳት አንድ ዓይነት በመሆኑና አለምአቀፋዊ በመሆኑ እንዳለ ተቀብለው እየሰሩበት እንደሆነና የምዝገባ መመሪያውንም ለማሻሻል እየሰሩ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

76. ይሁን እንጂ ባለስልጣኑ በራሱ መመሪያዎች ላይ ወቅታዊ ማሻሻያ አለማድረጉ አግባብነት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ባለስልጣኑ ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝርን ስለመዘጋጀቱና መዘርዝሩንም በየጊዜው መከለሱን በተመለከተ፣</u>

77. ባለስልጣኑ ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝርን ሊያዘጋጅ፣ መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በየዓይነታቸው ሊመድብ፣ መዘርዝሩንም በየጊዜው ሊከልስ ይገባል፡፡

78. አዋጅ ቁጥር 728/2004 እና የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች መመሪያ ቁ.1/2006ዓ.ም አንቀፅ 16/ሀ መሠረት ባለስልጣኑ ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝርን ሊያዘጋጅ፣ መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በየዓይነታቸው ሊመድብ፣ መዘርዝሩንም በየጊዜው ሊከልስ ይገባል ቢልም ባለስልጣኑ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ይህን አላከናወነም፣

79. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች በሰጡት መግለጫ ላይ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች መዘርዝር ዝግጅትን በተመለከተ ባለስልጣኑ ከተቋቋመበት ወቅት ጀምሮ ተጨማሪ የመኖ ንጥረ ነገር ወደ ሀገር የማስገቢያ ፈቃድ ሲሰጥና እየገባም ያለ ሲሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝር ካሁን ቀደም በሀገሪቱ ያልተዘጋጀ መሆኑና በአንድ ታዳጊ ሀገር በውስጥ ባለሙያ አቅም ብቻ የሚከናወን አለመሆኑን፣ እንዲሁም አብዛኛው የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች ከውጭ የሚገቡ በመሆናቸው እስካሁን ወደ ሀገር በማስገባትና በመጠቀም ተጠቃሽ ምርቶች በእንስሳት ሀብት ልማት ተዋንዮች ዘንድ የሚኖራቸውን ተቀባይነት መከታተልና ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ እና ወደ ሀገር በማስገባት፣በማሰራጨትና በመጠቀም ላይ ያስከተለው ጉዳት ወይም የጎንዮሽ ተፅዕኖ አለመኖሩ በተጨማሪም ተጠቃሚዎች ስለምርቱ ባህሪይ፣በእንስሳት ምርታማነት ላይ ያስገኘው ውጤት እንዲሁም ያስከተለው ችግር ካለ ዝርዝር ቅኝት በማካሄድ ውጤት ማፈላለግ የሚገባ መሆኑን እንዲሁም በላብራቶሪ ፍተሻ የታገዘ ሙያዊ ትንታኔና ተፅዕኖ ደሰሳ ላይ የተመሰረተ ውጤት ለመጨበጥ ተጨማሪ ዕውቀት አስፈላጊ በመሆኑ ምክንያት መዘርዝሩ ሳይዘጋጅ የቆየ ቢሆንም ሀገራዊ መኖ መሰረታዊ ሀብት ለማዘጋጀት ታቅዶ ስራው በሂደት ላይ እንደሆነና ለወደፊት እንደሚያዘጋጁ የእንስሳት መኖ ጥራት ደረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ ዳይሮክቶሬት ዳይሮክተር ገልፀዋል፡፡

80. እንዲሁም ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒት መዘርዝርን በተመለከተ በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የእንስሳት በሽታ ስርጭት፣ያለውን የጤና መሰረተ ልማት ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሀገሪቱ አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶች ዝርዝር የያዘ ሰነድ መሆኑን የእንስሳት መድኃኒት መዘርዝር ከዚህ በፊት በነበረው ተቆጣጣሪ አካል ተዘጋጅቶ እንደነበረ መዘርዝሩ ክፍተቶች ቢኖሩትም ማሰራት ስለሚችል አሁን ባለስልጣኑ እየተጠቀመበት እንደሚገኝ ነገር ግን መዘርዝሩ ከተዘጋጀ ረዥም ጊዜ በመሆኑ መከለስ እንዳለበት በባለስልጣኑ እና በተገልጋዮች ታምኖ ከተቋቋመበት ግዜ ጀምሮ እንቅስቃሴ ሲደረግ መቆየቱን ሆኖም ግን ለስራው ሚያስፈልገው በጀትና የሰው ሀይል ከግምት ውስት በማስገባት በዳይሮክቶሬት ደረጃ መስራትና መከለስ አስቸጋሪ በመሆኑ የተለያዩ በዘርፉ የተሰማሩ ለጋሽ ድርጅቶችን ፕሮፖዛል ለመቅረፅ ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም አውንታዊ ምላሽ አለመገኘቱን እና በ2009ዓ.ም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለመከለስ በዕቅድ ተይዞ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ እንደሚገኙ የእንስሳት መድኃኒት ጥራት ደረጃ ምዝገባና ፍቃድ ዳይሬክቶሬት ገልፀዋል፡፡

81. ይህንን በተመለከተ መዘርዝሩን ለመከለስ ገንዘብ ለማፈላለግ ፕሮፖዛል ቀርፆ ILRI, FAO እንዲሁም ለሌሎች ተሰጥቷቸው ሊያግዙ እንዳልቻሉ፣ ተፅዕኖም እንዳልፈጠረባቸው ሆኖም ግን በ2009 በወርልድ ባንክ እንደሚያዝ ካልሆነም በባለስልጣኑ እንደሚሰራ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ተገልጿል፡፡

## 2.2. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒት፡ መኖ ፣ ሕክምና መሣሪያዎችና መገልገያዎች ዙሪያ ከሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ተዋህዶ ለመስራት እንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን ብቃት ባለው መልኩ ለማስተዳደር የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤

<u>ባለስልጣኑ በዘርፉ ለተሰማሩ ተቋማት ስልጠና መስጠቱን በተመለከተ፤</u>

82. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ አግባብ ላላቸው አካላት ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

83. በኦዲቱ ወቅት ከታዩት 12 የመድኃኒት አስመጪ፣ 6 የጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች እና 3 የመድኃኒት አምራች ድርጅቶች ውስጥ ለ7 መድኃኒት አስመጪ እና ለ3ቱም የመድኃኒት አምራች ድርጅቶች እንዲሁም በመድኃኒት አያያዝና አከመቻቸት እንዲሁም አጓጓዝ ዙሪያ ስልጠና እንዳልተሰጣቸው እንዲሁም በናሙና ለታዩት ለ 5 መኖ አምራቾች እና ለ2 የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጪና ላኪ ድርጅቶች ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝ አጠቃቀም ዙሪያ ስልጠና ሰጥቷቸው እንደማያውቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

84. ይህም በመሆኑ ድርጅቶቹ የአሰራር ክፍተቶቻቸውን እና ደካማ ጎናቸውን ለመለየትና ለማስተካከል አለመቻላቸውን እንዲሁም አንዳንድ ድርጅቶች ደግሞ የስልጠናውን ጥቅሙንና ጉዳቱንም ባለማወቃቸው በድርጅታቸው ላይ ያስከተለውን ክፍተት ለመግለፅ እንደሚቸገሩ የስራ ኃላፊዎቹ የገለፁ ሲሆን፣ በተጨማሪም ባለስልጣኑ የአዳማ ሞጆና የቃሊት እና የካርጎ ቅ/መ/ቤት ሰራተኞች ስራቸውን በተገቢው መልኩ ለመስራት የሚያስችል ምንም ዓይነት ስልጠና በባለስልጣኑ ተሰቷቸው እንደማያውቅና ያለባቸውን የአቅም ክፍተት በመለየት ለባለስልጣኑ በየጊዜው የሚያሳውቁ ቢሆንም እስካሁን ምላሽ አለማግኘታቸውን በቀረበላቸው ቃለመጠይቅና ባቀረቡት ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

85. ባለስልጣኑ በ2007 በጀት ዓመት 2 የአቅምና ክህሎት ክፍተት መለየትና ተገቢውን የማሻሻያ ምክረ ሃሳብ ለመስጠት አቅዶ አለመከናወኑ እንዲሁም በእንስሳት መድኃኒት አጠቃቀምና አያያዝ ላይ 16 የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ለማዘጋጀት አቅዶ ስለመከናወኑ ያልተገለፀ መሆኑ በተጨማሪም ለባለሙያዎች አቅም ግንባታና የመድኃኒት ጥራት ለማረጋገጥ በ2008 በጀት ዓመት ፕሮጀክት ለመቅረፅ የታቀደ ቢሆንም አለመከናወኑ ታውቋል፡፡

86. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ አግባብ ላላቸው አካላት ስልጠና መስጠትን

በተመለከተ በመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ለክልል አካላት ስልጠና የሰጠ ቢሆንም ለአስመጭዎች እና ለጅምላ አከፋፋዮች በአረንጓዴው መመሪያ ዙሪያ ውይይት ከማድረግ ውጭ ከአቅም አንፃር እና ባለስልጣኑም አዲስ ከመሆኑ የተነሳ በመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ስልጠና እንዳልሰጡአቸው ድርጅቶቹም ነባር ስለሆኑ ባለስልጣኑ ወደዚህ ሂደት እንዳልገባ ሆኖም ግን በባለስልጣኑም ክፍተቶች እንዳሉበት እና ትኩረትም እንዳልተሰጣቸው፡እንዲሁም የመኖ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ ግን ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ላገኙት ድርጅቶች በሙሉ የስልጠና ደብዳቤ እንደተላከ ሆኖም ግን ስልጠናው ላይ ካልተገኙ ምንም ማድረግ እንደማይችሉ፤ ለኢትዮ ፊድ፣ ለአቃቂ፣ ለቃሊቲ እና ለአዲስ አለም መኖ ማምረቻ ድርጅቶችና ለክልል አካላትና ለቢራ ፋብሪካዎች የተላከው የስልጠና ጥሪ ደብዳቤውም ለኦዲት ቡድኑ ቀርቦ እንደታየ ገልፀዋል፡፡

87. ይሁንእንጂ የኦዲት ቡድኑ ከባለስልጣኑ ባገኘው ማስረጃ መሰረት በመድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ባለስልጣኑ ለክልል ግብርና ቢሮዎች ባለሙያ ስልጠና እንደተሰጠ እንዲሁም በፋጎሎ አያያዝ ዙሪያ ለተወሰኑ ድርጅቶች ማለትም ከስድስት ለማይበልጡ ድርጅቶች ስልጠኛ እንደተሰጠ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፤በኦዲቱ ወቅት ግን በናሙና ከታዩት ደርጅቶች ውስጥ ለማንም ድርጅት በዚህ ዙሪያ ስልጠና ስለመሰጠቱ ከድርጅቶቹም ሆነ ከባለስልጣኑ የቀረበው በቂ ማስረጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

## <u>ባለስልጣኑ በዘርፉ ከተሰማሩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን በተመለከተ፣</u>

88. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

89. በኦዲቱ ወቅት በዚህ ዙሪያ በአካል ከታዩት 40 ድርጅቶች ውስጥ ባለስልጣኑ ከ6ቱ ጋር ቅንጅታዊ አሰራር የሌለው ሲሆን ከ 34ቱ ጋር ደግሞ የተጠናከረ እና በስምምነት ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቅንጅታዊ አሰራር ባይሆንም ከቅድመ ፈቃድ አሰጣጥና ዕድሳት ኢንስፔክሽን እና ስልጠና ውጭ በጋራ የማይሰሩ መሆኑን፣

90. ይህም በመሆኑ ቋሚ የሆነ የውይይት መድረክ እንዳይኖር ማድረጉን፣ ባለስልጣኑ ዕቅድ ሲያቅድ ድርጅቶች እንዲያውቁት አለማድረጉንና አሰራራቸውን ሊያጎለብትላቸው እንዲሁም ድክመታቸውን ሊያሳውቃቸው እንዳላስቻላቸው፣ ድርጅታቸውን ለማስተዋወቅና የገበያ ዕድል ለማግኘት እንደተቸገሩ፣ ባለስልጣኑ በመኖ አምራችና በጥሬ እቃ አቅራቢ ድርጀቶች ላይ ስራውን መስራት አለመቻሉ፣ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ በመድኃኒት ደረጃ ዝግጅት ዙሪያ የእንስሳት መድኃኒት ደረጃን በተመለከተ ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር በቅንጅት

እየተሰራ እንዳልሆነ፣ የሚፈልጉትን ጉዳይ በወቅቱና በፍጥነት ሊፈፀምላቸው እንዳልቻለ፣ ከዚህም በተጨማሪ የእንስሳት መኖ/ፋጉሎ/ የሚያመርቱ የዘይት መጭመቂያ ያላቸው ድርጅቶችን በተመለከተ ከገበያ በመውጣት ላይ እንደሆኑና ወደፊት ለመኖ ግብዓት የሚያገለግል የፋጉሎ ምርት እጥረት ሊያጋጥም እንደሚችል እንዲሁም ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር የጋራ የመግባቢያ ሰነድ የሌላቸው መሆኑና በሀገር የውጭ ምንዛሬ ላይ እና በዘይት ጨማቂ ድርጅቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው የገለጹ መሆኑ፣

91. በተጨማሪም ባለስልጣኑ ኃላፊነቶችን በአውደ ጥናት የማስተዋወቅና ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ጋር ግንኙነትና የቅንጅት አሰራርን መስርቶ ተግባራዊ ለማድረግ አቅዶ አለመከናወኑ እንዲሁም በ2007 በጀት ዓመት በባለስልጣኑ በተለያዩ የስራ ክፍሎች መካከል የስራ ትስስር እና ቅንጅታዊ አሰራር የላላ መሆኑ ታውቋል፡፡

92. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መስራትን በተመለከተ መኖን በሚመለከት ባለስልጣኑ ከዓለም እና ከሀገር አቀፍ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ለመስራት ሙከራ እንዳደረገ ሆኖም ግን ከአንዳንድ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጋር ምንም ዓይነት ቅንጅታዊ ስራ እንደሌላቸው፤ ለምሳሌ፡- ከኢትዮጵያ ምግብ ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣንና ከንግድ ሚኒስቴር እንዲሁም ከኢንዱስትሪ ሚ/ር ጋር በምንም ዓይነት ሁኔታ በቅንጅት መስራት እንዳልቻሉ ከባለፍቃዶች ጋር ግን በተወሰነ መልኩ በቅንጅት እንደሚሰሩ፡ነገር ግን የማይመለከታቸው አካላት የባለስልጣኑን ስራዎች ጣልቃ በመግባት በመስራት ላይ እንደሚገኙ፤ ለምሳሌ፡- ኢንደስትሪ ሚኒስቴር ፋጉሎ ወደ ውጭ ሃገር እንዲላክ እያደረገ መሆኑን በተጨማሪም በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር በኩል የቁም እንስሳት ወደ ውጭ በሚላክበት ጊዜ አብሮ የሚወጣ የእንስሳት መኖ የሚላክበት ሁኔታ እንዳለ እና የባለስልጣኑ የኢንስፔክሽንና የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተቋማት ጥራትና ደረጃ ፣ ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬቶች በቅንጅት እንደማይሰሩና የመናበብ ችግር እንዳለባቸው የገለፁ ሲሆን፤ መድኃኒትን በተመለከተ ግን የእንስሳት መድኃኒት አስመጭዎች፣ አምራቾች እና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶችን አሳትፎ በመመሪያ ላይ ማውጣት ራሱ ቅንጅታዊ አሰራር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

**ባለስልጣኑ በሀገር ውስጥ የተመረተም ሆነ ከውጭ ሀገር የገባ የእንስሳት መድኃኒቶች ላይ የጥራትና የፈዋሽነት ግምገማ በማካሄድ ስራ ላይ እንዲውል ማድረጉን በተመለከተ፣**

93. ባለስልጣኑ በሀገር ውስጥ የተመረተም ሆነ ከውጭ ሀገር የገባ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት በወቅቱ ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተገምግሞ ወይም ተረጋግጦ ከተመዘገበ በኃላ ጥቅም ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይገባል፡፡

94. አዋጅ ቁጥር 728/2004ዓ.ም አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 ባለስልጣኑ በሀገር ውስጥ የተመረተም ሆነ ከውጭ ሀገር የገባ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተገምግሞ ወይም ተረጋግጦ ከተመዘገበ በኃላ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ እንዳለበት የሚገልጽ ቢሆንም በባለስልጣኑ በፊት በዳግም ምዝገባ ሂደት ላይ ሆነው ላብራቶሪ ናሙና ላስገቡት የመድኃኒት አስመጪዎች የግዥ ትዕዛዝ ሲፈቀድ እንደቆየ ሆኖም ግን በአሁን ወቅት የዳግም ምዝገባ ሂደት አድርገው የላብራቶሪ ናሙና ለማስገባት ዝግጅት ላይ እያሉ የምግብ፣መድኃኒትና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን ናሙና መቀበል በማቆሙና የባለስልጣኑም ላብራቶሪ ስራ ባለመጀመሩ መድኃኒቶቹ በዳግም ምዝገባ ሂደት ላይ ያሉ ከሆነና ከዚህም ቀደም ወደ ሀገር ውስጥ ይገቡ ስለነበር የተለየ ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ ታውቆ ካለው የገበያ እጥረት አኳያ እስከ ቀጣዩ 6 ወራት ድረስ የግዥ ፈቃድ ትዕዛዝ እንዲሰጣቸው በማለት በየካቲት 22/2008 ዓ.ም. በተያዘ ቃለ ጉባኤ የተወሰነ ቢሆንም ይሄ ጉዳይ አዲቱ እስከተጠነቀቀበት ጊዜ ድረስ እንደቀጠለ ታውቋል፡፡

95. ከዚህም የተነሳ ባለስልጣኑ ለ21 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች የባለስልጣን መ/ቤቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ በየካቲት 29/2008 ባካሄደው የስብሰባ ውሳኔ መሰረት የእንስሳት መድኃኒት የጥራት ምርመራ ትኩረት አቅጣጫ ለውጥ በመደረጉ ምክንያት በቀድሞ ጊዜ በተደረገው ሰነድ ግምገማ እና የመልካም አመራረት ተግባር ውጤት መነሻነት ጊዜያዊ እና አዲስ የእንስሳት መድኃኒት ምዝገባ ሴርቲፊኬት መሰጠቱን ሆኖም ግን ባለስልጣኑ ለወደፊት በማንኛውም ወቅት በኮንሳይመንትና በድህረ ገበያ የጥራት ምርመራ ውጤት መሰረት ዋናውን የገበያ ፈቃድ እስከሚሰጥ ድረስ የእንስሳት መድኃኒቱን ማስመጣት እንዲችሉ በማለት ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ በላብራቶሪ ሳይገመገምና ሳይረጋገጥ ለ280 ዓይነት መድኃኒቶች ፈቃድ የሰጣቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

96. እንዲሁም በየካቲት/2008 በተያዘ ቃለ ጉባኤ የሰርተፍኬት ማብቂያ ጊዜን /CPP validity date/ በተመለከተ ሰነድ በሚገመገምበት ጊዜ የሴርትፍኬቱ ማብቂያ ጊዜ የቀረበ ከሆነ ባለፈቃዶቹ በአዲስ እንዲያስገቡ መደረግ እንዳለበት ሆኖም ግን በላብራቶሪ ምርመራ መዘግየት ምክንያት ከሆነ በባለስልጣኑ የተከሰተ ችግር በመሆኑ በጣም የቀረበና ስራውን

የማያስተጓጉል እስካልሆነ ድረስ ጥንቃቄ ተደርጎ ቢታለፍ በሚለው ሀሳብ ተስማምተው የወሰነ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በኦዲቱ ወቅት በአካል የታዩት የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት ውስጥ ያለምንም ላብራቶሪ ፍተሻ ድርጅቶቹ በጠየቁት መሰረት በባለስልጣኑ ለመድኃኒቶቹ ጊዜያዊ እንስሳት መድኃኒት ሰርትፍኬት በመስጠት መድኃኒቶቹ ወደ ሀገር እንዲገቡና እንዲሰራጩ ተፈቀደላቸው ድርጅቶች ዝርዝር በሠንጠረዥ 2 በአባሪ 6 ተያይዟል፡፡

97. እንዲሁም ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት ሃያ አንድ(21) ዓይነት የእንስሳት መድኃኒቶችን/ክትባቶችን/ በማምረት እያከፋፈለ ሲሆን የሚያመርታቸውን የእንስሳት ክትባቶች የኦዲት ማስረጃው እስከተሰባሰበበት ጊዜ ድረስ በባለስልጣኑ በማስገምገም ምዝገባ ያላደረገ ሲሆን ነገር ግን 5 ዓይነት መድኃኒቶችን /ክትባቶችን/ ለማስመዝገብ በሂደት ላይ መሆናቸውን በተጨማሪም አለማ ፋርም የእንስሳት ክትባቶችን /መድኃኒቶችን/ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ከውጪ ሀገር እያስመጣ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ከአንድ መድኃኒት በስተቀር በባለስልጣኑ በኩል ተገምግመው እንዳልተመዘገቡ ከዚህም ሌላ ባለስልጣኑ ለዳግም ምዝገባ የተሰጠው ሰርተፍኬት ከ5 ወር እስከ 2 ዓመት ከ5 ወር ጊዜ ድረስ በመዘግየት የዕድሳት ጊዜው አልፎ ጊዜያዊ ሰርተፍኬት የተሰጣቸው ሲሆን ድርጅቶቹም በዚሁ ጊዜ ሰርተፍኬቱን ሲጠቀሙበት እንደነበረ ከድርጅቶቹ በተገኘው ማስረጃ የታወቀ መሆኑ፣

98. ይህም በመሆኑና የላብራቶሪ አገልግሎት ባለመጀመሩም ድርጅቶቹ የሚያስመጧቸው መድኃኒቶች ናሙና የመጠቀሚያ ጊዜው እንደሚያልፍና ከፍተኛ መስተጓጎል እንደፈጠረባቸው ፣ አዳዲስ መድኃኒቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት እና ለማስመዝገብ አለመቻላውን እንዲሁም የተመዘገቡትንም መድኃኒቶች ለማስገባት የመዘግየት እና መጓተት ሁኔታ እንደፈጠረባቸው በተጨማሪም ባለስልጣኑ ለመድኃኒት ምዝገባ የናሙና ምርመራ ባለፈ የአንድን መድኃኒት ናሙና በየጊዜው እየወሰደ መመርመርና ጥራታቸውን ጠብቀው በስርጭት ላይ መሆናቸውን በማረጋገጥ የመድኃኒቶችን ፈዋሽነትና ጥራት በተጨባጭ መፈተሽ እንድሚገባው የስራ ኃላፊዎቹ የገለፁ መሆኑ፣

99. በተመሳሳይ መልኩ በባለስልጣኑ አዋጅ ቁጥር 728/2004ዓ.ም አንቀፅ 26/3 ላይ ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ሳይኖረው በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ስራ ላይ ከተሰማራ እንዲሁም ማንኛውም በእንስሳት መድኃኒት ጅምላ ወይም ችርቻሮ ንግድ የተሰማራ ሰው የብቃተ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካልተሰጠው ሰው መድኃኒት ከገዛ በተጨማሪም በአዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ 4/1 ላይ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተገምግሞ ወይም ተረጋግጦ በባለስልጣኑ ሳይመዘገብ በሀገር ውስጥ ተመርቶም ሆነ ከውጭ ሀገር ገብቶ ጥቅም ላይ ከዋለ በወንጀል እንደሚያስቀጣ ቢታወቅም የመድሃኒቱ ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ ሳይገመገም ወይም ሳይረጋገጥ ካከፋፈሉ ድርጅቶች ውስጥ አንደኛ

ዋፍ የተባለ የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ድርጅት የጅምላ አከፋፋይነት የብቃት ማረጋገጫ ከባለስስጣኑ ሳይኖረው አሴቶን የተባለ ኬሚካላዊ ይዘት ያለው የእንስሳት መድኃኒት1000ሊትር 129000 ብር የሚያወጣ ጥራቱ፣ደህንነቱና ፈዋሽነቱ በባለልጣን መ/ቤቱ ሳይገመገምና ሳይረጋገጥ እና ለመድኃኒቱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሳይሰጠው እንዲሁም በመድኃኒቱ ላይ የላብራቶሪ ፍተሻ ሳይደረግበት እና መድኃኒቱ ለእንስሳት ህክምና አገልግሎት እንዲውል አስፈላጊው ግምገማ ያልተደረገና ያልተመዘገበ መድኃኒት ሆኖ ሳለ ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለእንሰስሳትና ጤና አገልግሎት ቢሮ በጨረታ በመወዳደር በህገ ወጥ መንገድ በገበያ ላይ እንዲውል መደረጉ/ ሽጦ/ የተገኘ መሆኑ በግንቦት 2008 ከኢንስፔክሽን ቡድን በተገኘው መረጃ መሰረት ባለስልጣኑ ለአራዳ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በፃፈው ደብዳቤ የታወቀ ቢሆንም ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት ዋፍ ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የሌለው ሲሆን በዚህም ዙሪያ መድኃኒቱን ያስመዘገበ አምራችም ሆነ አስመጪ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

100. በተጨማሪም ባለስልጣኑ ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርናና ገጠር ቢሮ ጥቅም ላይ እንዳያውለው የከለከለበት ማስረጃ በባለሰልጣኑ ያልተገኘ ሲሆን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ጉዳዩን ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከመወሰድ ውጭ ባለስልጣኑ ለዋፍ ይሄንን መድኃኒት ለሸጠለት ታፈለን ኢንዱስትሪና ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ላይም ሆነ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርናና ገጠር ቢሮ እንዲሁም በህገ ወጥ መንገድ መድኃኒቱን በሸጠው ድርጅቶች ላይ ተከታትሎ የወሰደው እርምጃ አለመኖሩ፣

101. በተጨማሪም ኢስት አፍሪካ ፋርማሲውቲካል ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተባለ የመድኃኒት አምራች የንግድ ድርጅት ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተገምግሞ በባለስልጣኑ ያልተመዘገበ ብዛቱ1483 ሳጥን ቴሊን የተባለ የእንስሳት መድኃኒት አምርቶ ለሶስት ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች (ለማርቆስ ኃ/የተ/ የግ/ማ፣ ለአ.ል.ፒ.ስ እና ለዳምቲ ቬቲት ፋርማ ትሬዲንግ) እንዲከፋፈል የተደረገ ቢሆንም ኢስት አፍሪካ ፋርማሲውቲካል ኃ/የተ/የግ/ማህበር በስራ ብዛት ምክንያት ጥቂት መድኃኒቶችን ለአሁኑ ባለስልጣን ሳያሳውቁ እንዳዘገዩና የተከሰቱት ክስተቶች ወደ ፍትህ አካል በምርመራ በመታየት ላይ መሆኑንና በዚሁ መቀጠሉ ድርጅታቸውን የሚጎዳ ሆኖ በማግኘታቸው የተጀመረው ክስ እንዲሰረዝላቸው እና ክሱ በአስተዳደራዊ ጉዳይ እንዲታይልን ብለው በመጠየቃቸው ብቻ የይቅርታ ደብዳቤ ለባለስልጣኑ አስገብቷል በማለት ባለስልጣኑ ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወስድ ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑ ፣

102. በተመሳሳይ ሁኔታ አዳሚ ቱሉ ፀረ ተባይ ማዘጋጃ ድርጅት ዲያዝኖን የሚባል መድኃኒት በባለስልጣን መ/ቤቱ የማስመዝገብ ሂደት ላይ እንደሆነ እንዲሁም ቬንታዝኖን ደግሞ ለዳግም ምዝገባ ሂደት ላይ እንደሆነ በኦዲቱ ወቅት ቢታወቅም ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ ሳይገመገም ወይም ሳይረጋገጥ ለእንስሳት ለውጭ ጥገኛ ማከሚያ አገልግሎት የሚውሉ

መድኃኒቶች ከባለስልጣኑ ከተዘጋጀው ሪፖርት ከሁለት ዓመት በፊት በቤንሻንጉል አከባቢ 50 ከብቶችን፣ በኦሮሚያ አከባቢ ደግሞ 36 ከብቶችን የገደለ መሆኑን ከባለስልጣኑ ከተገኘው የኢንስፔክሽን ሪፖርት እና ከአዳሚ ቱሉ በተገኘው ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

103. እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒት ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ ሳይገመገም ወይም ሳይረጋገጥ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ ተገኝተው ካለምንም እርምጃ ከተለቀቀላቸው ድርጅቶች ውስጥ

ሀ) ራንግ ኢንጅነሪንግ ፒ.ኤል.ሲ. በተባለ አስመጪ ራንግ እስፕሬይ የተባለ ለእንስሳት መድኃኒት አገልግሎት የሚውል መድኃኒት በሞጆ ደረቅ ወደብ በኩል ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባቱ አዳማ/ሞጆ ደረቅ ወደብ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በፍተሻ ወቅት ማግኘታቸውን በባለስልጣኑ አዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ12/1 መሰረት ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ለባለስልጣኑ በደብዳቤ ቢያሳውቁም ባለስልጣኑ ምንም ዓይነት እርምጃ ያልወሰደባቸው መሆኑ፣

ለ) ባለስልጣኑ ፓን አፍሪካ ቬተርነሪ ቫክስን ሴንተር የተባለ ድርጅት የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ክትባቶች፣ ሪኤጀንቶች፣ የህክምና መሳሪያዎችን ደብረዘይት በሚገኙ የጥራት ቁጥጥር የሚሰራ ቢሆንም ከተለያዩ ሀገራት የሚያስገባቸውን ክትባቶችና ሪኤጀንቶች ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡበት ጊዜ በቁጥጥር ጣቢያ በሚገኙ ባለሙያዎች ተከፍቶ መፈተሽ እንደሌለበትና እንደማንኛውም የዲፕሎማቲክ ዕቃ የእንስሳት መድኃኒት ደህንነቱ፣ ፈዋሽነቱና ጥራቱ ሳይገመገም ወይም ሳይፈተሹ እንዲገቡ በባለሰስልጣኑ የተደረገ መሆኑ፣

ሐ) እንዲሁም ኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ ከውጭ ሀገር የገባ ማንኛውም የእንስሳት የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተገምግሞ ወይም ተረጋግጦ ከተመዘገበ በኃላ ጥቅም ላይ እንዲውል እያደረገ አለመሆኑ፣

መ) በተጨማሪም በባለስልጣኑ በ2007 በጀት ዓመት በተለያዩ ዘዴዎች የእንስሳት መድኃኒት ጥራት የሚረጋገጥ አገልግሎት 100% ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ አፈፃፀሙ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ያልተገለፀ መሆኑ

104. የባለስልጣኑ አዋጅ ቁጥር 728/2004 ዓ.ም አንቀፅ 4 እንዳለ ሆኖ ባለስልጣኑ በአስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት ማለትም ከፍተኛ የእንስሳት ፍልሰት የሚያስከትሉ የተፈጥሮ አደጋዎች እንደ ድርቅ፣ ጎርፍና የመሬት ነውጥ የመሳሰሉት ወይም ባዕድ የእንስሳት በሽታ ወረርሽኝ ክስተት ወይም ለእንስሳት ጤና ምርምር አገልግሎትና ለቅድመ ምዝገባ የሙከራ አገልግሎት እንዲውል ሊፈቅድ ይችላል ቢልም በባለስልጣኑ ከ 6 በላይ የሚሆኑ የዶሮ አርቢ ድርጅቶች ከ2006ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን የዶሮ መድኃኒቶችን በማስገባት ላይ ቢሆኑም

ሀ/ በአዋጅ መሰረት ወረርሽኝ ተከስቶ ሳይሆን በ2006 ዓ.ም የዶሮ አርቢዎች መድኃኒት በማስገባት ላይ እያሉ በመጋቢት/2006ዓ.ም. በባለስልጣኑ በህዝብ ክንፍ በተደረገው

ውይይት ላይ የዶሮ እርባታ ድርጅቶች የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት የአስመጪነት ፈቃድ በማውጣት ክትባቶችን በማስመዝገብ በዘላቂነት ማስመጣት እንደሚችሉ ሆኖም ግን አቅም ያላቸው ድርጅቶች ለራሳቸው ፍጆታ ብቻ ጥራት ያለው ክትባት ከሚመረትበት ለማስመጣት የግዥ ፈቃድ ሲጠይቁ እንዲፈቀድላቸው ያመጡትም ክትባት ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በፓንቫክ/AU-PANVAC/ የክትባቱ ጥራት ፈዋሽነትና ደህንነት እየተረጋገጠ ኃላፊነት በተሞለበት ለግል ፍጆታቸው እንዲያውሉ በሚል የጋራ መግባቢያ ላይ የደረሱ መሆኑ፣

ለ/ በመስከረም/2007 ዓ.ም በማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ የዶሮ አርቢ ድርጅቶች ለዶሮ ክትባት የሚያስፈልገውን መድኃኒትና የተለያዩ የዶሮ መድኃኒቶችን ከውጭ ሀገር ገዝተው እንዲጠቀሙ ለማድረግ በማኔጅመንቱ የተለያዩ ተያያዥ ጥያቄዎች ተነስተው የነበሩ ቢሆንም የዶሮ አርቢዎች ደቡብ አፍሪካ ከሚገኘው ድርጅት ለክትባት የሚውለውን መድኃኒት በቀጥታ እንዲያስመጡ ቢፈቀድ እንዲሁም ፈረንሳይ የሚገኘው ላብሮቬት የተባለው ድርጅት ከዚህ ድርጅት ወኪል ሆነው ለማምጣት የተመዘገቡ ድርጅቶች ፈቃድ እስኪሰጣቸው ድረስ የዶሮ አርቢዎቹ የተለያዩ የዶሮ መድኃኒቶችን ከዚህ ድርጅት በቀጥታ እንዲያስመጡ ቢፈቀድላቸው በሚል ስምምነት የተደረሰበት ቢሆንም ነገር ግን የሚያስመጡትን ለንግድ ስራ እንዳያውሉት፣ ምን ያህል ዶሮዎች እንደዋላቸውና ምን ያህል መድኃኒት ለዶሮ ክትባት እነደሚያስፈልግ በማጣራት የሚበቃቸውን ብቻ እንዲያስመጡ ሆኖም ግን ያስመጡትን በገበያ ላይ ሲሸጡ ቢገኙ ሊደርስባቸው የሚችለውን ቅጣት ከወዲሁ አውቀው ውል ስምምነት እንዲፈፅሙ ቢደረግ የሚለው ሃሳብ ቀርቦ እስከ 30/4/2007ዓ.ም. ድረስ ብቻ ተፈፃሚ እንዲሆን በማለት የማኔጅመንት አባላት የወሰኑ ቢሆንም የፈፀሙት ስምምነት እና ያሏቸውን የዶሮ መጠን ያሳወቁበት ማስረጃ በባለስልጣኑ ያልተገኘ መሆኑ ፡፡

ሐ/ በተጨማሪም በ29/11/2007ዓ.ም ለራስ ፍጆታ ብቻ የሚውል የእንስሳት መደኃኒት ግዥ የሚካሄደው እንደዶሮ በሽታዎች ያሉ በወረርሽኝ መልክ ለሚከሰቱ የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከል የሚውሉ በመሆናቸውና ተግባሩ በአዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ4/2 ላይ ሊወድቅ ስለሚችል በማለት ከዚህ በፊት የቀረቡትን የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ ጨምሮ ለወደፊትም የሚቀርቡትን ተመሳሳይ ጥያቄዎች በመድኃኒት ምዝገባና ፍቃድ ዳይሬክቶሬት አማካኝነት አስፈላጊነታቸው እየታየ በአግባቡ እንዲስተናገዱ በኮሚቴው የተወሰነ ሲሆን እነዚህ የዶሮ አርቢዎች በአዋጁ አንቀፅ 4/2 ሳይሆን ከ2006-2009 በማንኛውም ጊዜ በማኔጅመንት ቃለ- ጉባኤ በተፈቀደ ጊዜ እና ከዛ ውጭ ባልተፈቀደ ጊዜ ዶሮ አርቢዎቹ መድኃኒት እያስገቡ የነበረ መሆኑ፣ ከዚህም በተጨማሪ ለሁሉም ፋርሞች/የዶሮ አርቢዎች/ በእኩል የማይፈቀድላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

105. እንዲሁም ኤልፎራ አግሮኢንዱስትሪ በቀድሞ ጊዜ የተለያዩ መድኃኒቶችን እንዲያስገባ ሲፈቀድለት የነበረ ቢሆንም በ2008 ዓ.ም ነሐሴ ወር አከባቢ በደብረ ዘይት አከባቢ ኢንፌክሽየስ ቢሮንካይት IB(Infectious Bronchites) የሚባል ወረርሽኝ በሽታ መታየቱ እና ከ8 ዶሮዎች 6ቱ ላይ መገኘቱ በሐምሌ/2008 ዓ.ም በብሄራዊ እንስሳት ጤና ኢንስትቲዩት/NVI/ ላብራቶሪ ውጤት ታውቆ እንደነበር ይህም በሽታ በአየር ስለሚተላለፍ እና ክትባቱ በአንድ እርባታ ማለትም አለማ ፋርም በሚባል ድርጅት እንደተከሰተና ፋርሙ ይሄንን ክትባት(live vaccine) ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባቱ በሽታው በአየር ተሰራጭቷል በማለት ኤልፎራ በዶሮዎቹ ላይ IB Digonosis ለማድረግ ክትባቱን ለማስገባት ባስመረመረው ማስረጃ መሰረት ባለስልጣኑን ፈቃድ ቢጠይቅም በወቅቱ ምላሽ ባለመስጠቱ ካሉት ዶሮዎች ወደ 40% የሚሆኑ ያለቁበትና እያንዳንዱ ዶሮ ዋጋው 100 ብር እንደሆነና ወደ 160,000 የሚሆኑ ዶሮዎች እንዳለቁባቸው ይህ ደግሞ ለሀገርቱ እና ለድርጅቱ የኢኮኖሚ ቀውስ እንደሚያስከትል በሰጡት መግለጫ እና በ10/10/2008 ለባለስልጣኑ በፃፉት ደብዳቤ ቁጥር GM-ADF 2016-758ና ለእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር በ11/12/08 በደብዳቤ ቁጥር ደምስ/ዳ/ግሂ/08/8 ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በግብርና ሚ/ር መ/ቤቱ ለባለስልጣኑ ደብዳቤ (ቁጥር 15/እና/1.1/1/18 በቀን 30/12/2008 )ከተፃፈ በኃላ ባለስልጣኑ ኤልፎራ በአዲስ ቬት የመድኃኒት አስመጪ በኩል እንዲያስገባ ጥቅምት/2009 አከባቢ የተፈቀደለት መሆኑ፣ ሆኖም ግን ለሌሎችም የዶሮ አርቢ ድርጅቶች እንዲያስገቡ በወቅቱ የተፈቀደላቸው መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

106. የመድኃኒት ጥራት፣ ደህንነት እና ፈዋሽነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ከአውሮፓ ወይም ከሌሎች ተመሳሳይ ሀገሮች የኤስ አር ኤ/SRA/ Stringent regulatory Authority- መድኃኒት እያስመረቱ ወደ ሀገራችን ለማስገባት የሰነድ ግምገማ የተደረገላቸው በአሁን ሰዓት የላብረቶሪ ምርመራ ለማካሄድ ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ ምክንያት መድኃኒቶቹን ማስገባት አለመቻላቸው እና ለዚሁ መፍትሄ መደረግ አለበት በማለት በየካቲት/2008 ዓ .ም በቃለ ጉባኤ ተይዞ ሁኔታው ታይቶ የላብራቶሪው ምርመራ መደረግ እንዳለበት እና መድኃኒቶቹ መግባት እንዳለባቸው ሁኔታዎች መመቻቸት እንዳለባቸው ሀሳብ ቀርቦ የነበረ ቢሆንም አውሮፓ ሀገራት በአሁን ሰዓት ሆርሞንና አንቲባዮትክ መስጠት እየተው እንደሚገኙ እንዳንድ መድኃኒቶችም እንደ አፍሪካ ሀገር ላሉ ሀገራት ብቻ የሚመረቱ መሆናቸውንና አንዳንድ በሽታዎች እዛ ስለማይገኙ ከዚህም በተጨማሪ የእንስሳቱን አያያዝ በተሻሻለ መንገድ መጠቀም ስለጀመሩ መድኃኒቶቹን እንደማይጠቀሙ እና ስለመድኃኒቱ ጥራት ለማወቅ የላብራቶሪ ምርመራ ወሳኝ እንደሆነ ሆኖም ግን የመድኃኒት እጥረት በሀገራቱ ያሉት የቁጥጥር አካላት/SRA/ ማረጋገጥ ሚገባቸውን(CPP/SPC/Free sale certificate) አረጋግጠው መላክ ይጠበቅባቸዋል በማለት እንዲሁም ባለስልጣኑ አስፈላጊ ነው ብሎ

ባመነበት ሰዓት የላብራቶሪ ምርመራ /ድህረ ገበያ ናመና ምረመራ / እንደሚያደርግ ለዚህም አምራች ድርጅቱ መተማመኛ የፅሁፍ ማስረጃ እንዲያስገባ ተደርጎ ካለ ላብራቶሪ ምርመራ ለጊዜው በዚሁ አግባብ እንዲስተናገዱ መደረጉ እና ግዥ እንድፈፅሙ መፈቀዱ የታወቀ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡

107. የባለስልጣኑ የአደማ ሞጆ ደረቅ ወደብ የቅርጫፍ መ/ቤት ሰራተኞች በቅርንጫፍ መ/ቤቱ በኩል አልፎ አልፎ የግዥ መጠየቂያ ሰነዶች ያለመሟላት እንደሚያጋጥምና ለባለስልጣኑ ሪፖርት በማቅረብ አስፈላጊውን መረጃ እንዲያቀርቡ በማደረግ መድኃኒቶቹ እንዲለቀቁ የሚደረግበት ሁኔታ እንደሚኖር ፣ ሀገር ውስጥ እየገቡ ያሉትን የእንስሳት መድኃኒቶች/የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮች በአካላዊ ምልከታ(ፊዚካል ኢንሰስፔክሽን) ብቻ በመጠቀም እየሰሩ መሆኑን በቀረበላቸው ቃለመጠይቅንና የኦዲት ቡድኑ ባረጋገጠው ምልከታ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በቦታው ለእይታ ጥርጣሬ የሚይፈጥርበት ሁኔታ ከሌለ በስተቀር ያለምንም የላብራቶሪ ምርመራ መድኃኒቶች የሚለቀቁበት ሁኔታ መኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

108. በዚህ ዙሪያ የቅርንጫፍ ሰራተኞቹ በሰጡት አስተያየት ቦታው ላይ የላብላቶሪ አገልግሎት ለማስጀመር ከኢኮኖሚ አንፃር ከባድ ቢሆንም ላብራቶሪው ቢቋቋም የመድኃኒቶችን ደህንነትና ፈዋሽነት መጠበቅና ማረጋገጥ እንደሚየያስችል በመግለፅ በአብዛኃኛው መድኃኒቶቹ ለብልሽት የሚዳረጉት በአያያዝ እና በሚጓጓዙበት ጊዜ ላላስፈላጊ ሙቀትና ቅዝቃዜ በሚጋለጡበት ሁኔታ መሆኑን የስራ ኃላፊዎቹ ሙያዊ አስተያየታቸውን የሰጡ ሲሆን በዚህ ላይም ባለስልጣኑ አየሰራበት እንዳልሆነም ጭምር ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ባለስልጣኑ የግዥ ትዕዛዞችን በመሚሰጥበት ጊዜ የጊዜ ገደብ ሊያበጅለት እንደሚገ እና ህገ-ወጦች በሚያጋጥሙበት ጊዜ አሰተማሪ እርምጃ ለመውስድ እንዲያስችል የእርምጃ አወሳሰድ መመሪያ ሊያዘጋጅ እንደሚገባውና የባለስልጣኑን ዳይሬክቶሬቶች የእርስ በርስ የስራ ጣልቃ ገብነትም ሊስተካከል እንደሚገባው ገልፀዋል፡፡

109. ስለሁኔታው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ባለስልጣኑ በሀገር ውስጥ የተመረተም ሆነ ከውጭ ሀገር የገባ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተገምግሞ ወይም ተረጋግጦ ከተመዘገበ በኋላ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግን በተመለከተ ሁሉም መድኃኒት በፖርት/port/ ላይ ማለትም በኮንሳይመንት ላይ ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፈዋሹነቱን ማረጋገጥ ቢቻል ጥሩ እንደነበረ ሆኖም ግን ከአቅም አንጻር ማድረግ እንደማይችሉ፣ የባለስልጣኑም አዋጅ የእንስሳት መድኃኒት ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባታቸው በፊት መረጋገጥ አለባቸው ቢልም ባለስልጣኑም የተከተለው የኢትዮጵያ ምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣንን ልምድ እንደሆነና ይህም የተወሰነው በማኔጅመንት እንደሆነ፣ ሆኖም ግን የመድኃኒት ጥራት፣ ደህንነትና ፈዋሽነት በላብራቶሪ ብቻ የሚገመገም አለመሆኑንና በአካልም እይታ የሚታይ እንደሆነ፣

የባለስልጣኑም ላብራቶሪ አሁን ስራ ስላልጀመረ ከገበያ እየተሰበሰበ ማየት እንደጀመሩ እና ለወደፊትም በማንኛውም ጊዜ ችግር ከተፈጠረ ከገበያ አይተው ማስቆም እንደሚችሉ ገልፀዋል፡፡

110. ይህንን በተመለከተ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እንደ መ/ቤት ላብራቶሪው በጊዜ ስራ ባለመጀመሩ ይህን ክፍተት ለመሙላት በፊት በኢትዮጵያ ምግብ፣መድኃኒትና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን ላብራቶሪ ከዚያም በማኔጅሜንት በማስወሰን ሰነድ ግምገማና መልከም አመራረት ያለፉትን በኮናሳይሜንት ናሙናና በድህረ ገበያ አሰራር ጥራትና ፈዋሽነት የማረጋገጥ ስራ ለማካሄድ ብሎ የወሰነው ስትራቴጅ እንደሆነ ምክንያቱም በባለስልጣኑ ቀርቶ በኢትዮጵያ ምግብ፣መድኃኒትና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን ላብራቶሪ እንኳ አስመጪዎች ለናሙና ብለው ጥራት ያለውን ናሙና ሲያመጡ ስለቆዩ እስካሁን የወደቀ ናሙና አለመገኘቱ፤እንዲሁም መኖን በተመለከተ ከባለስልጣኑ በፊት ተቆጣጣሪ አካል ባለመኖሩ የብቃት ማረጋገጫም ሳይኖራቸው በተለመደው አሰራር ሲያስገቡ እንደነበረ ነገር ግን ግንዛቤ ከተሰጣቸው በኃላ በልዩ ሁኔታ ፈቃድ ሳይሰጣቸው ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖራቸው አሁን ማንም እንደማያስገባ፤በ2008ዓ.ም ደሰሳ ጥናት ለማድረግ ታቅዶ አልተሰራም ለተባለው ከሪፖርት በኃላ ተተችቶ የተዘጋጀ ሙሉ የጥናት ውጤት ማግኘት እንደሚቻል፣እንዲሁም የክልኒካል ሙከራን በተመለከተ የአዳሚ ቱሉ ፀረ ተባይ መድኃኒት ዲያዝኖን 60% በሰበታ የእንስሳት ጤና ላብራቶሪ ድርጅቱ ባቀረበው የጥናት ፕሮቶኮል መሰረት ባለስልጣኑ ባመቻቸው መሰረት ጥናቱ እየተካሄደ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

111. ይሁንእንጂ ባለስልጣኑ ከውጭ ሀገር የሚገቡ  የእንስሳት መድኃኒቶች ላይ ከናሙና ጀምሮ እስከ ፖርት ድረስ ባለው ሂደት በወቅቱ ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ በላብራቶሪ እየተረጋገጠ ጥቅም ላይ እንዲውል አለማድረጉን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

## <u>ባለስልጣኑ የላብራቶሪና የክሊኒካል ጥናት በማደረግ የባህላዊ መደኃኒቶችን ደህንነት፤ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንድውሉ ስለማድረጉ በተመለከተ፣</u>

112. ባለስልጣኑ የላብራቶሪና የክሊኒካል ጥናት በማደረግ የባህላዊ መደኃኒቶችን ደህንነት፤ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንድውሉ ሊፈቅድ ይገባል፡፡

113. ባለስልጣኑ በ2007 ዓ.ም ለተመዘገቡ የእንስሳት መድኃኒቶች  10 ሳይንሳዊ መረጃ ለማዘጋጀት አቅዶ ስለመከናወኑ ያልተገለፀ መሆኑ ፣ በተጨማሪም የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የተለያዩ ዕፅዋት በቀንድ ከብቶች ውጫዊ ጥገኛ ተባዩች ላይ ያላቸውን ውጤት ምርምር ሲያካሄድ ቆይቶ በዚህም መሰረት ለቀንድ ከብቶች ውጫዊ ጥገኛ ተባዩች

በማጥፋት ጥሩ ውጤት የተመዘገበባቸው ሁለት ከዕፅዋት የተቀመሙ መድኃኒቶችን ከምርምሩ እንዳገኙ እና አነዚህን የምርምር ውጤቶች ለህብረተሰቡ ለማዳረስ በቅድሚያ መመዝገብ እንደሚያስፈልገው እና ባህላዊ መድኃኒቶችንም ለመመዝገብ ያላቸውን መመሪያ እንዲልኩላቸው ለባለስልጣኑ በደብዳቤ ቁጥር ኢ.ሕጤኢ. 534/71 በ22 ጥቅምት 2008 ዓ.ም ጠይቀው ቢሆንም እስካሁን የባህላዊ መደኃኒቶችን ደህንነት፤ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንድውሉ አለመፍቀዱ ታውቋል፡፡

114. በዚህ ጉዳይ ላይ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው እስካሁን ባለው ጊዜ ውስጥ ባለስልጣኑ የባህላዊ የእንስሳት መድኃኒቶችን ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት በማጥናት ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለማድረጉንና የባህላዊ ህክምና ድርጅቶችም ለባለስልጣኑ ጥያቄ እንዳላቀረቡ በተጨማሪም ባለስልጣኑ በእቅድ ደረጃ እንጂ ለማጥናት ከባህላዊ የእንስሳት መድኃኒት ተቋማት ጥያቄን ከመጠበቅ ውጭ በራሱ ለማጥናት እንዳልተንቀሳቀሰ በቃለ መጠይቅ ወቅት የገለፁ ሲሆን፤በተጨማሪም የእንስሳት መድኃኒት ጥራት ደረጃ፤ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የባህላዊ የእንስሳት መደኃኒቶችን ደህንነት፤ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ለእንስሳት ጤና አገልግሎት ውስጥ ጥቅም እንዲውል በተመለከተ የተለያዩ ባህላዊ መድኃኒቶችና ባህላዊ የህክምና አዋቂዎች በሀገሪቱ እንዳሉ ቢታወቅም ባለስልጣኑ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ የባህላዊ መድኃኒቶችን ለማስመዝገብ የቀረበ ጥያቄ ባለመኖሩ የባህላዊ መደኃኒቶችን ደህንነት፤ ፈዋሽነትና ጥራት የማረጋገጥ ስራ አለመሰራቱን ነገር ግን እንደሀገር ይህን ስራ ከሚመለከታቸው ሰዎች ጋር በቅንጅት እየሰሩ መሆኑን በመግለጫ ገልጸዋል፡፡

115. ስለሁኔታው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የላብራቶሪና የክሊኒካል ጥናት በማደረግ የባህላዊ መደኃኒቶችን ደህንነት፤ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንድውሉ ማድረግን በተመለከተ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የተጠየቀው በሳይንሳዊ አካሄድ እንጂ በባህላዊ መልኩ የተሰራ አለመሆኑን ይሁን እንጂ የላብራቶሪና የክሊኒካል ጥናት በማድረግ የባህላዊ መድኃኒቶችን ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግን በተመለከተ ክፍተቶች እንዳሉ፤ ይህም የሆነው ፈቃድ የጠየቀ አካልም ባለመኖሩ እንደሆነና ፡፡ በዚህም ዙሪያ ባለስልጣኑ ምንም ጥናት አለማድረጉንና መዋቅሩ እስከ ወረዳ ድረስ ባለመውረዱ ምክንያት እንዳልተሰራ ለወደፊት ግን ፈልገው ፈቃድ እንደሚሰጡ ገልፀዋል፡፡

116. ይህንን በተመለከተ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ባህላዊ መድኃኒትን በተመለከተ እስካሁን የቀረበ ጥያቄ አለመኖሩ፣ለኢትዮጵያየህብረተሰብ ኢንስቲትዩት የተለያዩ ዕፅዋት በቀንድ ከብቶች ውጫዊ ጥገኛ ተባዮች በዘመናዊ መድኃኒት እንዲያስመዘግቡ አሰራሩ ተገልፆላቸው እየተጠበቁ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

117. ይሁንእንጂ በአዋጁ መሰረት በባህላዊ መድኃኒቶች ዙሪያ የላብራቶሪና የክሊኒካል ጥናት እስካሁን አለማድረጉን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

## ባለስልጣኑ የድህረ-ገበያ ቅኝት በማድረግ በውጤቱ መሰረት እርምጃ ስለመውሰዱ፣

118. ባለስልጣኑ የተመዘገበ የእንስሳት መድኃኒት ከተሰራጨ በኋላ ያስገኘውን ጠቀሜታና ያስከተለውን ጉዳት ለማወቅ የድህረ-ገበያ ቅኝት በማድረግ በውጤቱ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

119. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት 12 የመድኃኒት አስመጪና 3አምራች ድርጅቶች ውስጥ ሁሉም(15ቱም) ድርጅቶች የእንስሳት መድኃኒት በባለስልጣኑ ያስመዘገቡ ቢሆንም ባለስልጣኑ መድኃኒቶቹ ከተሰራጩ በኃላ የድህረ ገበያ ጥናት በመድኃኒቶቹ ላይ ማስደረግ ቢገባውም የድህረ ገበያ ጥናት አድርጎ የማያውቅ መሆኑ እና ድርጅቶቹም የፋርማኮቪጅላንስ ማስረጃም ለባለስልጣኑ አቅርበው የማያውቁ መሆኑና ባለስልጣኑም ጠይቋቸው የማያቅ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

120. ይህም በመሆኑ የመድኃኒቶቹ ፈዋሽነት በተግባር ተረጋግጠው እና ተለይተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ እገዛ እየተደረገ አለመሆኑንና የንግድ እንቅስቃሴውም ላይ ለወደፊት ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ፣ በተግባር ደረጃ የመድኃኒቶቹን ጥራትና ፈዋሽነት መለየት እንዳላስቻለና በመድኃኒት አስመጪዎች መካከልም ለሀገሪቱ ጥራቱ የተረጋገጠ መድኃኒት ለማስመጣት የውድድር መንፈስ እንዳልፈጠረ ፣ የሚያሰራጯቸውን መድኃኒቶች ጥቅምና ጉዳት ለማወቅ የገበያ ፍላጎትንም ለማወቅ እንዳላስቻላቸው፣በመድኃኒቶቹ ጥራት፣ ደህንነትና ፈዋሽነት ላይ ጥርጣሬ እንደሚያሳድር እና በእርግጠኝነትም የመድኃኒቶችን የፈዋሽነት ደረጃ በየጊዜው ቀጣይ በሆነ መልኩ ይዘዋል ለማለት ማረጋገጫ እንደማይኖር፣የፋርማኮቪጅላንስ መረጃ የመድኃኒት አስመጪ ድርጅቶችን ባስመዘገቡት መድኃኒት ላይ በሚያጋጥሙ የጥራት ችግሮች ዙሪያ የተጠያቂነት ስርዓት ለማስፈን አስገዳጅ መሆን እንዳለበት ፣በገበያ ላይ ችግር እንዳስከተለባቸው ማለትም 3የተለያየ የመከላከል አቅም ያለውና(different size active ingredient) መጠኑ የተለያየ ሆኖም ግን በስም አንድ ዓይነት መድኃኒት በገበያ ያለ ሲሆን በመጠኑ ልዩነት በመኖሩ ገዥዎችን እያወዛገበ መሆኑ የድርጅቶቹ የስራ ኃላፊዎች የገለፁ መሆኑ፡

121. በ2007 ዓ.ም በስራ ክፍሉ አገልግሎቶች የተገልጋይ እርካታ ደሰሳ ለማካሄድ 40 መጠይቅ ለማሠራጨት እንዲሁም 4 የተገልጋይ እርካታ ደሰሳ ጥናት ውጤት ሪፖርት ለማዘጋጀት አቅዶ ስለመከናወኑ ያልተገለፀ መሆኑ በተጨማሪም በ2008 በጀት ዓመት የእንስሳት

መድኃኒት፣ ክትባት፣ ውጤቶችና መኖ የሙከራ ጥራት ምርመራ ስራዎችን ለማከናወን የታቀደ ቢሆንም በእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ያልተገለፀ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

122. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ባለስልጣኑ የባለስልጣኑ ላብራቶሪ ስራውን ባለመጀመሩ ምክንያት በተሰራጩት የእንስሳት መድኃኒቶች ላይ የድህረ ገበያ ጥናት አለማድረጋቸውን የገለጹ ሲሆን፤ ባለስልጣኑ የተመዘገበ የእንስሳት መድኃኒት ከተሰራጨ በኋላ ያስገኘውን ጠቀሜታና ያስከተለውን ጉዳት ለማወቅ ላብራቶሪው ባለመጠናቀቁ ከላብራቶሪ ቴስት ውጭ በአንድ የመድኃኒት አስመጪ ድርጅት(ትሮፕካል) እና በ4 የመኖ አምራች የግለሰብ ድርጅቶች ላይ ብቻ የድህረ-ገበያ ቅኝት መደረጉን እና ይህንንም ባለማድረጉ እየተቆጣጠረ ነው ለማለት በራስ መተማመንን እንዳሳጣቸው በዚህም ላይ 3 የተበላሹ መድኃኒቶች የተገኙ መሆኑንና እንዳይሰራጩ እና እንዳይለወጡ ባለድርጅቱን በኢንስፔክሽን ሪፖርት እንዲፈርም መደረጉን ሆኖም ግን ለክልሎች የተሰራጨው እንዲሰበሰብ ለማድረግ በሂደት ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

123. ይህንን በተመለከተ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የድህረ ገበያ ቅኝት ያልተደረገው ናሙናውን ለማሰራት ላብራቶሪው ወደ ስራ እስከሚገባ ድረስ የነበረ ሲሆን፤አሁን ግን ወደ ስራ ስለገባ በ2009ዓ.ም ከ3ኛ ሩብ ዓመት ጀምሮ የሚሰራ እንደሚሆን ተገልጿል፡፡

## ባለስልጣኑ የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የሚያስችል እና ያለመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶችን ዝርዝር መመሪያዎች ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤

124. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ጥቅም ላይ የሚውለው አግባብ ያለው መድኃኒት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ ባለስልጣኑ በሚያወጣቸው የአሰራር መመሪያዎች መሰረት ሊሆን እና ከእንስሳት ሀኪም በተጨማሪ በሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ትዕዛዝ እና ያለመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶችን ዝርዝር በመመሪያ ሊወሰን ይገባል፡፡

125. በአዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ 6/2 ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ጥቅም ላይ የሚውለው አግባብ ያለው መድኃኒት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ ባለስልጣኑ በሚያወጣቸው የአሰራር መመሪያዎች መሰረት መሆን አለበት ቢልም ባለሰልጣኑ የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር መመሪያ አለማውጣቱ ፣

126. በኦዲቱ ወቅት ከታዩ ድርጅቶች ውስጥ 6 የመድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች እና 5 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች እና አንድ አምራች ድርጅት ባለስልጣኑ የእንስሳት መድሃኒቶች ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል መመሪያ እንዳላዘጋጀ እና ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት

ጥቅም ላይ መዋሉን እንደማይከታተል እንዲሁም መመሪያ በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ስለማዋል ያከናወነው ተግባር አለመኖሩን የገለፁ መሆኑ፤

127. ይህም በመሆኑ ለሀገሪቱ አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶች በጥናት ተለይተው በብዛት ተደራሽ እንዳይሆኑ እንደሚያደርግ እንዲሁም በገኘዎች በኩል ቅሬታ ካልቀረበ በስተቀር እንደማይከታተል የስራ ኃላፊዎቹ ገልፀዋል፡፡

128. በዚህ ጉዳይ ላይ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በመመሪያ ደረጃ ሳይሆን ከጎንደር ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር የእንስሳት መድኃኒት አጠቃቀምና አያያዝ በሚመለከት የአጠቃቀም ማንዋል/Rational veterinary drug use manual/ እንዳዘጋጁና የእንስሳት መድኃኒት አጠቃቀም በጤና ተቋማት ምን መምሰል እንዳለበትና በመድኃኒት ተቋማት ደግሞ አያያዝ ምን መምሰል እንዳለበት ለሚመለከታቸው የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠትና በመድኃኒት ተቋማት ደግሞ አያያዝ ምን መምሰል እንዳለበት ክትትልና ቁጥጥር እንደሚደረግ ግንዛቤም እንደሰጡ ከእንስሳት መድኃኒት ጥራት ደረጃ፣ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በመግለጫ እና በቃለ መጠይቅ ምልሽ የተሰጠ ሲሆን፤ በተጨማሪም የእንስሳት መድኃኒትና ምግብ እና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን ከ10 ዓመት በፊት standard treatement guidline ያወጣው መመሪያ እንዳለ ሆኖም ግን ባለስልጣኑ update አለማድረጉን ያላደረገበትም ምክንያት የቀድሞው ባለሰልጣን ብዙ አስጠንቶ መመሪያውን ያወጣው በመሆኑና resource based ነው በማለት መሆኑን፤ ይሁንእንጂ በጋይድ ላይኑ መሰረት የእንስሳት መድኃኒት ጥቅም ላይ ስለመዋሉ የመከታተል ኃላፊነትም የባለስልጣኑ ሳይሆን የቀድሞው የግብርና ሚኒስቴር ኃላፊነት መሆኑን የኢንስፔክሽን ክፍል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ገልፀዋል፡፡

129. ባለስልጣኑ ከእንስሳት ሀኪም በተጨማሪ በሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ትዕዛዝ እና ያለመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶችን ዝርዝር በመመሪያ አለመወሰኑ ታውቋል፡፡

130. በመሆኑም በኦዲቱ ወቅት ከታዩት 9 ድርጅቶች ውስጥ 2ቱ ውስጥ በመመሪያ ባለመወሰኑ ስራቸው ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ማለትም ገበያቸው እንዲቀንስ እንደሚያደርግ እንዲሁም በህክምና ዘርፍ ጉዳት እንዳለው በተጨማርም በሀይበርመልቲን እና በአልመንዳዞል የተባሉ የእንስሳት መድኃኒቶች አገር አቀፍ በሆነ መልኩ ባለመገለፁ በቀለማቸው ብቻ የሚለዩበትና የሚታዘዙበት ሁኔታ መፍጠሩን እንዲሁም 7ቱ ድርጅቶች ደግሞ ቀጥተኛ ችግር ባይኖርም እንደ ሀገር የመጨረሻ ተጠቃሚዎች ላይ ችግር እንደሚያስከትል፣ ለቸርቻሪዎች ተፅዕኖ እንደሚኖረውና የሚሰራጩት መድኃኒቶች የሚላመዱበት ሁኔታም እንደሚኖር፣ ማንኛውም ፋርማሲስት ያለመዘዣ ወረቀት እያዘዙ ስለሆነ የእንስሳት መድኃኒት ክሊኒኮች እንዳይስፋፉ እንደሚያደርግ የየድርጅቶቹ የስራ ኃላፊዎቹ የገለፁ መሆኑ፣

131. ስለሁኔታው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ባለስልጣኑ እስካሁን በእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ትእዛዝ እና ያለመድኃኒት ማዘዣ ሊታደሉ የሚችሉ መድኃኒቶችን ዝርዝር መመሪያውን አለማውጣቱን ሆኖም ግን ማወጣት እንደነበረባቸው ነገር ግን በሌሎች ስራዎች በመጠመድ እንደዘገዩና ሌላው ደግሞ በገበያ ላይ ያሉ መድኃቶች በቁጥርና በዓይነት ውስን በመሆናቸው ምክንያት ባለስልጣኑ መጀመሪያ የመድኃኒቶቹ ብዝሃነትና ቁጥር መጨመር ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት አለበት ብለው በማመናቸው እንደሆነና  ሆኖም ግን በሚቀጥለው አመት መመሪያውን ለማውጣት ጥረት እንደሚያደርጉ በሰጡት መግለጫ ላይ ገልፀዋል፡፡

132. ይህንን በተመለከተ በባለስልጣኑ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር መመሪያ አለማዘጋጀቱን በተመለከተ ባለስልጣኑ ለመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም የስልጠና ማንዋል እንዳዘጋጀ፤ሆኖም ግን በእያንዳንዱ መድኃኒት ላይ አምራቹ ለአስመጪዎች አጠቃቀሙን ከመድኃኒት ጋር አያይዞ እንደሚልክ ነገር ግን ድርጅቶች ሲጠየቁ  ስለማያውቁ መድሃኒት ጥቅም ላይ ለማዋል የሚስችል አሰራር መመሪ አልደረሰንም ሊሉ እንደሚችሉ እንዲሁም በባለሙያዎች ትዕዛዝና ያለመድኃኒት ማዘዣ ሊታደሉ የሚችሉ የእንስት መድኃኒቶችን ዝርዝር መመሪያ አለመወሰኑ ለሚለው በማዘዣ ብቻና ያለማዘዣ ወረቀት የሚታደሉ መድኃኒቶችን አስመልክቶ በሀገሪቱ ያሉት መድኃኒቶች በዓይነትም ሆነ በቁጥር አነስተኛ በመሆናቸው ባለስልጣኑ በአሁን ወቅት በማዘዣ ብቻና ያለማዘዣ ወረቀት የሚታደሉ መድኃኒት ለማውጣት አስፈላጊ አለመሆኑን፣የእንስሳት መድኃኒት በሁሉም ባለሙያዎች የታወቁ እንደሆኑና ወደፊት ህገወጥ አሰራሮችን በእጅጉ ከቀነሰ በኃላና አመቺ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ እንደሚሰራ ተገልጿል፡፡

133. ይሁንእንጂ በማዘዣና ያለማዘዣ ወረቀት የሚታደሉ መድኃኒቶች ግዢ በተጠቃሚው ላይ ችግር እንደሚያስከትል ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶች፤ መኖዎች ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮች የአወጋገድ መመሪያ ማውጣቱን በተመለከተ፤

134. ባለስልጣኑ  የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸውን የእንስሳት መድኃኒቶች፤ መኖዎች ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮች አወጋገድን በተመለከተ  ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን መመሪያ ተከትሎና አከባቢን በማይበክል መንገድ  በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

135. በኦዲቱ ወቅት የታዩት5 የእንስሳት መድኃኒቶች አስመጪ፣ 1ጅምላ አከፋፋይ እና 2 አምራች ድርጅቶች  መጋዘን  ውስጥ ከ2006 ዓም ጅምሮ ጊዜ ያለፈባቸውና በልዩ ልዩ

ምክንያቶች ለብልሽት የተዳረጉ የእንስሳት መድኃኒቶች ያሉ ሲሆኑ የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በቁጥጥር ጊዜ ቢያዩም በተጨማሪም ፎርም ቀርፀው በዝርዝር አሳውቁን ብለው ያሳወቁአቸው ቢሆንም ባለስልጣኑ የአወጋገድ መመሪያ እስኪያወጣ ድረስ ተለይተው እንዲቀመጡ ከማድረግ ውጭ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ አለመደረጉ የስራ ኃላፊዎቹ የገለፁ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ባለስልጣኑ አካባቢን እንደሚበክልና እንደማይበክል ሳያጠና እንዲሁም ያለምንም የአወጋገድ መመሪያ ባለስልጣኑን ሳያሳውቁና በማሳወቅ ያስወገዱ ድርጅቶችም እንዳሉ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 7 የመኖ አምራች እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪ ድርጅቶች ውስጥ 3ቱ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው የመኖ ንጥረ-ነገር እና መኖ ያላቸው ሲሆኑ እንዲሁም 4 ድርጅቶች ያስወገዱበት ሁኔታ ቢኖርም በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን ባለስልጣኑ አለመቆጣጠሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዝርዝራቸውም 14 ነጥቦች በአባሪ 7 ከሪፖርቱ ጋር ተያይዟል፡፡

136. እንዲሁም የባለስልጣኑ የመኖ አምራች፣ አስመጭ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የምዝገባና የስራ ፈቃድ መስጫ አሰራር መመሪያ ቁጥር 03/2007ዓ.ም መሰረት የተበላሹ፣ የተከለሱ ወይም የመጠቀሚ ጊዜ ያለፈባቸውን መኖ ወይም የመኖ ግብአቶችን እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው ከሌሎች ተለይተው ጥቅም ላይ እንደማይውሉ ሚገልፅ ፅሁፍ በመለጠፍ ለብቻ መቀመጥ(መደርደር) እንዳለባቸው ቢገልፅም አዲስ አለም የእስሳት መኖ ማምረቻ ድርጅት የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት የመኖ ግብዓት አጋጥሟቸው እንደሚያውቅና ግብቶቹንም በራሳቸው ማለትም ለባለስልጣኑ ሳያሳውቁ እንዳቃጠሉት ገልጸዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜም ሊወገዱ የተለዩ ግብዓቶች እንዳሉና ተለይተው በተቀመጡበት ቦታ በስብሰውና አስፈላጊውን ቁጥጥር ሳይደረግባቸው ሜዳ ላይም የተበተኑበት ሁኔታ እንዳለ የኦዲት ቡድኑ በአካል ለማየት መቻሉ፤ በተጨማሪም የባለስልጣኑ ባለሞያዎች ጊዜ ያለፈባቸው የእንስሳት መድኃኒቶችን ለመውረስ የአወጋገድ መመሪያ በባለስልጣኑ ባለመውጣቱ በአደራ እንዳስቀመጡ በጎንደር አከባቢ በሚያዝያ/2008 ዓ.ም አዋሳኝ ወረዳዎችና ዞኖች በተካሄደውን ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር የማፅዳት ስራ ሪፖርት ላይ የተገለጸ መሆኑ ታውቋል፡፡

137. በመሆኑም የእንስሳት መድኃኒቶች እንዲሁም የመኖ ንጥረ ነገሮች እና መኖ በአወጋገድ መመሪያ መሰረት በወቅቱ እና በተገቢው ቦታ አለመወገዳቸው በአካባቢ ላይ ብክለት ሊያስከትል ይችላል፡፡

138. ስለሁኔታው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የአወጋገድ መመሪያ ማዘጋጀትን በተመለከተ የየትኛው ዳይሮክቶሬት ስራ እንደሆነ ለማወቅ ባለመቻሉ እስካሁን ተዘጋጅቶ ሳይፀድቅ እንደቆየ፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት በኩል ረቂቅ መመሪያው ተዘጋጅቶ ለውይይት ለማኔጅመንት ለማቅረብ ዝግጅት ላይ እንደሆኑ፤

ባለስልጣኑ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸውን መኖዎች ወይም ንጥረ ነገሮችን ጥቅም ላይ እንዳይውሉ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን ለመቆጣጠር በ2008 በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም በመመሪያ ምክንያት ወደ ስራ እንዳልገቡ እና መኖን በተመለከተ እንደ መድኃኒት መርዛማ ባለመሆኑ ድርጅቶች እንዲያስወግዱ አልፎ አልፎ እንደሚፈቅዱ ይህ የሚሆነው ግን የባለስልጣኑ ባለሙያዎች ባሉበት ሲሆን ብቻ እንደሆነ፡፡ የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በሌሉበት ያስወገዱት አራት የመኖ አምራች ድርጅቶች ተገቢ ስራ አለመስራታቸውን እንዲሁም ራንግቬት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት ያስወገደውን በተመለከተ ባለስልጣኑ እንደተቋቋመ አካባቢ በመጠየቁ እንደተወገደለት ሆኖም ግን በዚህ ሁኔታ መቀጠል ስለሌለበት መመሪያ እስኪወጣ ሌሎች ለይተው እንዲያስቀምጡ እያደረገ መሆኑን ይሁን እንጂ ሁሉም በመመሪያ መስተናገድ ቢገባም ለአንዱ ተፈቅዶ ለሌላው መከልከሉ አግባብነት እንደሌለው መረዳታቸውን ገልፀዋል፡፡

139. ይህንን በተመለከተ በባለስልጣኑ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የእንስሳት መድኃኒቶች የአወጋገድ መመሪያንም በተመለከተ ድራፍት መመሪ በ2009ዓ.ም.በ2ኛው ሩብ ዓመት ተዘጋጅቶ ለትችት እንደቀረበ ተገልጿል፡፡

140. ይሁንእንጂ በአዋጅ ቁጥር 728/2004ዓ.ም መሰረት እነዚህ መመሪያዎች በወቅቱ ተዘጋጅተው ስራ ላይ አለመዋላቸው ተጠያቂነትንም እንዳያጠናክር አለማድረጉን ለመረዳት ችለናል፡፡

## 2.3. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶች ደህንነታቸውና ፈዋሽነታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ እንዲሁም የእንስሳት መኖ ደህንነት በተዘጋጀው የምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ መመዘኛ መስፈርት መሰረት እየተሰራ ስለመሆኑ የድጋፍ ፡ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤

### ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን ፈዋሽነት እና የእንስሳት መኖና የመኖተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኅንነትና ጥራት ደረጃዎች በማዘጋጀትና በማፀደቅ ስራ ላይ ስለማዋሉ በተመለከተ፤

141. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ደረጃዎች እንዲሁም የእንስሳት መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኅንነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

142. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብና ተከታትሎ በማፀደቅ ስራ ላይ አለማዋሉ ታውቋል፡፡

ይህም በመሆኑ ባለስልጣኑ በዝርዝር ውስጥ የተካተቱ ለሀገሪቱ አስፈላጊ የሆኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን የጥራት ቁጥጥር ለማድረግ በ2006 ዓ.ም አቅዶ ያላከናወነ መሆኑ፤

143. እንዲሁም ባለስልጣኑ የእንስሳት መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኅንነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብና በማፀደቅ ስራ ላይ አለማዋሉ ታውቋል፡፡ ይህም በመሆኑ ባለስልጣኑ በ2007 በጀት ዓመት 4 የክትትልና የግምገማ ስራዎችን ለማካሄድ አቅዶ አለማከናወኑ በተጨማሪም ቃሊቲ የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ድርጅት የእንስሳት መኖ ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን ለመፈተሽ አንድ ጊዜ ብቻ ናሙና በመውሰድ የምርመራ ውጤቱን በግብረ- መልስ አማካኝነት እንደሰጣቸው በቃለ-መጠይቅ ወቅት የገለፁ ቢሆንም ባለስልጣኑ በሰጣቸው የላብራቶሪ ውጤት መሰረት ማለትም በ2007 ዓ.ም 5 ዓይነት የመኖ ናሙናዎችን በመውሰድ ከመኖ ጥራት ደረጃ አንፃር የተካሄደው ፍተሻ እንደሚያሳየው Crude Fiber እና Crude Fat ከተቀመጠው የመኖ ጥራት ደረጃ መስፈርት በጣም የበዛ መሆኑ፤ለታላቢ ዳልጋ ከብት(Lactating Cows) የተዘጋጀው መኖ የCrude Protein ይዘት ከተቀመጠው የመኖ ጥራት ደረጃ መስፈርት አንፃር አነስተኛ መሆኑ፤ በተለያየ የዕድሜና ምርታማነት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ዶሮዎች የተመረተው መኖ የካልሴም ይዘት ከተቀመጠው መስፈርት ያነሰ ስለመሆኑና እንዲሁም የካልሴምና ፎስፈረስ ይዘት የተመጣጠነ አለመሆኑን እና ለቄብ ዶሮ (Pullets) የተመረተው መኖ የCrude Protein ይዘት ከተቀመጠው የመኖ ጥራት ደረጃ መስፈርት አንፃር አነስተኛ መሆኑን ከላብራቶሪ ውጤት ትንተና ባለስልጣኑ በምክረ ሀሳብ መልክ ለድርጅቱ ቢያቀርብም ድርጅቱ ለቄብ ዶሮ (Pullets) የተመረተውን መኖ ምርመራ ውጤት እንደማይቀበሉ እና የባለስልጣኑ የመኖ ስታንዳርድ መነሻ ከዓለም አቀፍ ስታንዳርዱ ያፈነገጠ በመሆኑ ችግሩን ለባለስልጣኑ አቅርበው ምላሽ አለመሰጠቱን የገለፁ መሆኑ፤

144. በዚህም ዙሪያ ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን፣ ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ደረጃዎችን በማዘጋጀትም ሆነ ለማሻሻል ለደረጃዎች ኤጀንሲ መረጃ/ማስረጃ ያቀረበበት ወይም እንዲጸድቅ ጥያቄ የጠየቀበት ሁኔታ አለመኖሩን የመኖ ደረጃን በተመለከተ ግን ባለስልጣኑ ሀያ ሰባት(27) የእንስሳት መኖ ደረጃዎችን ማለትም ሦስት አዳድስ እና ሀያ አራት ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ደረጃ የነበሩና ክለሳ የተደረገባቸው ደረጃዎችን ረቂቅ በማዘጋጀት ለኤጀንሲው እንዳቀረበና ኤጀንሲው እስካሁን ደረጃዎችን በማፅደቅ ለባለስልጣን መ/ቤቱ አለማቅረቡን የገለፁ ሲሆን፤ ይህም የሆነበት ምክንያት ብሔራዊ ደረጃዎች የሚዘጋጁት በሀገሪቱ ካሉ ተቋማት በተውጣጡ ባለሙያዎች በሚሳተፉበት ብሔራዊ የቴክኒክ ኮሚቴ ሲሆን በሀገራችንም ሆነ በአለም አቀፍ አሰራር ደረጃዎች ፀድቀው ወደስራ ከመግባታቸው በፊት የላብራቶሪ ፍተሻዎችን ማለፍና ሂደቱን እና ተያያዥ ጉዳዮችን የተለያዩ ተቋማት ሚኒስቴር መ/ቤት የሚሳተፉበትና በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚመራው ካውንስል ተቀብሎ

ሲያፀድቃቸው መሆኑንና በባለስልጣኑ ተዘጋጅተው ቀርበው የነበሩት ደረጃዎች ተጨማሪ ግብዓትና ማብራሪያ እንዲሰጥባቸው ሲባል እስካሁን አለመፅደቃቸውን የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች የገለፁ መሆኑ፣

145. ይህም በመሆኑ መኖ ጥራት ደረጃን መሰረት ያላደረገ ክትትል እንዲኖርና የባለስልጣኑንም የቁጥጥር ስራ ተአማኒነት እንዳይኖረው ሊያደርግ ይችላል፡፡

146. ስለሁኔታው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በመድኃኒት ደረጃዎች ዙሪያ የዓለም አቀፍ ደረጃ/መስፈርት ያሟላል ወይስ አያሟላም የሚለውን ከማየት ውጪ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመድኃኒት ደረጃ ማዘጋጀት እንደማያስፈልግ፡፡ እንደ ሀገር ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ሀገሪቱ አቅም እንደሌላት፤ በዚህ ምክንያት እንደ እንስሳት መኖ ለመድኃኒቶች ደረጃ እንዲዘጋጅ ለደረጃዎች ኤጀንሲ ጥያቄ አቅርበው የማያውቁ ሲሆን፤ መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኅንነትና ጥራት በተመለከተ በመኖ ዙሪያ ሀያ (20) ደረጃዎች እንዲከለሱ እንዲሁም ስምንት (8) ደረጃዎች በአድስ መልክ እንዲዘጋጁ ለደረጃዎች ኤጀንሲ እንዳቀረቡ፡፡ ኮሚቴ ተቋቁሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉትን የመኖ ደረጃዎች በምን አይነት መልኩ ወደሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ማምጣት እንደሚገባ በመሰራት ላይ እንደሆኑ ነገር ግን ከተቋቋመው ኮሚቴ አቅም በላይ የሆኑ ስራዎችም እንዳጋጠሙአቸው ገልፀዋል፡፡

## ባለስልጣኑ ወደ ውጭ ሀገር ለሚላክ መኖ የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠቱን በተመለከተ፣

147. በአዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ 18/2 ማንኛውም ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ መኖ በባለስልጣኑ የተሰጠ የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው መሆን አለበት

148. ይሁን እንጂ ባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ አውጥተውና ሳያወጡ በተደጋጋሚ መኖና የመኖ ግብዓት ወደ ውጭ ሀገር የሚልኩ ድርጅቶች ቢኖሩም ባለስልጣኑ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ወደ ውጭ ሀገር ለሚላኩ ለእንስሳት መኖዎች የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት ያልጀመረ መሆኑ ታውቋል፡፡

149. የበርካታ ዓይነት መኖ ቅልቅል ፋጉሎ(የኀመን ዘር፣የኑግ፣የተልባ፣ ለውዝ፣እና የጥጥ ፍሬ ወዘተ) እንዲሁም ሌሎች በበላይ አመራር አካላት ትዕዛዝ ወደ ውጭ ይላክ እንደነበረ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 8 ከሪፖርቱ ጋር ተያይዟል፡፡

150. ስለሁኔታው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከባለስልጣኑ ፈቃድ አውጥቶ መኖን ወደ ውጭ ሀገር የሚልክ አንድ ድርጅት ብቻ ሲሆን ይህም ድርጅት ኤልፎራ እንደሆነና ድርጅቱም በራሱ ማሳ ላይ ምርቱን ዲሃይድሬት በማድረግ ወደ ውጭ እንደሚልከው፤ ይህም ድርጅት ወደ መስመር ሊገባ የቻለው ከብዙ ድካም በኋላ እንደሆነ፤ ሆኖም ግን ከተለያዩ

ድርጅቶች ሰብስበው ወደ ውጭ ሀገር የመኖ ግብዓቶችን የሚልኩ ድርጅቶች እንዳሉ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን እንዳወቁ፤ በሌላ በኩል ጥቅምት 2000ዓ.ም በግብርና ሚኒስቴር መኖ ከሀገር ውጭ እንዳይወጣ ተከልክሎ እንደነበረና በዚህ ላይ አንድ አካል ሲፈቅድ ሌላው ደግሞ ሲከለክል እንደቆየ ይሁን እንጂ የጥራት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ግን እስካሁን ድረስ ያልሰጠንበት ምክንያት መኖ የተላከለት ሀገር ላኩልኝ ብሎ ባለመጠየቁ እና ላኪው ድርጅትም ለባለስልጣኑ ጥያቄ ባለማቅረቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

## ባለስልጣኑ የዘርፉን የመረጃ አያያዝ፣ልወውጥ እና አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ስለማድረጉ በተመለከተ፤

151. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ የመረጃ አያያዝ፣ልወውጥ እና አጠቃቀም ስርዓት ሊዘረጋ እና መረጃዎቹን በዳታ ቤዝ አጠናክሮ ሊይዝ እንዲሁም ባለስልጣኑ ወቅታዊ የሆኑ የእንስሳት መዲኃኒትና መኖ መረጃዎችን በመደበኛነት ለባለሙያዎችና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚያስተላልፍበትን ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

152. በባለስልጣኑ በ2007 በጀት ዓመት የመረጃ አያያዝ፣ ልወውጥና አጠቃቀም ስርዓት በተደራጀ እና በተገቢው መልኩ ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል እንዲሁም የባለስልጣኑ ስራዎችን በመረጃ ቴክኖሎጂ አስደግፎ ለመስራት አቅዶ አለመስራቱ፣ በተጨማሪም በእንስሳት መድኃኒትና በህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ንግድ ላይ የተሰማሩ የንግድ ድርጅቶችን መረጃ ለማዘጋጀት 2 አቅዶ ስለመከናወኑ ያልተገለፀ መሆኑ፣

153. ባለስልጣኑ ወቅታዊ የሆኑ የእንስሳት መዲኃኒትና መኖ መረጃዎችን በመደበኛነት ለባለሙያዎችና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚያስተላልፍበትን ስርዓት አልዘረጋም፡፡በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 29 ድርጅቶች ውስጥ 9 ድርጅቶች (ዛፍ ፋርማሲስውቲካል፣ጎናፍርና ልጆቹ ፣ የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን ፣ ኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ፣ አለማ ፋርም ፣ ራንግቬት ፅጌ ፣ ፈሁላ እና ሳቫና የእንስሳት መድኃኒት ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች) ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር የእንስሳት መድኃኒትን እና የህክምና መሳሪያዎችን በተመለከተ የሚኖሩትን ወቅታዊ መረጃዎች የሚለዋወጥበት ስርዓት አለመኖሩን እንዲሁም ሌሎች 7ቱ (ባዮቴክ ፤ ትሮፒካል ፋርማ ፡ ማርቆስ ፣ ጎናፍርና ልጆቹ ፤ አግቴክ ፤ ኤ.ኤች.ኤም የእንስሳት መድኃነት አስመጪ ድርጅቶች አግሪን የእንስሳት መድኃኒት ጅምላ አከፋፋይ) እንዲሁም 3ቱ አምራቾች(ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት ፣አዳሚ ቱሉ እና ኢስት አፍሪካ የመድኃኒት አቅራቢ ድርጅት) በተጨማሪም 8 የመኖ አምራችና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር ድርጅቶች(ፒካና ፣ ኢኳቶሪያል ቢዘነስ ግሩፕ፣ቃሊቲ ፣ አቃቂ ፣ ኢትዮ ፊድ ፣ ቦራ እና አለማ ካውዳይስ የእንስሳት መኖ ማደራጃ/ማምረቻ ኃ/የተ/የግ/ ድርጅቶች እና ኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ) ባለስልጣኑ በመደበኛነት ለባለሙያዎችና ለተጠቃሚው

ህብረተሰብ ወቅታዊ የሆኑ  የእንስሳት መዲኃኒትና መኖ መረጃዎችን የሚያስተላልፍበትን ቋሚ የሆነ የመረጃ ስርዓት እንደሌለው የገለፁ መሆኑ፡

154. ይህም በመሆኑ የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማወቅ እንዳላስቻላቸው እንዲሁም እንደ ሲክተሩም መረጃ ልውውጥ  ባለመኖሩ ምንምን ዓይነት መድኃኒት እንደሚያስመጡ ባለመታወቁ በድርጅቶቹ ገበያ ላይ ችግር እየፈጠረ መሆኑን  ከዚህም የተነሳ ስራው በግምትና በድፍረት እተሰራ መሆኑን ፣ ሀገሪቱ የሚያስፈልጋትን የመድኃኒት ዓይነት መረጃም አለመኖሩን፣ መረጃ ሲፈልጉም ለባለስልጣኑ ደብዳቤ በመፃፍ የሚያገኙበት ሁኔታ ብቻ እንዳለ  እና የእንስሳት መድኃኒትን በተመለከተም የመረጃ ስርዓት አለመኖሩንና አስፈላጊ መረጃዎች በወቅቱ ማግኘት እንዳላስቻላቸውና  አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት ባለስልጣን መ/ቤቱ ድረስ መሄድ እንደሚጠይቅ ይህ ደግሞ የገንዘብና የጊዜ ብክነት እያስከተለባቸው እንደሚገኝ፣ በመሆኑም ባለስልጣኑ ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችል የመረጃ ሲርዓት በመዘርጋት መረጃዎችን በሚፈለገው መጠንና ጊዜ እያደረሰ አለመሆኑን እና መደበኛ የሆነ የባለድርሻ አከላት ውይይት እንዳይኖር ማድረጉን እንዲሁም ቋሚ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ባለመኖሩ ለአላስፈላጊ ምልልስ እንደተዳረጉ እና ተወዳዳሪነታቸው ላይ ተፅዕኖ እንደፈጠረባቸው ፣በገበያም ዙሪያ ችግር እንደፈጠረባቸው ፣ ለስራቸው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት እንዳላስቻላቸው ፣ ለስራ መጓተትና ላላስፈላጊ ወጭ እንደተዳገሩ እንዲሁም በባለሰልጣኑ በኩል የሚቀየሩ የአሰራር ስርዓቶችንም/ለምሳሌ፣ፎርሞች/ በየጊዜው ለማወቅ እንዳላስቻላቸው የየድርጅቱ የስራ ኃለፊዎቹ ገልፀዋል፡፡

155. በሌላ በኩል ባለስልጣኑ  አስፈላጊ መረጃዎችን ከየዳይሬክቶሬቶቹ በማሰባሰብ ባለስልጣን መ/ቤቱን ለማስተዋወቅና ህገ-ወጥ ንግድን ለመቆጣጠርና ግንዛቤ ለመስጠት እንዲያስችል የተለያዩ ስራዎችን በሚዲያ ተቋማት አለማከናወኑ፣ በ2006 ዓ.ም የሀገር ውሰጥ ባለሙያዎችን በተለያዩ የልምድ ልውውጥ ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ ፣በ2007 በጀት ዓመት የጋራ ምክክር መድረክ በማዘጋጀት አብሮ ማቀድና አፈፃፀም ለመገምገም  እና 4የልምድ ልውውጥ መድረክ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ለማድረግ እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት በእንስሳት መድሃኒት ዙሪያ የቁጥጥር ማስገንዘቢያ መረጃዎች፣ ብሮሸሮች ፖስተር መጽሔቶች ለማዘጋጀትና ለመስራት የታቀደ ቢሆንም ስለመከናወኑ በአፈፃፀም ሪፖርቱ ላይ ያልተገለፀ መሆኑ፣ በተጨማሪም በ2007 በጀት ዓመት በእንስሳት መድኃኒትና መኖ ጥራት ቁጥጥር ህገ ወጥ ዝውውር ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በ16 ዙር ለማከናወን አቅዶ  ዕቅድ አፈፃፀሙ ላይ እንደ ዕቅድ የተቀመጠው 2 ዙር የሚል ሲሆን አፈፃፀሙም  24 በማድረግ 150% እንደተከናወነ ተደርጎ የተገለፀ መሆኑ እንዲሁም በህገ-ወጥ መድኃኒትና የመኖ ዝውውርን በተመለከተ በኬላዎች ላይ ለተሰማሩ ባለድርሻ አካላት ባለስልጣኑ 6 ጊዜ የግንዛቤ

ማስጨበጫ ስራዎችን ለማከናወን ያቀደ ቢሆንም በአፈፃም ሪፖርቱ ላይ 1 ጊዜ ብቻ በማከናዎን የዕቅዱን 100% እንደተከናወነ ተደርጎ መገለፁ ታውቋል፡፡

156. ስለሁኔታው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ዙሪያ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት እንዲሁም መረጃዎችን በዳታ ቤዝ አጠናክሮ መያዝን በተመለከተ ስርዓቱም በባለስልጣኑ እንደሌለና ድህረ ገፅ በመዘርጋት ስራ ላይ ስለነበሩ ድህረ ገፁ ቢዘረጋም በባለሙያ ያልተደገፈ በመሆኑ ስራውን እንዳልጀመሩ ባለሙያም ለመቅጠር ቢሞክሩም ባለስልጣኑ ያወጣው የደመወዝ ስኬል ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት ባለሙያዎችን ለማቆየት እንዳልተቻለ እንዲሁም ወቅታዊ የሆኑ የእንስሳትና መኖ መረጃዎችን በቋሚነት ለተጠቃሚ ህብረተሰብ በቋሚነት ተደራሽ ማድረግን በተመለከተ በአካል መምጣት የማይችሉ ባለጉዳዮችም መረጃዎችን የሚያገኙበት ስርዓት እንዳልተዘረጋ እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒት መረጃን በሚመለከት ከሞላ ጎደል የቁጥጥር መረጃዎችን መዝግቦ መያዝ ለሚመለከተው አካል የሚያቀርቡበት ሁኔታ እየተሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

157. ይህንን በተመለከተ በባለስልጣኑ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ባለስልጣኑ በኮሚንከሽን ዳይሬክቶሬትና በመረጃና ደረጃ ቡድኖች የተለያዩ መፅሄቶችን፣ብሮሸሮችን፣አዋጅና ደንብ ጭምር እያዘጋጀ እንደሚሰጥ፣ድህረ ገፅም እንዳዘጋጀ ነገር ግን የአይቲ ባለሙያ የመልቀቅና ያለመቀጠር ችግር እንዳለ ተገልጿል፡፡

158. ይሁንእንጂ ተዘረጋ ተባለውም ድህረ ገፅ በአንድ ዳይሬክተር ስም ቢሆንም ስለ ባለስልጣኑ በቂ መረጃ አለመያዙን በኦዲት ቡድኑ ለማየት ተሞክሯል፡፡

## የክልል አካላት ስለሰጧቸው፣ ስላገዷቸውና ስለሰረዟቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች እና የሙያ ፈቃዶች ለባለስልጣኑ መረጃ መተላለፉን በተመለከተ፣

159. ባለስልጣኑ አግባብ ያላቸው የክልል አካላት ስለሰጧቸው፣ ስላገዷቸውና ስለሰረዟቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች እና የሙያ ፈቃዶች ለባለስልጣኑ መረጃ መተላለፉን ሊከታተል ይገባል፡፡

160. ከባለስልጣኑ ለሁሉም ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ስለሰጧቸው፣ ስላገዷቸውና ስለሰረዟቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች እና የሙያ ፈቃዶች መረጃ እንዲያስተላልፉ ሰርኩላር ቢተላለፍም በእንስሳት መድኃኒት ዙሪያ ከ2006-2008ዓ.ም ከአራት ክልሎች (ከአማራ፣ ኦሮሚያ ፣ከትግራይና ከደቡብ) ውጪ ሌሎቹ ክልሎች በዚህ ዙሪያ ለባለስልጣኑ መረጃ እንደማያስተላልፉ እንዲሁም በእንስሳት መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ

ነገሮች ዙሪያ ለሚመለከተው ክፍል በተደጋጋሚ በቃል ቢጠየቅም ምንም ዓይነት መረጃ ከክልሎች እንደማይተላለፍ በተጨማሪም ባለስልጣኑም መድኃኒትን በተመለከተ ለባለስልጣኑ መረጃ መተላለፉን በተሟላ መልኩ እንደማይከታተልና መኖንም በተመለከተ ሙሉ በሙሉ እንደማይከታተል ለማወቅ ተችሏል፡፡

161. ስለሁኔታው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በአጠቃላይ በመድኃኒትና በመኖ መረጃ ዙሪያ ክልሎች እንዲልኩ የማድረግ ክፍተቶች እንዳሉ፣ ክልሎች ለባለስልጣኑ መላክ እንዳለባቸው አዋጁ ግዴታ ቢያስቀምጥም በመድኃኒት ዙሪያ በመጀመሪያ ደረጃ ለሁሉም ክልሎች ሰርኩላር እንደተላከና፣ የተለያዩ መድረኮችንም አዘጋጅተው በወርክ ሾፕ እና በሴሚናር የግንዛቤ ማስጨበጫ እንደሰጡ፣ ለወደፊት ግን ስርዓት ዘርግተው እንዴት መስራት እንዳለባቸው በመነጋገር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን አቋቁመው ለመስራት እንዳቀዱ፣ በዚህ ዙሪያ ክልሎችም የራሳቸው የሆነ መዋቅር እንደሌላቸውና በተደራቢነት ሰርተው ሲልኩ እንደነበረና ተጠያቂ የሆነ ራሱን የቻለ የክልል አካል አለመኖሩን እንዲሁም መኖንም በተመለከተ ከክልል የተላከ አንድም መረጃ አለመኖሩንና ስርአቱም እንዳልተዘረጋ ባለመደረጉም የመረጃ ክፍተት እንደፈጠረባቸውና መኖና መድኃኒትም በአንድ ዓይን መታየት እንደሌለበትና በመኖ ላይ ብዙ እንዳልተሰራ፣ ነገር ግን ሀገራዊ መረጃ ቢያስፈልግም በክልሎች ላይ ይህንን የሚሰራ አካል ባለመኖሩ አለመሰራቱን፣ ለወደፊት ግን ወደዚህ ስራ እንደሚገቡ ገልፀዋል፡፡

## <u>ባለስልጣኑ በናርኮቲክና በሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፣</u>

162. ባለስልጣኑ በእንስሳት ህክምና ጥቅም ላይ የሚውሉ ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡

163. ባለስልጣኑ በእንስሳት ህክምና ጥቅም ላይ የሚውሉ ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ሪፖርት እንደማያደርግ እንዲሁም ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችና ንጥረ ነገሮች ዙሪያ ከየቦታው የሚላኩ ሪፖርቶችን ሪከርድ መያዝ እና ወደ ምግብ ፣መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን 1 ቅጂ ሪፖርት ለመላክ በ2007 ዓ.ም አቅዶ ስለመከናወኑ ያልተገለፀ መሆኑ፣

164. ይህም በመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒት ፍላጎትና አቅርቦት ለማጣጣም ችግር እንደሚፈጥር ማለትም ዘርፉ ለህገ-ወጥ አሰራር የተጋለጠ በመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ የናርኮትክ ቦርድ የሀገሪቱን አመታዊ ፍላጎትና ፍጆታን በመጠየቅ ፈቃድ

የሚሰጥ በመሆኑ  በአሰራሩ ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ለኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የስራ ኃላፊዎች የገለፁ መሆኑ፣

165. ስለሁኔታው የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች/እንደማስታገሻ የሚታዩ ሲሆኑ/ በሀገራችን ደረጃ ለእንስሳት መድኃኒትነት ጥቅም ላይ እየዋሉ እንዳልሆኑ፤ በዚህ ዙሪያ የተመዘገበ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ በባለስልጣኑ ባለመኖሩ ምክንያት ለኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ሪፖርት እንዳልተደረገ እነዚህ መድኃኒቶች በእኛ ሀገር የተለመዱ አለመሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

## <u>ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር ዘርፉን አስመልክቶ የመግባቢያ ሰነድ (MOU) ስለመፈራረሙ በተመለከተ፤</u>

166. ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመሆን በክልል ተሻጋሪ የመድኃኒትና መኖ አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይ ባለፈቃዶች እና በችርቻሮ ንግድ እንዲሁም በህገ-ወጥ መድኃኒትና የመኖ ዝውውር ላይ የመግባቢያ ሰነድ (MOU) ሊኖረው ይገባል፡፡

167. ሆኖም በክልሎች ውስጥ አዲስ አበባን ጨምሮ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ችርቻሮ ንግድና ዝውውርን መቆጣጠር እጅግ አስቸጋሪ መሆኑና ባለስልጣኑም በተለያየ መንገዶች የሚደርስባቸው በክልሎች አከባቢ የሚያጋጥሙ ህጋ ወጥ ድርጊቶችን በተገቢው ሁኔታ ለፍትህ ለማቅረብ የስልጣን ወሰኑ ስለማያስችለው ብቻ ለክልሉ አሳልፎ ቢሰጥም ክልሎቹ በቸለልተኝነት በማለፍ ለጉዳዩ ትኩረት ሳይሰጥ እንደሚቀርና ወንጀለኞቹም ከቅጣት እንደሚያመልጡ፣

168. በሌላ በኩል ችርቻሮን ጨምሮ ለማንኛውም የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ንግድ ላይ ለሚሰማሩ ድርጅቶች መመዘኛ የሚያገለግል የብቃት መመዘኛ መመሪያ አዘጋጅቶ ለክልሎች ቢላክም መመሪያውን አምኖበት ከመቀበል አንስቶ  ስራውን በአግባቡ በመመሪያው መሰረት የመስራት ችግር መኖሩ እና ለባለስልጣኑ መረጃ የማስተላለፍ ግዴታቸውን ባልወጡትም ላይ በመመሪያው መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃም አለመውሰዱ፣

169. አንደዚሁም በባለስልጣኑ እና በክልል አካላት መካከል ያለመናበብ ችግር  በመኖሩ ፈቃዳቸውም ለችርቻሮ ብቻ ሲሆን እነዚህ ድርጅቶች ግን በተቃራኒው ጨረታን ጨምሮ በሌሎች የጅምላ ንግድ ስራዎች ላይ እንደሚሳተፉ ባለስልጣኑም በእነዚህ ህገ ወጥ ነጋዴዎች ላይ በህጉ መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዳይወስድ የብቃት ማረጋገጫቸው ከክልል በመውሰዳቸው እና ባለስልጣኑም ያገኘውን ማስረጃ አቀናብሮ ለክልል ተቆጣጣሪ አካላት በማስረከብ ራሳቸው እርምጃ እንዲወስዱ የሚያደርግ አስገዳጅ የሆነ ስምምነት በባለስልጣኑና

በክልሎች መካከል አለመኖሩ፣ በመጨረሻም በክልሎች ውስጥ የእንስሳት መድኃኒትና አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ያልተቋቋመ መሆኑና ስራው በተለያዩ ሴክተሮች ውስጥ ተበታትኖ የሚሰራ በመሆኑና አብዛኞቹ ክልሎች ደግሞ ጭራሹን ለስራው ባለቤት ያልሰጡትና ጉዳዩ የባለስልጣኑ ብቻ አድርገው የማየት አመለካከት እንዳለ ከባለስልጣኑ በተሰጠ መግለጫ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## ባለስልጣኑ በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን ሊያግዙ የሚያስችል የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት ተግባራዊ ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ፤

170. ባለስልጣኑ ባለፈቃዶች በተሰማሩበት በእንስሳት መድኃነትና መኖ አምራችነት፣ጅምላ አከፋፋይነት፣ላኪነትነ አስመጪነት ዘርፍ ላይ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

171. ይሁን እነጂ በኦዲቱ ወቅት 6 ድርጅቶች (ኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ ፤ኀናፍር እና ልጆቹ የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት ፤ ማርቆስ ኃ.የተ.የግል ማ. የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት ፤የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮረፖሬሽን ፤ ኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ እና ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት) የቅርንጫፍ ጽ/ቤት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ፤የባለስልጣኑ የላብራቶሪ አገልግሎት አለመጀመሩን በተመለከተ፤ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮቸን ከመድኃኒት መሸጫ መደብር ውስጥ መሸጥን በተመለከተ፤ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን የእንስሳት መድኃኒቶች በባለስልጣኑ የአወጋገድ መመሪያ መሰረት እንዲወገድ አለመደረጉን በተመለከተ፤ የመረጃ አቅረቦትን ና የመድኃኒት ምዝገባ መዘግየትን ክትባቶችን ወደ ውጭ ለመላክ ያሉ ችግሮች በተመለከተ በተለያየ ጊዜ የቃል እና የፅሁፍ ቅሬታ ቢያቀርቡም ምላሽ ያላገኙ መሆኑን በተደረገላቸው ቃለመጠይቅ የገለጹ መሆኑን፤

172. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ባለስልጣኑ ባለፈቃዶች በተሰማሩበት በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አምራችነት ፣ ጅምላ አከፋፋይነት ፣ ላኪነት እና አስመጭነት ዘርፍ ላይ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት የዘረጋ ሲሆን ተገልጋዮች የሚያቀርቡት ቅሬታ ፈጣንና ትክክለኛ ምላሽ እንዲያገኙ ከሌላ መ/ቤት ማለትም ከኢትዮጵያ ምግብ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የቅሬታ አቀባበል እና ግብረ መልስ አሰጣጥ መመሪያ እንደሞዴል በማየትና ወደራሳቸው በማምጣት ለጊዜው እየተገለገሉበት ሲሆን ቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓቱም ተገልጋዮች ለሚያቀርቡትን ቅሬታ የቅሬታ መቀበያ ፎርም የተዘጋጀ መሆኑንና በቀረበው ቅሬታ ላይ እንደአስፈላጊነቱ ከባለሙያና ከሚመለከታቸው ጋር የተለያዩ መረጃዎችና ማስረጃዎች ከተሰበሰበ በኋላ

በአገልግሎት አሰጣጥና በቅሬታ ማስተናገጃ የተሰጠ የውሳኔ ሃሳብ ለዋና ዳይሬክተር ቀርቦ ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን፤ ተገልጋዩም ቅሬታ ማቅረብ ሲፈልግ ቅሬታውን የትና እንዴት ማቅረብ እንዳለበት እንዲሁም ፎርሙን ከየት ማግኘት እንዳለበት ማሟላት ያለበት በባለስልጣኑ ግብ ውስጥ በተሰቀለ ታፔላ ተፅፎ እንደሚገኝ ነገር ግን ባለስልጣኑ ቅሬታን ለመቀበልና አስተዳደራዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የፀደቀ መመሪያ የሌለው መሆኑንና ረቂቅ መመሪያውን አፀድቆ ስራ ላይ ለማዋል በሂደት ላይ እንደሆነ ከአገልግሎት አሰጣጥና ቅሬታ ማስተናገጃ ክፍል የስራ ኃላፊ በተሰጠ መግለጫ ገልፀዋል፡፡

173. ይህንን በተመለከተ በባለስልጣኑ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የመግባቢያ ሰነድን በተመለከተ በአዋጅ ቁ 728/2004ዓ.ም. ለክልሎች የተሰጠ ስልጣን ስላለ በአዋጁ መሰረት እንደሚሆን እንዲሁም የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት በመመሪያ ደረጃ አለማዘጋጀቱን በተመለከተ በባለስልጣኑ በመሄድ የቅሬታ አሰጣጥ ስርዓት እንደተዘረጋ ነገር ግን የአወጋገድ መመሪያ ሳይዘጋጅ ቢዘገይም ለጠየቁት እስከ አዳማ ድረስ በመሄድ ጊዜ ያለፈበት መድኃኒቶች እንደተወገደላቸው ተገልጿል፡፡

174. ይሁንእንጂ በክልል ተሻጋሪ የመድኃኒትና መኖ አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይ ባለፈቃዶች እና በችርቻሮ ንግድ እንዲሁም በህገ-ወጥ መድኃኒትና የመኖ ዝውውር ላይ በአዋጅ ቁጥር728/2004ዓ.ም ከክልሎች ጋር በጋራ የሚያሰራ አለመኖሩ ለመረዳት የተቻለ ሲሆን፤በባለስልጣኑ የቅሬታ መቀበያ ስርዓቱም ቢኖር ወጥ በሆነ መልኩ ሁሉም እንደማይስተናገድ ተገንዝበናል፡፡

## ባለስልጣኑ መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት ስለመመረቱ፤ ስለመከማቸቱና ስለመጓጓዙ በተመለከተ ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፤

175. ባለስልጣኑ መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፤ መከማቸቱንና መጓጓዙን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

176. በአዋጅ ቁጥር 728/2004 መሰረት ባለስልጣኑ የእንስሳት መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፤ መከማቸቱንና መጓጓዙን በተሟላ መልኩ የተቆጣጠረ አለመሆኑ፣

177. ይህም በመሆኑ፡ባለስልጣኑ በ2006 ዓ.ም የመልካም አመራረት ቁጥጥር ለማካሄድ የታሰበባቸው ተቋማት(GMP) 10 የነበሩ ቢሆንም በአፈፃፀም ሪፖርት ላይ የዕቅዱን 10 % ብቻ መከናወኑ፤እንዲሁም በ2007 በጀት ዓመት መልካም አመራረት ምልከታ በተመለከተ በ30 የእንስሳት መኖ አምራች ድርጅቶች ለማካሄድ አቅዶ በ1 (3.3%)ድርጅት ብቻ ማካሄዱ፣

በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በአካል ከታዩት 7 የመኖ አምራች/ማቀነባበሪያ/ ድርጅቶች ውስጥ ባለስልጣኑ አንድ ድርጅት(ኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ) ከ2006-2008ዓ.ም ተቆጣጥሮ እንደማያውቅ፣ 3 ድርጅቶችን ( ቃሊቲ ፤ ፒካና ፤ቦራ የእንስሳት መኖ ማደራጃ ኃ/የግ/ማህበር) ደግሞ ባለስልጣኑ መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፤ መከማቸቱንና መጓጓዙን በቋሚነት የሚቆጣጠርበት ስርዓት እንዳልዘረጋ እንዲሁም በሌሎች 3 ድርጅቶች ደግሞ (አቃቂ፤ኢትዮ ፊድ እና አለማ ካውዳይስ የእንስሳት መኖ ማደራጃ ኃ/የግ/ማህበር ድርጅቶች) የመኖ አመራረት እና መከማቸቱን በተመለከተ ቁጥጥር ቢያደርግም የመኖ አጓጓዝን በተመለከተ ቁጥጥር አድርጎ እንደማያውቅና አልፎ አልፎ ለኢንስፔክሽን በሚመጡበት ጊዜ የአመራረት ሂደትን ብቻ የሚያዩበት ሁኔታ እንዳለ በተጨማሪም አንድ ጊዜ በአፍላቶክሲን ምክንያት የመኖ ግብአቶችን እንደ ናሙና በመውሰድ ጥናት ያደረገ ቢሆንም ውጤቱን እስካሁን አለማሳወቁና በቋሚነት ክትትል ባለማድረጉ የሚያመርቱአቸው መኖዎች የጥራት ደረጃና ጤናማነት በየጊዜው ለማሻሻልና ለመፈተሽ እንዲሁም ያሉበትን ደረጃ ለማወቅ እንዳላስቻላቸው የገለፁ መሆኑ፤

178. እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት የታዩት ሁሉም የመኖ አምራች ድርጅቶች ማለትም 9ኙም መኖን ለማምረት የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ የመኖ ግብዓቶች ከተገኙበት ቦታ ሁሉ በመግዛት መኖ የሚያመርቱ ቢሆንም የመኖ ድህንነትንና ጥራትን ለማስጠበቅ እንዲያስችል አምራቾች ጥራቱን የተጠበቀ የመኖ ግብዓት ስለመጠቀማቸው እንዲሁም የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች/ግለሰቦች/ ድህንነቱ የተጠበቀ ግብዓት ስለማቅረባቸው እና የመኖ አምራች ድርጅቶችም ደህንነቱ የተጠበቀ ግብዓት ከታወቀ ድርጅት ስለመግዛታቸው ባለስልጣኑም በዚህ ዙሪያ ክትትል እያደረገ አለመሆኑ የታወቀ ሲሆን፣ከዚህም ሌላ ባለስልጣኑ በ7 የመኖ አምራች ድርጅቶች ላይ እየተመረቱና ለህብረተሰቡ እየቀረቡ ያሉትን የተለያዩ ዓይነት መኖዎችን አስመልክቶ የባለስልጣኑ ባለሙያዎች ቡድን በተለይም ከጥሬ እቃ መረከብ ጀምሮ ምርቱ ተመርቶ ለተጠቃሚዎች እስከሚቀርብ ድረስ ያለውን የምርት ሂደት ውስጥ ከጥራትና ደህንነት አኳያ የታዩትን አሉታዊ አሰራሮችን በተመለከተ በባለስልጣኑ ምክረ-ሀሳብ የተሰጠባቸው ጉድለቶች መካከል የምርት ክፍል ዋና ኃላፊና የጥራት ቁጥጥር ክፍል ኃላፊነት መስፈርት የሚያሟሉ የመኖ ባለሙያዎች ያለመቅጠር፤ የማሸጊያና የምርት ማሳወቂያ አሰራር(Labeling) ያልተዘረጋ መሆኑ፤ ንፅህናው የተጠበቀ አመራረትና ጥራቱ ያልተረጋገጠ የመኖ ግብዓት የመጠቀም ሂደት መኖሩ የሚሉ መሰረታዊ የብቃት መስፈርቶች መሆናቸው እና ድርጅቶች በመጀመሪያ ወደስራ ከመግባታቸው በፊት ማሟላት የሚገባቸው ሆነው ሳለ የብቃት ማረጋገጫ አውጥተው ወደስራም ከገቡ በኋላ ክፍተቶቹ የቀጠሉ መሆኑና ባለስልጣኑም ከምክረ-ሀሳብ በዘለለ አስገዳጅ የሆነ እርምጃ አለመውሰዱ ታውቋል፡፡

179. አዋጅ ቁጥር 728/2004 ባለስልጣኑ መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፤ መከማቸቱንና መጓጓዙን ሊቆጣጠር እንደሚገባ ቢደነግግም ባለስልጣኑ ከኢትዮጵያ የምግብ መድኃኒት ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በጋራ የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነት ከግብዓት አቅራቢዎች ጀምሮ ወጥነትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ባለመስራቱ መነሻው ፈንገስ ወይም ሻጋታ የሆነ አፍላቶክሲን የተባለ መርዛማ ኬሚካል በወተት ላይ እንደተፈጠረና ይህ የአፍላቶክሲን መርዝ በተለይ የግብርና ውጤቶች እና የእንስሳት መኖ መነሻ በማድረግ ችግሩ ሊፈጠር እንደሚችል አለም አቀፍ ጥናቶች የሚያሳዩ መሆኑ፣

180. እንዲሁም ከኢትዮጵያ የምግብ መድኃኒት ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን በኩል በ2008ዓ.ም በወተት ምርት ላይ የተካሄደ የአፍላቶክሲን ጥናት ሪፖርት የሚያመለክት ሲሆን፤ የጥናቱ ሪፖርት እንደሚያሳየው በናሙና ከተመረጡ 18(አስራ ስምንት) የወተትና ወተት ተዋፅኦ አቀነባባሪ ድርጅቶች ሦስት ዓይነት ናሙናዎችን ማለትም ጥሬ ወተት፤ ያለቀለት ወተት ከማምረቻው እና ያለቀለት ወተት ከገበያ በድምሩ 50 ናሙናዎችን በመሰብሰብ የኮዴክስ ኤልምታሪየስ ደረጃን ማለትም 0.5μg/L(Maximum Limit) በመጠቀም ጥናቱን ያከናወነ ሲሆን በጥናቱ ውጤት መሰረት 16.67% የጥሬ ወተት፤ 12.5% ያለቀለት ወተት ከማምረቻው እና 31.25% ያለቀለት ወተት ከገበያ ናሙናዎች ከ0.5μg/L በላይ የአፍላቶክሲን M1 ይዘት ያላቸው ሆነው መገኘታቸው፣

181. እንዲሁም ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር በማያያዝ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ዙሪያ ስራውን መስራት ባለመቻሉ ይህ አፍላቶክሲን የተባለው መርዛማ ኬሚካል ሊከሰት እንደቻለ የምግብ መድኃኒት ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን የስራ ኃላፊዎች ባቀረቡት ማስረጃና በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ መታወቁ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በ15/2/2008ዓ.ም መኖ እና የወተት ናሙና ተወስዶ ሁሉም ናሙናዎች በአፍላቶክስን እንደተጠቁ ጥናቱ እንደሚያሳይ በተለይ ደግሞ የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ላይ ችግሩ እንደከፋና ወተት ላይ የታየውም ምንጩ የሚመገቡት መኖ እንደሆነ ጠቅሰው ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ለማዘጋጀት እንዲሁም በታንዛኒያ በሚደረገው 4ኛው ግሎባል የእንስሳት ጤና ኮንፍሬንስ ለመዘጋጀት እንዲረዳ ለባለስልጣኑ እና ለ6 መኖ ማቀነባበሪያ ድርጅቶችች ማሳወቃቸው የታወቀ ሲሆን፤

182. በተጨማሪም ባለስልጣኑ የካቲት6/2008ዓ.ም በሀገሪቱ በቅርብ ጊዜ ተከስቶ የነበረው የወተት አፍላቶክሲን ችግር መንስኤው በዋናነት ከመኖ በተለይም ከፋጉሎ መኖ አከመቻቸት ችግር ጋር በተያያዘ መሆኑን መረጃዎች እንደሚጠቅሱ እና ይህንንም ችግር ለመቅረፍ ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ለማካሄድ የፋጉሎ አፈላቶክሲን ችግር ለመቅረፍ የምክክር

ዝክረ ተግባር በስልጠና መልክ እንዲሰጥ በጀት በማስፈቀድ ላይ የነበረ ቢሆንም ስልጠናው ስለመሰጠቱ ከባለስልጣኑ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡በዚህም ዙሪያ ባለስልጣኑ የጥናቱን ሪፖርት እንዲያቀርብ በተደጋጋሚ በኦዲት ቡድኑ በቃልና በፁሑፍ ቢጠየቅም ጥናቱን ያላቀረበ መሆኑ፣

183. ይህንን በተመለከተ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ባለስልጣኑ እንዲቋቋም ካስፈለገበት ምክንቶች መካከል አንዱ በገበያ ላይ የዋለው የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነት በማነስ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ የእንስሳት በሽታዎችን በመከላከል የእንስሳት ጤንነትን በመጠበቅ ምርታማነትን ማሳደግ ሲሆን ፤በዚህም መሰረት ባለስልጣኑ በምግብ፣መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን አስተባባሪነት እነርሱ የወተት አፍላቶክስን ባለስልጣኑ ደግሞ የመኖ አፍላቶክሲን ለማጥናት በተስማሙት መሰረት ጥናት እንዳካሄዱ እና በጥናቱ ፕሮቶኮል መሰረት ከባለስልጣን ዋና መ/ቤት ኮር ዳይሬክቶሬቶችና ከእንስሳት ውጤቶች መድኃኒትና መኖ ጥራት ምርመራ ማዕከል የተወጣጡ ባለሙያዎች ጥናቱን አካሂደው እንደነበረና ናሙናዎችም ከመኖ ማቀነባበሪያዎች፣ከዘይት መጭመቂያዎችና ከወተት እርባታ ቦታዎች እንደተሰበሰቡ በዚህም መሰረት የተሰበሰቡ ናሙናዎች በላብራቶሪ አማካይነት ውጤታቸው ከታወቀ በኃላ ናሙናውን ከሰበሰቡ ባለሙያዎች ጋር የምግብ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በማነፃፀር ለማየት ተሞክሮ እንደነበር ይሁን እንጂ የወተት አፍላቶክስን ውጤት ከመኖ አፍላቶክስን ጋር የተያያዘና የሚናበብ መሆን ሲገባው ውጤቱ በጣም የተራራቀ በመሆኑ ችግሩ ባለስልጣኑ አዲስ ከመሆኑ የተነሳና አዲስ የተቀጠሩ ባለሙያዎች ናሙና አሰባሰብ ዜዴ ላይ ልምድ ያካበቱ ካለመሆናቸው የተነሣ በተወሰኑ ናሙናዎች አሰባሰብ ዙሪያ ችግር ስለነበረ በተጨማሪ ናሙናዎች ተሰብስበውና ውጤቱ ከቀረበ በኃላ በባለሙያዎች መድረክ ከታዬና ከፀደቀ በኃላ ለወደፊት ውጤቱን የሚያሳውቁ መሆኑን በመግለጫ አሳውቀዋል፡፡

184. በኢንስፔክሽን ዳይሮክቶሬት አማካኝነት በየጊዜው ድንገታዊና እንዲሁም በማሳወቅ በድርጅቶቹ ላይ ቁጥጥር የሚያደርግ ቢሆንም መደበኛ ያልሆነና በተቆጣጠረውም መሰረት ለድርጅቶቹ ግብረ መልስ በማዘጋጀት እንዲያውቁት የማያደርግ መሆኑ እንዲሁም ክልል ተሻጋሪ የእንስሳት መድኃኒትና መኖን ለሚያስተዋውቁ እና የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎችን መቆጣጠር እንዳልጀመረ ለማወቅ ተችሏል፡፡

185. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 12 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች፣ 6 ጅምላ አከፋፋዮች፣3አምራች ድርጅቶች እንዲሁም 6 መኖ አምራች ድርጅቶች እና 2 የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪና ላኪ ድርጅቶች ውስጥ 10 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ፣ 2 የመድኃኒት አምራቾች እንዲሁም 6 የመኖ አምራች ድርጅቶችና 2የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች አስመጪና ላኪ ድርጅቶች ባለስልጣኑ ቁጥጥር ቢያደርግባቸውም

በየዓመቱ ለቅድመ ፈቃድ እድሳት ቁጥጥር እንደሆነና አልፎ አልፎም የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በራሳቸው ፕሮግራም ሳያሳውቁ ድርጅቶቹ ድረስ በመምጣት ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግ ቢሆንም መደበኛ በሆነ መልኩ የማያደርግ እና በተቆጣጠረው መሰረት ለድርጅቶቹ ግብረ መልስ በማዘጋጀት እንዲያውቁት የማያደርግ መሆኑ ታውቋል፡፡

186. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ባለስልጣኑ መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፤ መከማቸቱንና መጓጓዙን መቆጣጠርን በተመለከተ በሀገሪቱ የተከሰተው የአፍላቶክሲን ችግር በመኖና በመኖ ጥሬ እቃ ጥራትና ደህንነት መጓደል ነው ብለው ቢያምኑም ይህን ክስተት እንደሀገር ለመቆጣጠር ለባለስልጣኑ ብቻ የሚተው አለመሆኑንና በዚህ ዙሪያ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ስራውን መስራት እንደሚጠበቅበት እንደሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መስራት ያለባቸው መሆኑን፣

187. በተጨማሪም የበላይ የመንግስት አካላት የሚሰጡት የተሳሳተ መመሪያና ትዕዛዝ አሰራሩን እንዳበላሸው፡፡ በተለይም መኖ ከሀገር እንዳይወጣ እገዳ በመጣሉ ለረጅም ጊዜ በመጋዘን ታሽገው ለሻጋታ የተጋለጡ መኖዎች ለሀገራዊ ፍጆታ የሚውልበትን ሁኔታ የጨመረው ሲሆን፤ ሆኖም እገዳው ቢነሳ ችግሩን ያቃልለዋል ብለው እንደሚያምኑ፡

188. የመኖ ግብዓት አቅራቢ ድርጅቶችን በተመለከተ እንደባለስልጣን የግብዓት አያያዝን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች እየተሰራ መሆኑን ነገርግን ለግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች የሰጡት የብቃት ማረጋገጫ እንደሌለና፡፡ እያንዳንዱን የግብዓት አቅራቢ ድርጅት/ግለሰብ እንደ ሀገረ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ መሆኑን እና ይህም ኃላፊነት ለባለስልጣኑ ብቻ የሚተው አለመሆኑን በተጨማሪም በባለስልጣኑ መደበኛ የሆነ ቁጥጥር ስላለመኖሩና በተቆጣጠረውም መሰረት ለድርጅቶቹ ግብረ መልስ በማዘጋጀት እንዲያውቁት አለማድረጉን ገልፀዋል፡፡

## ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ለሚያመርቱ፣ በሀገር ውስጥም ሆነ ወደ ውጭ ሀገር የሚልኩ ድርጅቶችን የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎችን መከታተሉን በተመለከተ፣

189. ባለስልጣኑ ክልል ተሻጋሪ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ለሚያመርቱ፣ ለሚያከፋፍሉ፣ ለሚያስተዋውቁ፣ መድኃኒትና መኖ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገቡና ወደ ውጭ የሚልኩ አካላትን እና የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎችን ሊቆጣጠር እና በተቆጣጠረውም ላይ ግብረ መልስ በማዘጋጀት እንዲያውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡

190. በዚህ ዙሪያ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ባለስልጣኑ ክልል ተሻጋሪ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ለሚያመርቱ፣ለሚያከፋፍሉ፣ ለሚያስተዋውቁ፣መድኃኒትና መኖ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገቡና ወደ ውጭ የሚልኩ አካላትን እንደሚቆጣጠር ሆኖም ግን የባለስልጣኑንም ሆነ የድርጅቶችን የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎችን እንደማይቆጣጠርና የመኖ አምራቾችን የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪ መጀመሪያ ፈቃድ ሲሰጥ ክትትል እንደሚያደርግ ከዚያ ውጭ የመኖ አከፋፋይ ድርጅቶች ቁጥጥር የሚጠበቀው በባለስልጣኑ ላብራቶሪ መሆኑን፤ይህም የሆነው የባለስልጣኑ ላብራቶሪ ባለመጠናቀቁ መሆኑንና በተጨማሪም የባለስልጣኑ የኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መግለጫ የእንስሳት መድኃኒቶችን በማስተዋወቅ በኩል ምንም ዓይነት ፈቃድ ያወጡ አካላት ባለመኖራቸውና በህገወጥ ቁጥጥሩም ወቅት ስላላጋጠማቸው በዚህ ረገድ እስካሁን የተሰራም ሆነ የተደረገ ነገር አለመኖሩን እንዲሁም በጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎች ዙሪያ የመድኃኒት አምራች ተቋማት ውስጥ የምርት ጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪ ቢኖራቸውም አጠቃላይ የመልካም አመራረት ግምገማ ካልሆነ በስተቀር የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪያቸውን ለይተው ቁጥጥር እንደማያደርጉ ገልፀዋል፡፡

191. ይህም በመሆኑ ባለስልጣኑ ሕይወት እንድኖረው አለማድረጉን እንዲሁም በየድርጅቶቹ ላይ ክትትል አለመደረጉ ችግር ሊያስከትል እንደሚችል የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

192. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ክልል ተሻጋሪ የእንስሳት መድኃኒትና መኖን ለሚያስተዋውቁ እና የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎችን መቆጣጠርን በተመለከተ ባለስልጣኑ መኖን የሚያስተዋውቁትንና የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎችን እንደማይቆጣጠር እንዲሁም ላብራቶሪን በተመለከተ የአቅም ክፍተት/ውስንነት በመኖሩ ምክንያት መቆጣጠር እንዳልጀመረና የመኖና የመድኃኒት ተቋማትን ኢንስፔክት በሚደረግበት ሰዓት ያሉትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት ለድርጅቶቹ ግብረ መልስ በማዘጋጀት መስጠት እንዳልጀመሩ በተጨማሪም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ስህተት ፈጥሮ ግብረ መልስ ያልተሰጠበት ሁኔታ አለመኖሩን ነገር ግን ድንገተኛ ፍተሻ ማጠናከሩ የተሻለ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

# ክፍል ሦስት
# የመደምደሚያ ሃሳቦች

193. የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ እና የመኖ አምራቾች፣ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስመጪዎች፣ ላኪዎች፣ አከፋፋዮችን ለመደገፍና ውጤታማ ለማድረግ በባለስልጣኑ እና በባለስልጣኑ ቅ/ፅ/ቤት የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን፤ የዚህ ክዋኔ ኦዲት ዓላማ የእንስሳት መድኃኒትና መኖን በተመለከተ ምዝገባ በማካሄድና የቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ደህንነቱና ጥራቱን የጠበቀ መኖ እንዲሁም ጥራቱ፣ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት ለተጠቃሚው እንዲደርሱ ድጋፍ ማድረጉን እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ አንፃር የአሰራር ስርዓቱ አፈፃፀምና ውጤታማነትን በተመለከተ የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ያሉበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

194. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒት ወይም በመኖ ንግድ ስራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች ወይም ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ቢሰጥም፤ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት በወቅቱ የምስክር ወረቀታቸውን ባለማደሱ፣ ባለማገዱ እና ባለመሰረዙ 3የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች በወቅቱ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ የተገኙ ሲሆኑ፣ እንዲሁም 6ቱ ደግሞ በቅጣት እድሳት የሚፈፅሙበት ጊዜ ያለፈ ቢሆንም ባለስልጣኑ እድሳት የፈፀመላቸው መሆኑ ፣

195. 7 መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጭ ድርጅቶች የፈቃድ እድሳት ክፍያ አለማከናወናቸውና 3ቱ የእንስሳት መኖ ድርጅቶች ደግሞ ፈቃድ ያወጡበትን የአገልግሎት ክፍያ አለመፈፀማቸው እንዲሁም ሌሎች 3 የእንስሳት መኖ አምራች ድርጅቶች እና 5 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ደግሞ እድሳት እንዳላከናወኑና ባለማሳደሳቸውም እንደተሰረዙ ይቆጠራሉ በማለት ባለስልጣኑ የወሰደው እርምጃ አለመኖሩ፡፡ ከነዚህ ድርጅቶች ውስጥ በኦዲቱ ወቅት ሲሰራ የተገኘ ድርጅት መኖሩ ከዚህም ሌላ አንዳንድ አስመጪዎች እየሰሩ ቆይተው ፈቃዳቸው መታደስ ሲገባው እንደ አዲስ ለሁለተኛ ጊዜ ፈቃድ የተሰጣቸው ድርጅት መኖራቸው፣ 2 የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጪ ድርጅቶች ደግሞ የ2006 ፈቃድ እድሳት የተፈፀመበት ማስረጃ ያልተገኘ መሆኑ፣

196. ከዚህም ሌላ 3 የእንስሳት መኖ አምራች / ማቀነባበሪያ ድርጅቶች / የማምረት አቅማቸው ከፍተኛ ቢሆንም ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ያልወሰዱ ሲሆን እንዲሁም ከ3 የመድኃኒትና የክትባት አምራች ድርጅቶች ውስጥ 2ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው እየሰሩ መሆኑ፤

197. ባለስልጣኑ ማንኛውም ሰው የሙያ ፈቃድ የተሰጠው የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በሌለበት የእንስሳት መድኃኒት ቤት ንግድ እንዳይካሄድ በተሟላ መልኩ እንዳልተቆጣጠረ እና በቁጥጥሩም ወቅት በታዩት ክፍተቶች ላይ እርምጃ አለመውሰዱን በኦዲቱ ወቅት ከታዩ 8 የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጪ እና የመኖ ማቀነባበሪያ ድርጅቶች ውስጥ 8ቱም ከባለስልጣኑ ፈቃድ የወሰዱ ድርጅቶች በሙሉ ከመመሪያ ውጭ እንደሚሰሩ እና ባለስልጣኑም በዚህ ዙሪያ ያልጠየቃቸው ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 2ቱ በመድኃኒት ባለሙያዎች ስራውን እንደሚያከናውኑና እስካሁን ድረስ ቅጥር ያልፈፀሙ ሲሆን ፣ አንድ ድርጅት ደግሞ የባለሙያዎችን የቅጥር ደብደቤያቸውን ከብቃት ማረጋገጫ ሰሪትፊኬት ጋር በማያያዝ ለባለስልጣኑ አለማቅረቡ እንዲሁም 5ቱ የእንስሳት መኖ ማቀነባባሪያ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩት የድርጅቱ ባለሙያዎች ከባለስልጣኑ የተሰጠ ጊዜያዊ የሙያ ፈቃድ ሰርተፍኬት እንደሌላቸው እንዲሁም ባለስለጣኑም ኢንዲያወጡ አለመጠየቁንና ለማውጣት ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ያላደረጉ መሆኑ፤

198. ባለስልጣኑ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ህክምና መሳሪያ አስመጪ ወይም ላኪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው በዘርፉ እንዳይሰማራ ለመቆጣጠር የሚስችል የአሰራር ስርዓት ቢዘረጋም በተሟላ መልኩ ያልተቆጣጠረ እና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

199. በኦዲቱ ወቅት 3 የመኖ ንጥረ ነገሮች ወይም ግብዓቶች ንግድ ድርጅቶች ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኙ መኖ፣የመኖ ንጥረ ነገሮች ወይም የመኖ ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቡ ሲሆን 8 የእንሰሳት መድኃኒት አስመጪ፣3 የመድኃኒት አምራቾች እና 2 የመኖ አምራች ድርጅቶች ፈቃድ ለሌለው ሰው መድኃኒት እና መኖ አከፋፍለው ቢገኙም ባለስልጣኑ እርምጃ ያልወሰደ ሲሆን በተጨማሪም አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው ከ2006-2008ዓ.ም በእንስሳት መድኃኒት እና በመኖ ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው የተገኙ ድርጅቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፣

200. ባለሰልጣኑ ለእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሳሪያዎች፤ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተቋማት ምዝገባና ፈቃድ ለመስጠት እንዲሁም ለውጭ አገር አምራች ኩባንያዎች ለእንስሳት መድኃኒት የመልካም አመራረት ተሞክሮ ምልከታ ለማድረግ በደንብ ቁጥር 325/2006 በወጣው ተመን መሰረት በተሟላ መልኩ በወቅቱ የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈፅሙ ያላደረገ መሆኑ፣

201. ባለስልጣኑ ለእንሰስሳት ለውጭ ጥገኛ ህክምና ወይም ለእንስሳት በሽታ አስተላላፊ ተባዮች መቆጣጠሪያ አገልግሎት የሚውሉ ንጥረ ነገሮችንና ውህዶችን በተማሏ መልኩ ያልመዘገበ እና ያልተቆጣጠረ መሆኑ እንዲሁም በአገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚመጡ

የእንስሳት መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎችን በከፊል ገምግሞ የመዘገበ ሲሆን ፣የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ግን ሙሉ በሙሉ ገምግሞ ያልመዘገበ መሆኑ፣

202. እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት ከታዩ 3 የእንስሳት መድኃኒት አምራች ድርጅቶች 3ቱም አስገምግመው ሳያስመዘግቡ አምርተው የሚሸጡ መኖራቸው እንዲሁም በአንድ አስመጪ እና በአንድ ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ያልተመዘገበ መድኃኒት ሲሸጥ መገኘቱ በተጨማሪም በ3 የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች ውስጥ በተደረገው ድንገተኛ ኢንስፔክሽን በባለስልጣን መስሪያቤቱ ያልተመዘገበ መድኃኒት የተገኘ መሆኑ በተጨማሪ 5 ድርጅቶች የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮችን ሳያስመዘግቡ ከውጭ ሀገር ያስመጡ ቢሆንም በድርጅቶቹ ላይ ምንም ዓይነት የፈቃድ እገዳ ወይም ስረዛ አለመደረጉ

203. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ የምስክር ወረቀት በከፊል በየ5ዓመቱ ቢያድስም በራሱ የምዝገባ መስፈርት በማዘጋጀትና አፀድቆ እየሰራ አለመሆኑ ነገር ግን በቀድሞ ጊዜ በኢትዮጵያ ምግብ፣መድኃኒትና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን በተዘጋጀ መመሪያ መሰረት የሚሰራ ቢሆንም በተሟላ መልኩ በምዝገባ መስፈርቶቹ መሰረት የማይሰራ መሆኑ፣

204. ከባለስልጣን መ/ቤቱ በእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ አስመጪነት ፈቃድ ከወሰዱ እና እስከ መስከረም 30/2009 ዓ.ም በባለስልጣኑ ዝርዝር ማስረጃ ውስጥ ከተካተቱ 30 ድርጅቶች ውስጥ 16ቱ የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ አስመጪ ድርጅቶች የመድኃኒት ሴሪትፍኬት ጊዜያቸው አብቅቶ ለዕድሳት በሂደት ላይ ያሉ 57 ዓይነት መድኃኒቶች ያሉ ሲሆን እንዲሁም መድኃኒቶቹ የሴሪትፊኬት ጊዜያቸው ካበቃ ከ5 ወር እስከ 6 ዓመት ቢሆንም ጊዜያዊ ሴሪትፍኬት እስኪሰጠቸው ድረስ መድኃኒቱን ከውጭ ሀገር አስገብተው በመሸጥ ላይ እንደነበሩ እና በኦዲቱ ወቅትም ሲሸጡ ነበረ ሲሆን ሌሎች ደግሞ እድሳት ቢያደርጉም የመድኃኒቶቹ ናሙና የላብራቶሪ ፍተሸ ያልተደረገ መሆኑ፣

205. ባለስልጣኑ ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝርን ያላዘጋጀ፣ መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በየዓይነታቸው ያልመደበ መሆኑ፣

206. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ አግባብ ላላቸው አካላት በተሟላ መልኩ ስልጠና ያልሰጠ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከታዩ 12 የመድኃኒት አስመጪ፣6 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች እና 3 የመድኃኒት አምራች ድርጅቶች ውስጥ ለ7 መድኃኒት አስመጪዎች፣ ለ1 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት እና ለ3 የመድኃኒት አምራች ድርጅቶች በመድኃኒት አያያዝ ፣ አከመቻቸት እና አጓጓዝ ዙሪያ ስልጠና ያልሰጠ መሆኑ፣

207. እንዲሁም በናሙና ለታዩ ለ 5 መኖ አምራች እና ለ2 የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጪና ላኪ ድርጅት በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ስልጠና ሰጥቶ የማያውቅ መሆኑ፤

208. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተሟላ መልኩ በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ ታውቋል፣

209. ባለስልጣኑ ከውጭ ሀገር መድኃኒት ለሚያስገቡ ለ21 እንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ በላብራቶሪ ሳይገመገምና ሳይረጋገጥ ለ280 ዓይነት መድኃኒቶች ጊዜያዊ ፈቃድ በመስጠት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረጉና ይሄ ጉዳይ ኦዲቱ እስከተጠነቀቀበት ጊዜ ድረስ የቀጠለ መሆኑ፤

210. ባለስልጣኑ የላብራቶሪና የክሊኒካል ጥናት በማደረግ የባህላዊ መደኃኒቶችን ደህንነት፤ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንድውሉ ያላደረገ መሆኑ፡፡

211. ባለስልጣኑ የተመዘገበ የእንስሳት መድኃኒት ከተስራጨ በኋላ ያስገኘውን ጠቀሜታና ያስከተለውን ጉዳት ለማወቅ የድህረ-ገበያ ቅኝት አድርጎ የማያውቅ መሆኑ እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት 15 የመድኃኒት አስመጪና አምራች ድርጅቶች ውስጥ 15ቱም ድርጅቶች የእንስሳት መድኃኒት በባለስልጣኑ ያስመዘገቡ ቢሆንም ባለስልጣኑ መድኃኒቶቹ ከተሰራጩ በኃላ የድህረ ገበያ ጥናት በመድኃኒቶቹ ላይ ማስደረግ ቢገባውም የድህረ ገበያ ጥናት አድርጎ የማያውቅ መሆኑ እና ድርጅቶቹም የፋርማኮቪጅላንስ ማስረጃ ለባለስልጣኑ አቅርበው የማያውቁና ባለስልጣኑም ጠይቋቸው የማያቅ መሆኑ፣

212. የእንስሳት መድኃኒት ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል እና የመድኃኒት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የሚያስችል ባለስልጣኑ የአሰራር መመሪያዎችን ያላወጣ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከታዩ ድርጅቶች ውስጥ 6 የመድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች፣ 5 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች እና አንድ አምራች ድርጅት ባለስልጣኑ የእንስሳት መድሃኒቶች ጥቅም ላይ ለማዋል ያወጣው መመሪያ እንደሌለ እና የእንስሳት መድኃኒት ጥቅም ላይ መዋሉን እንደማይከታተል እንዲሁም መመሪያ በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ስለማዋል ያከናወነው ተግባር አለመኖሩ እንዲሁም ከእንስሳት ሀኪም በተጨማሪ በሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ትዕዛዝ እና ያለመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶችን ዝርዝር በመመሪያ ያልወሰነ መሆኑን፤

213. በተጨማሪም የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸውን የእንስሳት መድኃኒቶች፤ መኖዎች ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮች አወጋገድን በተመለከተ ያወጣው መመሪያ እንደሌለ እንዲሁም አከባቢን በማይበክል መንገድ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን መቆጣጠር ያልጀመረ ሲሆን፣ በኦዲቱ ወቅት የታዩ 5 የእንስሳት መድኃኒቶች አስመጪ፣ 1 ጅምላ አከፋፋይ እና 2 አምራች ድርጅቶች መጋዘን ውስጥ ከ2006 ዓም ጅምሮ ጊዜ ያለፈባቸው የእንስሳት መድኃኒቶች ያሉ ሲሆኑ የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በቁጥጥር ጊዜ ቢያዩም በተጨማሪም ፎርም ቀርፀው በዝርዝር አሳውቁን ብለው ያሳወቁአቸው ቢሆንም ባለስልጣኑ የአወጋገድ መመሪያ እስኪያወጣ ድረስ ተለይተው እንዲቀመጡ ከማድረግ ውጭ

በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ ያልተደረጉ ሲሆን እንዲሁም ፡በኦዲቱ ወቅት ከታዩት 7 የመኖ አምራች እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪ ድርጅቶች ውስጥ 3ቱ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው የመኖ ንጥረ-ነገር እና መኖ ያላቸው ሲሆኑ እንዲሁም 4 ድርጅቶች ያስወገዱበት ሁኔታ ቢኖርም በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን ባለስልጣኑ ያልተቆጣጠረ መሆኑ ታውቋል፡፡

214. ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ደረጃዎች እና የእንስሳት መኖና የመኖተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኅንነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብና ተከታትሎ በማፀደቅ ስራ ላይ አለማዋሉ ታውቋል፡፡

215. እንዲሁም ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ አውጥተውና ሳያወጡ በተደጋጋሚ መኖና መኖ ግብዓት ወደ ውጭ ሀገር የሚልኩ ድርጅቶች ቢኖሩም ባለስልጣኑ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ወደ ውጭ ሀገር ለሚላኩ ለእንስሳት መኖዎች የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት እንዳልጀመረ ለማወቅ ተችሏል፡፡

216. ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ የመረጃ አያያዝ፣ልውውጥ እና አጠቃቀም ስርዓት ያልዘረጋ እና መረጃዎቹን በዳታ ቤዝ አጠናክሮ የማይዝ መሆኑ እንዲሁም ወቅታዊ የሆኑ የእንስሳት መዲኃኒትና መኖ መረጃዎችን በመደበኛነት ለባለሙያዎችና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚያስተላልፍበትን ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከታዩት ከ12 መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች፣ከ 6 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች፣ከ3 አምራች ድርጅቶች ውስጥ 6 መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች 3 ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር የእንስሳት መድኃኒት እና የህክምና መሳሪያዎችን በተመለከተ የሚኖሩትን ወቅታዊ መረጃዎች የሚለዋወጥበት ስርዓት የሌለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

217. ባለስልጣኑ አግባብ ያላቸው የክልል አካላት ስለሰጧቸው፣ ስላገዷቸውና ስለሰረዟቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች እና የሙያ ፈቃዶች መድኃኒትን በተመለከተ ለባለስልጣኑ መረጃ መተላለፉን በተሟላ መልኩ እንደማይከታተልና መኖን በተመለከተ ሙሉ በሙሉ እንደማይከታተል ታውቋል፡፡

218. እንዲሁም ባለስልጣኑ በእንስሳት ህክምና ጥቅም ላይ የሚውሉ ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ሪፖርት እንደማያደርግ ታውቋል፡፡

219. ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመሆን በክልል ተሻጋሪ የመድኃኒትና መኖ አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይ ባለፈቃዶች እና በችርቻሮ ንግድ እንዲሁም በህገ-ወጥ መድኃኒትና የመኖ ዝውውር ላይ የመግባቢያ ሰነድ (MOU) የሌለው መሆኑ፣

220. እንዲሁም በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አምራችነት፣ጅምላ አከፋፋይነት፣ላኪነትና አስመጪነት ዘርፋ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን ውጤታማ ለማድረግ እና በስራዎች ላይ የሚኖሩ የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶችን ለመፍታት የሚያስችል የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት በመመሪያ ደረጃ በማዘጋጀት እየሰራ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

221. አዋጅ ቁጥር 728/2004 ባለስልጣኑ መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፤ መከማቸቱንና መጓጓዙን ሊቆጣጠር እንደሚገባ ቢደነግግም ባለስልጣኑ የእንስሳት መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፤ መከማቸቱንና መጓጓዙን በተሟላ መልኩ እየተቆጣጠረ እንደማይገኝ ታውቋል፡፡

222. በኦዲቱ ወቅት የታዩት ሁሉም የመኖ አምራች ድርጅቶች ማለትም 9ኙም መኖን ለማምረት የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ የመኖ ግብዓቶች ከተገኙበት ቦታ ሁሉ በመግዛት መኖ የሚያመርቱ ቢሆንም የመኖ ድህንነትንና ጥራትን ለማስጠበቅ እንዲያስችል አምራቾች ጥራቱ የተጠበቀ የመኖ ግብዓት ስለመጠቀማቸው እንዲሁም የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች/ግለሰቦች/ ድህንነቱ የተጠበቀ ግብዓት ስለማቅረባቸው እና የመኖ አምራች ድርጅቶችም ደህንነቱ የተጠበቀ ግብዓት ከታወቀ ድርጅት ስለመግዛታቸው ባለስልጣኑ በዚህ ዙሪያ ክትትል ያላደረገ መሆኑ፣

223. ይህም በመሆኑ የኢትዮጵያ የምግብ መድኃኒት ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ከባለስልጣኑ ጋር በጋራ ተጠንቶ የጥናቱ ሪፖርት የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነት ከግብዓት አቅራቢዎች ጀምሮ ወጥና ውጤታማ በሆነ መልኩ ባለመስራቱ መነሻው ፈንገስ ወይም ሻጋታ የሆነ አፍላቶክሲን የተባለ መርዛማ ኬሚካል በወተት ላይ እንደተፈጠረ ማሳየቱ እንዲሁም ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር በማያያዝ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ዙሪያ ስራውን መስራት ባለመቻሉ ይህ አፍላቶክሲን የተባለው መርዛማ ኬሚካል ሊከሰት እንደቻለ፣በተጨማሪም የኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መኖ እና የወተት ናሙና ተወስዶ ሁሉም ናሙናዎች በአፍላቶክስን እንደተጠቁ ጥናቱ እንደሚያሳይ በተለይም ደግሞ የመኖ ጥሬ ዕቃዎች ላይ ችግሩ እንደከፋና ወተት ላይ የታየውም ምንጩ የሚመገቡት መኖ እንደሆነ በጥቅምት/2008ዓ.ም ለባለስልጣኑ ያሳወቀ መሆኑ፣

224. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ 12 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች፣ 6 ጅምላ አከፋፋዮች፣3 አምራች ድርጅቶች እንዲሁም 6 መኖ አምራች ድርጅቶች እና 2 የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪና ላኪ ድርጅቶች ውስጥ 10 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ፣ 2 የመድኃኒት አምራቾች እንዲሁም 6 የመኖ አምራች ድርጅቶችና 2የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች አስመጪና ላኪ ድርጅቶች ባለስልጣኑ ቁጥጥር ቢያደርግባቸውም

በየዓመቱ ለቅድመ ፈቃድ እድሳት ቁጥጥር እንደሆነና አልፎ አልፎም የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በራሳቸው ፕሮግራም ሳያሳውቁ ድርጅቶቹ ድረስ በመምጣት ክትትልና ቁጥጥር ቢያደርግም መደበኛ በሆነ መልኩ የማያደርግ እና በተቆጣጠረው መሰረት ለድርጅቶቹ ግብረ መልስ በማዘጋጀት እንዲያውቁት የማያደርግ መሆኑ ታውቋል፡፡

225. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት
# የማሻሻያ ሃሳቦች

- ተገልጋዮች የንግድ አሰራር ስርዓት አውቀው መደረግ የሚገባውን ቅድመ ዝግጅት በማሟላት የአገልግሎት ጥያቄያቸውን በአግባቡ ለመጠየቅ እንዲያስችላቸው ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ንግድ ስራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች ወይም ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊያዘጋጅና ሊሰጥ፤ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት በወቅቱ የምስክር ወረቀቱን ሊያድስ፣ሊያግድና ሊሰርዝ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ ማንኛውም ሰው የሙያ ፈቃድ የተሰጠው የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በሌለበት የእንስሳት መድኃኒት ቤት ንግድ እንዳይካሄድ ሊቆጣጠር እንዲሁም ማንኛውም የመኖ ማምረቻ ድርጅት ቢያንስ የምርት ክፍል ዋና ኃላፊ እና የጥራት ቁጥጥር ክፍል ኃላፊ እንዲሁም የመኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገሮች ወይም ግብዓቶች አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ቢያንስ የመኖ ሽያጭ ክፍል ኃላፊ ወይም መጋዘን ሰራተኛ መስፈርት የሚያሟሉ ባለሙያዎችን በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤውን ከብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡
- ባለስልጣኑ ግልፅና ተጠያቂነት በሰፈነበት አሰራር ለመስራት እንዲያስችለው ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ህክምና መሳሪያ አስመጪ ወይም ላኪ ወይም አከፋፋይ ድርጅት ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው በዘርፉ እንዳይሰማራ ለመቆጣጠር የሚስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- እንዲሁም ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 728/2004 ወይም ለአዋጁ አፈፃፀም የወጣውን ደንብ ቁጥር 272/2005 ወይም መመሪያዎች በመተላለፍ ሲሰራ የተገኘ ሰው ላይ በአዋጁ እና ደንቡ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ማንኛውም የመኖ ንጥረ ነገሮች ወይም ግብዓቶች ንግድ ድርጅት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ መኖ ወይም የመኖ ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ እንዳያስገባ ሊቆጣጠር እንዲሁም ህገ ወጥ የመድኃኒት አከፋፋይነት እንዳይስፋፋ ማንኛውም የእንሰሳት መድኃኒት ወይም መኖ አምራች ፣ አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ፈቃድ ለሌለው ሰው መድኃኒት /ወይም መኖ ካከፋፈለ በአዋጅ ቁጥር728/2004ዓ.ም አንቀፅ 26 ንሑስ አንቀፅ 2እና 3 መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

- ባለሰልጣኑ በዘርፉ ገቢውን ለማሳደግ እንዲያስችለው ለእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሳሪያዎች፤ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ ባለሙያዎች፤ ለንግድ ማስታወቂያ፤ ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተቋማት ምዝገባና ፈቃድ ለመስጠት እንዲሁም በውጭ አገር አምራች ኩባንያዎች ለእንስሳት መድኃኒት የመልካም አመራረት ተሞክሮ ምልከታ ለማድረግ በደንብ ቁጥር 325/2006 በወጣው ተመን መሰረት በወቅቱ የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈፀም ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ ለእንሰስሳት ለውጭ ጥገኛ ህክምና ወይም ለእንስሳት በሽታ አስተላላፊ ተባዮች መቆጣጠሪያ አገልግሎት የሚውሉ ንጥረ ነገሮችንና ውህዶችን መመዝገብና መቆጣጠር እና በአገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎች እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ገምግሞ ሊመዘግብ፣ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ምዝገባውን ማደስ ማገድና መሰረዝ እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ የምስክር ወረቀት በምዝገባው መስፈርቶች መሰረት በየ5ዓመቱ ሊያድስ ይገባል፡፡
- ሁሉንም የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን መዝግቦ ጥቅም ላይ እንዲውል እና የእንስሳት በሽታ ስርጭትን ለመቀነስ እንዲያስችል እንዲሁም ባለስልጣኑ በተገቢው መንገድ ለመከተተልና ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝርን ሊያዘጋጅ፣ መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በየዓይነታቸው ሊመድብ፣ መዘርዝሩንም በየጊዜው ሊከልስ ይገባል፡፡
- በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ለማግኘት እንዲያስችል ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ አግባብ ላላቸው አካላት ስልጠና ሊሰጥ እና በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ ደህንነቱ ፣ ፈዋሽነቱ እንድሁም ጥራቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት ለተጠቃሚው እንድደርሱና ጤንነታቸው የተጠበቀ የእንስሳት ውጤቶች ለማግኘት እንዲያስችል በሀገር ውስጥ የተመረተም ሆነ ከውጭ ሀገር የገባ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ደህንነቱ ፣ ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተገምግሞ ከተመዘገበ በኃላ ጥቅም ላይ እንዲውል ሊደርግ ይገባል፡፡
- እንዲሁም ባለስልጣኑ የላብራቶሪና የክሊኒካል ጥናት በማደረግ የባህላዊ መደኃኒቶችን ደህንነት፤ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንድውሉ መፍቀድ አለበት፡፡

❖ ባለስልጣኑ የተመዘገበ የእንስሳት መድኃኒት ከተስራጨ በኋላ ያስገኘውን ጠቀሜታና ያስከተለውን ጉዳት ለማወቅ  እንዲያስችለው የድህረ-ገበያ ቅኝት በማድረግ በውጤቱ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

❖ ባለስልጣኑ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ጥቅም ላይ  የሚውለው አግባብ ያለው መድኃኒት አጠቃቀምን  ለማረጋገጥ  በሚያወጣቸው የአሰራር መመሪያዎች መሰረት ሊሆን እንዲሁም ከእንስሳት ሀኪም በተጨማሪ በሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ትዕዛዝ እና ያለመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶችን ዝርዝር በመመሪያ ሊወስን ይገባል፡፡

❖ የእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ አወገገድን በተመለከተ  ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን መመሪያ ተከትሎና አከባቢን በማይበክል መንገድ በእንስሳትም ሆነ በሰዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ባለስልጣኑ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸውን የእንስሳት መድኃኒቶች፤ መኖዎች ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮችን ጥቅም ላይ እንዳይውሉ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

❖ የሀገርቱ ተጨባጭ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን ደኃንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

❖ እንዲሁም  የእንስሳት መኖና የመኖተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኃንነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል በተጨማሪም ማንኛውም ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ መኖ በባለስልጣኑ የተሰጠ የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

❖ ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ የመረጃ አያያዝ ፣ ልወውጥ እና አጠቃቀም ስርዓት ሊዘረጋ እና መረጃዎቹን በዳታ ቤዝ አጠናክሮ ሊይዝ እንዲሁም የሚፈልገው አካል በአጭር ጊዜ ስለባለስልጣኑ ተገቢውን መረጃ ለማግኘት እንዲያስችለው ባለስልጣኑ የእንስሳት መዲኃኒትና መኖ መረጃዎችን ለባለሙያዎችና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚያስተላልፍበትን ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

❖ አግባብ ያላቸው የክልል አካላት ስለሰጧቸው፤ ስላገዷቸውና ስለሰረዟቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች እና የሙያ ፈቃዶች ለባለስልጣኑ መረጃ መተላለፉን ሊከታተል  ይገባል፡፡

❖ እንዲሁም  በእንስሳት ህክምና ጥቅም ላይ የሚውሉ ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለኢትዮጵያ የምግብ ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡

❖ ባለስልጣኑ እርምጃ ለመውሰድ/መፍትሄ ለመስጠት እንዲያስችለው ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመሆን በክልል ተሻጋሪ የመድኃኒትና መኖ አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይ ባለፈቃዶች እና በችርቻሮ ንግድ እንዲሁም በህገ-ወጥ መድኃኒትና የመኖ ዝውውር ላይ የመግባቢያ ሰነድ (MOU) ሊኖረው ይገባል፡፡

❖ እንዲሁም ባለፈቃዶች በተሰማሩበት በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አምራችነት፣ጅምላ አከፋፋይነት፣ላኪነትነ አስመጪነት ዘርፍ ላይ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት ሊየዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

❖ የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነትን በማሳደግ ሊከሰቱ የሚችሉ የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከል እና የእንስሳት ጤንነትን በመጠበቅ ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲያስችል ባለስልጣኑ መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፣ መከማቸቱንና መጓጓዙን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

❖ እንዲሁም ባለስልጣኑ ክልል ተሻጋሪ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ለሚያመርቱ፣ ለሚያከፋፍሉ፣ ለሚያስተዋውቁ እንዲሁም መድኃኒትና መኖ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡና ወደ ውጭ የሚልኩ አካላትን እና የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎችን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

❖ በመጨረሻም ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 728/2004ዓ.ም የተቋቋመ ቢሆንም በአደረጃጀት ያለው የሰው ሃይል ከተፈቀደው 45 በመቶ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ የተቻለ በመሆኑ ባለስልጣኑ አደረጃጀቱን አስተካክሎ የታዩትን ጉድለቶች እንዲያስተካክል እናሳስበላን፡፡

## አባሪ1 -ባለስልጣኑ ደንብ እና መመሪያዎችን በተላለፉ ድርጅቶች/ግለሰቦች ላይ እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ የተገለፁ 6 ነጥቦች፤

- ✓ ማንኛውም አስመጭ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ከሌላ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ካለ የእንስሳት መድሃኒትና የእንስሳት ሕክምና መሳሪያ አስመጭ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት የእንስሳት መድሃኒትና የእንስሳት ሕክምና መሳሪያዎችን መሸጥም ሆነ መግዛት እንደማይችል በመመሪያ የተቀመጠ ቢሆንም 2 ድርጅቶች ማለትም አንድ (ራንግቬት)የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት እና አንድ(ፊሁላ) የእንስሳት መድኃኒት ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት በተመሳሳይ ደረጃ ላሉ 2 ድርጅቶች/ባዮቲክ የእንስሳት መድኃኒት ጅምላ አከፋፋይ፣ ለ አለማ ፋርም የመድኃኒት አስመጪ/ ሲሸጡ በኦዲቱ ወቅት የተገኘ መሆኑ፣
- ✓ አንድ የእንስሳት መድኃኒት አምራች መድኃኒቱን የሚሸጠው ለጅምላ አከፋፋይ ብቻ መሆን ሲገባው በችርቻሮ ፈቃድ ላላቸው መሸጥ እንደሚችሉ እና ባለስልጣኑ አምራቾችን እያበረታታ ባለሀብቶች እንደሚበራከቱ ለማድረግ ተግቶ እንደሚሰራ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በቃለ ጉባኤ የገለፁ መሆኑ፣
- ✓ ባለስልጣኑ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 01/2006 ዓ.ም አንድ የእንስሳት መድሃኒት አስመጪ ከውጭ የእንስሳት መድኃኒት ማስመጣት የሚችለው መጀመሪያ ከባለስልጣን መ/ቤቱ የግዥ ትዕዛዝ ካገኘ በኃላ ነው ቢልም 4የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ከባለስልጣኑ የግዥ ትዕዛዝ ሳይጠይቁ መድኃነት አዳማ/ሞጆ ደረቅ ወደብ ከገባ በኃላ እንዲለቀቅላቸው የግዥ ትዕዛዝ የጠየቁ መሆኑን ባለስልጣኑ ከሰነድ ግምገማ ቢረዳም ይህ አካሄድ መመሪያውን የጣሰና ቅደም ተከተሉን ያልጠበቀ መሆኑን፣ በተጨማሪም አንድ የመኖ ማምረቻ ኃ/የተ/የግ/ማ በአዲስ አበባ ከተማ በሲ.ኤም.ሲ ማከፋፈያ ቅርንጫፍ በ22/07/2008 በተካሄደው ኢንስፔክሽን ምልከታ የመኖ ማከፋፈያው ኮንቴነሩ ውስጥ በቂ የአየር ዝውውር እንደሌለና የኮንቴነሩም ሙቀት ከፍተኛ መሆኑ እየታወቀ ከአሁን በኃላ ህግና ደንቡን ተላልፈው ከተገኙ ባለስልጣን መ/ቤቱ ቀጣይ እርምጃ እንደሚወስድ የቃል ማስጠንቀቂያ በፅሑፍ እንዲደርሳቸው ከማድረግ ውጪ እርምጃ እንዳልወሰደባቸው እንዲሁም አንድ የመድኃኒት አስመጪ ድርጅት ከመድኃኒት ጋር የሚላከው ሊፍሌት ሳይኖረው መድኃኒት እንዳስገባ የታወቀ መሆኑ፣
- ✓ አንድ ከባለስልጣኑ ፈቃድ የሌለው አስመጪና ላኪ ድርጅት (አል ኢምፔክስ)የግዥ ፈቃድ ከባለስልጣኑ ሳይፈቀድለት ከውጭ ሀገር አንድ ኮንቴነር የእንስሳት መኖና ኬሚካል በማስመጣት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ ቢሆንም ባለስልጣኑም ካለምንም እርምጃ የእንስሳቱ መኖ በላብራቶሪ ተረጋግጦ እንዲለቀቅላቸው ማድረጉ፣
- ✓ እንዲሁም ሁለት የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች(ዳት ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አግቴክ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ) ለእንስሳት ህክምና አገልግሎት የሚውል መሳሪያ እና መዥገር መርጫ መሳሪያ የህክምና ስሪንጅና መርፌ ወደ ሀገር ውስጥ ሲያስገባ በመሳሪያው ላይ ያለው ሌብል እና አስተሻሸግ ለእንስሳት አገልግሎት ብቻ የሚል ፁሁፍ የለሌውና በመሳሪያው ላይ የአትክልትና ፍራፍሬ ምስል በማሳየቱ በባለስልጣኑ ተይዞ የነበረ

ቢሆንም  ባለስልጣኑ በቀጣይ ለሚያስመጣው ምርት እንደሚያስተካክለው ውል በማስገባት ብቻ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 728 አንቀፅ 24ን በመጥቀስ በማስጠንቀቂያ ያለፈ መሆኑ፤

- ✓ በተጨማሪም አንድ በዶሮ እርባታ ዙሪያ የሚሰራ ድርጅት(ዳዊት ያዕቆብ ደንበል)  ለዶሮ እርባታ የሚውል የዶሮ ክትባት መስጫ(የህክምና መሳሪያ) እቃውን ወደ ሀገር ውስጥ አስገብተው በኤርፖርት ጉምሩክ እንደሚገኝ እና ለወደፊት ይህንን አይነት ችግር እንደማይፈጥሩ ቃል በመግባት ለባለስለጣኑ ደብዳቤ በመፃፍ ባለስልጣኑ ከመመሪያ ውጭ ፈቃድ ሳይኖራቸው እና የግዥ ትዕዛዝ ሳይጠይቁ የፈቀደላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

## አባሪ 2፡ሠንጠረዥ1- የእንሰሳት መድኃኒት ወይም መኖ አምራች፣አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች መድኃኒት ወይም መኖ አከፋፍለው በባለስልጣኑ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ድርጅቶች ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | የእንሰሳት መድኃኒት ወይም መኖ አምራች፣አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች | ፈቃድ የሌለው ግለሰቦች/ድርጅቶች ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | ዛፍ ፋርማሲውስሲትካል ኃ/የተ/የግ/ድ | ለ15 ግለሰቦች እና ድርጅቶች፣ |
| 2 | ኤኤች.ኤም ኢንተርፕራይዝ | ለ6ግለሰቦች እና ድርጅቶች፣ |
| 3 | ባዮቴክ እን/መ/የህ/መ/አስመጪ ድርጅት | ለ11 ግለሰቦች፣NGO እና ድርጅቶች፣ |
| 4 | ጂሲትእን/መ/የህ/መ/አስመጪ ድርጅት | ለ30 ግለሰቦች እና ድርጅቶች፣ |
| 5 | ኢኳቶሪያልቢዝነስ ግሩብ እን/መ/የህ/መ/አስመጪ ድርጅት | ለ27ግለሰቦች |
| 6 | ፣የኢትዮጵያ የግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን (ለ6) | ለ8 ግለሰቦችና ለ3 ክልሎችና ለ1 አምራች |
| 7 | ራንግቬት ኃ/የተ/የግ/ማ | ለ12 ግለሰቦች፤ ድርጅቶች፤ ለመንግስት ተቋማትና ለመድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች |
| 8 | አለማ ፋርም የእንስሳት መድኃኒት/ክትባቶችን | ለ አስር ግለሰቦች እና ድርጅቶች፣ |
| 9 | ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት | ለ ግለሰቦች እንደሚሸጡ በቃለ-መጠይቅ ወቅት ተረጋገጠ |
| 10 | አዳሚ ቱሉ ፀረ ተባይ ማዘጋጃ አክሲዮን ማህበር | ለ5 ግለሰቦች እና ድርጅቶች፣ |
| 11 | ኢስት አፍሪካ ፋርማሲውቲካል ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ለ1 ግለሰብ |
| 12 | ቃሊቲ የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ድርጅት | ለ6 ግለሰቦች እና ድርጅቶች፣ |
| 13 | አለማ ካውዳይስ ኃ/የተ/የግ/ማ የእንስሳት መኖ አምራች ድርጅት | ለ6 ግለሰቦች እና ድርጅቶች፣ |

## አባሪ 3፡-አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው በእንስሳት መድኃኒት ወይም በመኖ ንግድ ስራ ላይ ሲሰማሩ የተገኙ ድርጅቶችን የያዘ 17 ነጥቦች

- ወደ 17 የሚሆኑ ተቋማት በክልል 14 በኩል በገጠር መድኃኒት ቤት በችርቻሮ ፈቃድ አውጥተው እያለ በተግባር ግን በኢንስፔክሽን ወቅት ሲጠና ክልል ተሻጋሪ የጅምላ ንግድ እያከናወኑ መሆናቸውን ባለስልጣን መ/ቤቱ ቢደረስበትም ለ10 ድርጅቶች ሰርኩላር በመበተን ምንም እርምጃ ሳይወሰድ እና መስፈርት ሳያሟሉ ለነዚሁ ተቋማት ወደ ጅምላ አከፋፋይነት የሚያድጉበትን ሁኔታ ማመቻቸቱ ታውቋል፡፡ ሆኖም 7ቱም ተቋማት የጅምላ አከፋፋይነት ፈቃድ ያላወጡ መሆኑ፣
- ባምቢሰ ኃ/የተ/የግ/ማ የእንስሳት መኖ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው ለ7 ዓመታት ሲሰራ የቆየ እና ከውጭ ሀገር የድመትና ውሻ መኖ ማስገባቱ እየታወቀ በይቅርታ ደብዳቤ ብቻ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ኮሜት ኬላ የተያዘበትን መኖ እንዲለቀቅለት በባለስልጣኑ ባለሙያዎች የተወሰነ መሆኑ፣
- እንዲሁም በኢንስፔክሽን ሪፖርት የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት የጅምላ አከፋፋይነት ፈቃድ ሳይኖራቸው በቀጥታ ለችርቻሮ ድርጅቶች እየሸጡ እንደሚገኙና በጅምላ አከፋፋይነት ስራ ለተሰማሩ ድርጅቶች እንቅፋት እንደፈጠሩባቸው መጠቆሙና በተደጋጋሚ በዚህ ተግባር ላይ የተሰማሩት ድርጅቶችም ትሮፒካል ፋርማ፣ ኤ.ኤች.ኤም እና ጂ.ሲ.ቲ መሆናቸው መታወቁ፣
- ዋፍ የሚባል የገጠር እንስሳት የመዲኃኒት ቤት ድርጅት ከባለስልጣኑ የጅምላ አከፋፋይነት የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው ከአዲስ አበባ መስተዳድር በክልል ደረጃ በጅምላ አከፋፋይነት ተሰማርቶ መገኘቱና ጉዳዩ በህግ ቢያዝም መፍትሄ ሳያገኝ ባለስልጣኑ ካለምንም እርምጃ ወዲያውኑ የጅምላ አከፋፋይነት ፈቃድ እንዲያገኝ ማድረጉ፣
- በሀዋሳ ከተማ የሚገኝ ሻላ የተባለ የገጠር የእንስሳት መድኃኒት ቤት የመንግስት መስሪያ ቤት በሲዳማ ዞን ዳራ ወረዳ ለሚፈፅሙት የግዥ ጨረታ ላይ ለመጫረት የያዙት የጨረታ ሰነድ በእጃቸው እንደተገኘ መረጋገጡ በተጨማሪም ለአንድ ግለሰብ ካለ መድኃኒት ማዘዣ እስከ ብር 7950 መድኃኒት የሸጡበት ደረሰኝ መገኘቱ እንዲሁም በዛው ከተማ ታንክስ ሎርድ የእንስሳት መድሃኒት ቤት የመንግስት መስሪያቤቶች በሚፈፅሙት ግዥ ለመሳተፍ በአቅራቢዎች ዝርዝር መመዝገባቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት መገኘቱ፣ ከኢንስፔክስን ሪፖርት የተገኘ መሆኑ፣
- መቀሌ አካባቢ ጅምላ አከፋፋዮች በመመሪያው መሰረት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ማውጣትና ማሳደስ ሲገባቸው በክልላቸው እየተስተናገዱ መሆናቸው በማኔጅመንት ቃለ ጉባዔ የተገለፀ ቢሆንም ዝርዝራቸው በባለስልጣኑ ያልተገኘ መሆኑ፣
- ከአዲሰ አበባ ውጭ የሚገኙ የተወሰኑ የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ተቋማት የእንስሳት መድኃኒት በጅምላ እስከ 100 ሽህ ብር መሸጥ መቻላቸው መረጋገጡ በማኔጅመንት ቃለ ጉባዔ የተገለፀ ቢሆንም ዝርዝራቸው በባለስልጣኑ ያልተገኘ መሆኑ፣
- ባዮቴክ ኃ/የተ/ የግ/ማ የመድኃኒት አስመጪ ድርጅት እና አግሪን ኃ/የተ/ የግ/ማ የመድኃኒት ጅምላ አከፋፋይ ድረጅት የስራ ኃላፊዎች በባለስልጣኑ ፈቃድ ሳይኖራቸው በህገወጥ መልኩ

የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ዙሪያ የተሰማሩና በህገ-ወጥ መንገድ መድኃኒት በማስገባት በሶማሌና በአፋር አካባቢ የሚንቀሳቀሱ እንዳሉ የገለጹ ሲሆን ይህ ህገ ወጥ እንቅስቃሴም በመድኃኒት ዋጋ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያለው መሆኑን ነገር ግን ጉዳዩን በተናጠል በመለየት ለባለስልጣኑ ያሳወቁበት ጊዜ ባይኖርም በህዝብ ክንፍ ውይይት ላይ ለባለስልጣኑና ለባለድርሻ አካላት እንዳሳወቁ ሆኖም ግን እንደ ሀገር ግን ከፍተኛ ጉዳት እንዳለው የስራ ሃላፊዎቹ የገለፁ መሆኑ፣

- ፍሬንድሽፕ አግሮ ኢንደስትሪ ፣ አስኳል፣ ኢትዮ ፊድ ፣ቦራ እና አዲስ አለም የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪ/ያማምረቻ/ ድርጅቶች ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያወጡ እየሰሩ ቢሆንም ባለስልጣኑ ምንም ዓይነት እርምጃ ያልወሰደባቸው መሆኑ፣ ባለስልጣኑም ወደ ስርዓቱ እንዲገቡ የማድረግ ስራ አለመስራቱን የድርጅቶቹ የስራ ኃላፊዎች የገለፁ ሲሆን በተጨማሪም ድርጅቶቹ ያመረቱትን መኖ ጥራቱና ደህንነቱ ባልጠረጋገጠበት ሁኔታ ለተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ሽያጭ እያከናወኑ መሆኑና ባለስልጣን መ/ቤቱም እየተቆጣጠረ አለመሆኑን እንዲሁም ቃሊቲ ፣አቃቂ ፣ኢትዮ ፊድ እና አዲስ አለም/ሞጆ የእንስሳት መኖ ማምረቻ/ማቀነባበሪያ/ ኃ/የተ/የግ/ድርጅቶች ከባለስልጣኑ በዘርፉ ፈቃድ ሳይኖራቸው የመኖ ጥሬ እቃዎችን/ግብአቶች/ በህገ ወጥ መልኩ ያለፕት በመግዛት የሚያመርቱ እንዳሉና ጥራቱን ያልተጠበቀ/ያልተረጋገጠ/ መኖ ህጋዊ የብቃት ማረጋገጫ ይዘው የሚሰሩ ድርጅቶች ጋር ጨረታ ላይ በመሳተፍ እንደሚያቀርቡና በድርጅታቸው አካባቢ በተናጠል ሱቆች የመኖ ግብዓቶችን መኖ በማለት የሚሸጡ ግለሰቦች/ድርጅቶች/ እንዳሉ በተጨማሪም የድርጅታቸውም ገቢ እንዲቀንስ ዋነኛ ምክንያት እንደሆነና በድርጅታቸው ላይ ከፍተኛ የመኖ ዋጋ መዛባት እንደገጠማቸውና እንዲሁም የድርጅታቸው ተወዳዳሪነት ላይ ጉዳት እያደረሱ መሆኑን፤ ቃሊቲ የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ድርጅት ለባለስልጣኑም ስለሁኔታው በቃል እንዳሳወቁና የተወሰደ መፍትሄ የሌለ መሆኑ፤
- በኮንትሮባንድ መልክ የሚሸጡ መድኃኒቶች እንዳሉ በዚህም ምክንያት ኢስት አፍሪካ የመድኃኒት አምራች ድርጅት የሚሸጠው መድኃኒት ውድ ነው በማለት ማግኘት ያለበትን ገበያ እያጣ መሆኑን እንዲሁም አልቤንዳዞል የተባለውን የእንስሳት መድኃኒት አስመስሎ በማምረት ወይም በማስመጣት የሚያሰራጩ ድርጅቶች መኖራቸውና በስራቸውም ላይ እንቅፋት እየፈጠረባቸው መሆኑን የኢስት አፍሪካ የመድኃኒት አምራች ድርጅት እና የኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት የስራ ኃላፊዎች የገለጹ ሲሆን ፣ከዚህም ሌላ ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይወስዱ ምንጩ ከማይታወቅ አቅጣጫ በህገ ወጥ የመድኃኒት ዝውውር ሙያዊ ፈቃድ በሌላቸው ግለሰቦች በየቤቱ እየተዞረ የሚሰጥ መሆኑን እንዲሁም በኤርፖርት በኩል በመንገደኞች አውሮፕላን በህገወጥ መንገድ የሚገቡ ክትባቶች እንዳሉ በህዝብ ክንፍ በተደረገው ቃለ ጉባኤ የታወቀ መሆኑ፣
- በተጨማሪም ብሄራዊ እንስሳት ጤና ኢንስቲቲዩት/NVI/ ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው የእንስሳት መድኃኒት ማምረት፣ከውጭ ሀገር የማስመጣት/የማስገባት/ና ወደ ውጭ ሀገር ክትባትና ህክምና መሳሪያዎችን የመላክ ስራ እንዲሰሩ በተለያየ ጊዜ የግዥ ትዕዛዝ እና ወደ ውጭ እንዲያስወጡ ከባለስልጣኑ የተፈቀደላቸው መሆኑና በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ስራ ላይ ሲሰማሩ የነበሩ ቢሆንም ባለስልጣኑ በድርጅቶቹ ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ አለመውሰዱ፣

- የአዳሜቱሉ የእንስሳት ፀረ-ተባይ ማምረቻ ድርጅት በባለስልጣኑ በአምራችነት ያልተመዘገበ መሆኑና ፋብሪካውም ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ለማውጣት የሚያስችለውን መስፈርት የማያሟላ መሆኑ በባለስልጣኑ የክትትል ሪፖርት የታወቀ ቢሆንም በዘርፉ ተሰማርቶ የሚገኝ ሲሆን ባለስልጣኑ በድርጅቶቹ ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ አለመውሰዱ፣ ፣
- የዳሽን ቢራ ፋብሪካ ሰራተኛ የሆኑ አንድ ግለሰብ ያለፈቃድ ከውጭ ሀገር ወደ 21 ዓይነት የውሻ መኖ ወደ ሀገር ውስጥ ሊያስገቡ ሲሉ ኬላ ላይ የተያዘ ቢሆንም የመኖው ሁኔታ በጥናት ቡድን ታይቶ ከፊሉ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት እና ሁሉም መኖ ዘረመሉ ከተለወጠ ግብዓት ነፃ ስለመሆኑ፣ የምርት ጥራት ሰርተፍኬት ስለመኖሩ፣ የመኖ ጤናማነትና ደህንነት የሚገልፅ የጤና ምስክር ወረቀት ሳኖረውና ግለሰቡዋ ለምን ጥቅም እንደምታውለው እርግጠኛ ባለተሆነበት ሁኔታ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበትን 5ቱን ብቻ እንዲወገዱ በማድረግ በመመሪያው ለግል ጥቅም መጠኑ ምን ያህል መሆን እንዳለበት በግልፅ ባልተቀመጠበት ሁኔታ የተያዘው መኖ እንዲለቀቅ መደረጉ፤
- ከንግድ ሚኒስቴር በቅባት እህል ጥራጥሬ ሽፋን የእንስሳት መኖ ማለትም የጎመን ዘር ፋጉሎ ነው በማለት ነጋዴዎች በህገ ወጥ መንገድ የተቀላቀለ ፋጉሎ ሌቴር ኦፍ ክሬዲት ከፍተው ውል በመግባት በመጋዝኖቻቸው የተከማቸውን ፋጉሎ ወደ ውጭ ሀገር እንዲወጣ ከበላይ አካላት ባለስልጣኑ በተጠየቀው መሰረት ባለስልጣኑ ኪሳራ እንዳይከሰት ለወደፊት የብቃት ማረጋገጫ እስኪያወጡ ድረስ ከነጋዴዎቹ መጋዘን የተቀላቀለ ፋጉሎ እንድወጣ ማድረጉ፣ እንዲሁም ወደ ውጭ ሀገር ያለፈቃድ ሲወጣ የነበረ ፋጉሎ በኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል የተያዘ ቢሆንም ባለስልጣን መ/ቤቱ ያለምንም እርምጃ የተያዘው መኖ እንዲለቀቅ በሚል ለጉምረክ ባለስልጣን ደብዳቤ በመፃፍ እንድለቀቅ መደረጉ፤
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በህገ-ወጥ የመኖ ዝውውር ላይ በ2008 በጀት ዓመት ቁጥጥር ለማድረግና ድንገተኛ አሰሳ ለማካሄድ የታቀደ ቢሆንም በእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ያለተገለፀ መሆኑ፤
- በ2008 በጀት ዓመት በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አጠቃላይ ንግድ ዝውውር ላይ የዳሰሳ ጥናት ለማድረግ ታቅዶ በእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ አለመገለፁ፣
- ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው በእንስሳት መኖ ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው እንዳሉና ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ፈቃድ በማውጣት ከባለስልጣኑ እውቅና ውጭ የጎመን ዘር ፋጉሎ ወደ ውጭ ሀገር ለማስወጣት ይንቀሳቀሱ የነበሩ 55 የቡራዩ ከተማ እና 50 የአዳማ ከተማ የምግብ ዘይት መጭመቂያ ባለቤቶች የጎመን ዘር ፋጉሎ ከሀገር ውጭ ለማስወጣት ለባለስልጣኑና ለግብርና ሚኒስቴር አቤቱታ ያቀረቡ መሆናቸውና በተጨማሪም ከኤፌማካ በዘይት አምራችነት ፈቃድ ያወጡ ድርጅቶች የዘይት ተረፈ ምርት ከባለስልጣኑ እውቅናና ፈቃድ ውጭ እየሸጡ መሆናቸው ቢታወቅም የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች የዘይት አምራች ድርጅቶችን ማን መቆጣጠር እንዳለበት እንደማይታወቅ የገለፁ መሆኑ ታውቋል፡፡

## አባሪ4፡-ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ ሴርትፍኬት በምዝገባው መስፈርቶች መሰረት በተሟላ መልኩ በየ 5 ዓመቱ አለማደሱን እና ሴርተፍኬታቸው ከ 5 ወር እስከ 6 ዓመት ሳይታደስ ቆይቶ መድኃኒቱን ከውጭ ሀገር አስገብተው በመሸጥ ላይ ያሉትን የሚያመለክት 13 ነጥቦች

- ✓ ዛፍ ፋርማስሲቲካል የተባለ የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት AMPROLIUM Hcl 20% oral powder ,Box of 10 sachets of 100gm የሆነ እና TRICLABENDAZOLE 900mg Bolus የሴርተፍኬት ቁጥራቸው 198/01 እና 095/02 የሆነ የመድሃኒቶቹን ምዝገባ ያከናወኑት በ07/04/2009 እና በ30/11/2009 ሲሆን የመድሃኒቱ ምዝገባ እድሳት ያለፈው 07/04/2014 እና በ30/11/2014 ቢሆንም የመድሃኒቶቹ እድሳት ጊዜ ካለፈ በኃላ ድርጅቱ እድሳት ሳያከናውን እስከ ነሀሴ/2015 ድረስ መድኃኒቶቹን በመሸጥ ላይ እንደነበረ ስለመሆኑ ከዛፍ ፋርማስትውቲካል ኃ/የተ/የግ/ኩ ከተገኘው ከመድኃኒት ሽያጭ ደረሰኞች (cash sale attachement) የታወቀ መሆኑ፣
- ✓ AHM የእንስሳት አስመጪ ድርጅት ANCOTRYP powder for injection 2.36gm/sachet የመድኃኒት ፈቃድ የተሰጠው 01/04/2011 ሲሆን በተጨማሪም ALBENTONG 2500MG BOLUS,5BOIL8 strips per box የመድኃኒት ፈቃድ የተሰጠው በ17/03/2011 ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት የፈቃድ ዕድሳት ጊዜው ከ5-6 ወር በማለፍ የዘገየ መሆኑ ፣
- ✓ አጎናፍርና ልጆቹ የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት DIAZINOL 60% የተባለ የእንስሳት መድኃኒት በቀድሞው መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በኩል በ2001 ዓ.ም ምዝገባ ያከናወነ ሲሆን ድርጅቱ ቢያመለክትም ባለስልጣኑ እስካሁን ድረስ ዳግም ምዝገባ ሳያደርግለት መድኃኒቱ እየተሰራጨ መሆኑ፤
- ✓ ለባዮቴክ ኃ.የተ.የግ.ማ,OXYTETRACYCLINE 10% certificate no.086/04 እና ,OXYTETRACYCLINE 20% certificate no.085/04 ፈቃድ ያገኙት14/10/2011 ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ሌላ ሴርተፍኬት በ14/10/2012 ያላቸው መሆኑ ማለትም በአንድ መዝገብ ቁጥር ሁለት ጊዜ የተለያየ ዓመት ሴርተፍኬት የተሰጠው ሲሆን ሰርተፍኬቱ ሳይታደስ ለ2 ዓመት ያለፈ ቢሆንም ድርጅቱ መድኃኒቱን በማስመጣት እየሸጠ መሆኑ እንዲሁም የመድኃኒት ምዝገባ ምስክር ወረቀቱን በባለስልጣኑ መስፈርት መሰረት ለማሳደስ የትኛውን ፈቃድ ያገኘበትን ጊዜ መወሰድ እንዳለበት ግልፅ ያልሆነ መሆኑ፤
- ✓ ራንግቬት ኃ/የግ/ማህበር የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ የሚያስመጣቸውን የእንስሳት መድኃኒቶች በባለስልጣኑ ማስመዝገቡና ምዝገባቸውንም በጊዜው መሰረት እያሳደሱ መሆናቸውን የስራ ኃላፊዎቹ ቢገልፁም OXYTETRACYCLINE 10% 100ML GLASS VIAL, INJUCTION የተባለ የእንስሳት መድኃኒት በተመሳሳይ የመድኃኒት ምዝገባ ቁጥር እና Certificate NO በ2011ና 2012 ዓ.ም በባለስልጣኑ በማስመዝገብ እያስመጣ መሆኑ እና የመድኃኒት ምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ የትኛውን ጊዜ መውሰድ እንዳለበት ግልፅ ያልሆነ መሆኑ፤
- ✓ አግቴክ ትሬድንግ ኃ/የግ/ማህበር የሚያስመጣቸውን የእንስሳት ህክምና መሳሪያ በባለስልጣኑ ምዝገባ -- አከናውነናል ቢሉም በልዩ ሁኔታ ለአንድ ጊዜ ግዥ ብቻ ተብሎ ለመንግስት መ/ቤቶች

የሚያስመጡዋቸውን ሪኤጀንቶች በባለስልጣኑ እንደማያስመዘግቡና መመሪያውም እንደሚፈቅድ የስራ ኃላፊዎች የገለፁ ሲሆን በተጨማሪም የላብራቶሪ እቃዎችን እንደ እንስሳት ህክምና መሳሪያ ቢታይም አንኳ በባለስልጣኑ ፈቃድና ምዝገባ ሳይሆን በሳይንስና ቶክኖሎጂ ተቋም በኩል እንደሚያስገቡ የታወቀ መሆኑ፣

- ✓ በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ፈቃድ ተሰጥቶት የነበረ አንድ የመድኃኒት አስመጪ ድርጅት ፈቃዱ ሳይታደስ 5 ዓመት ያለፈ ሆኖ ሳለ ድርጅቱ ከባለስልጣኑ እውቅና ውጭ የአስመጪነት ፈቃድ በእድሳት ላይ ነው በሚል ሰበብ መድኃኒት ወደ ሀገር ውስጥ አስገብቶ በኬላ ላይ ቢያዝበትም ካለምንም እርምጃ ባለስልጣኑ እንዲለቀቅለት የተፈቀደለት መሆኑ የባለስልጣን መ/ቤቱ የመስክ ምልከታ ቡድን የሞጆ ቅርጫፍ ጽ/ቤትን በተመለከተ ባቀረበው ሪፖርት የተገኘ መሆኑ፣
- ✓ በቃሊቲና ሞጆ ደረቅ ወደብና በቦሌ አየር መንገድ በነበረው የኢንስፔክሽን ምልከታ የመድኃኒቶች ምዝገባ ሰርተፍኬታቸው ሳይታደስ ድርጅቶች እየሰሩ መሆኑና ከነዚህም ውስጥ ራንግቨት ኃ/የተ/የግ/ማ በ2ዓይነት መድኃኒቶች(DIMINAZEN 445MG+555MG,GRANULE FOR INGECTION,SACHET OF 2.36MG and CYCLOSPRAY15.21GM/ML CAN OF 211ML SPRAY) በ1998ዓ.ም እና በ1999 ዓ.ም መድኃኒቶቹን ያስመዘገበ ቢሆንም እስካሁን ድረስ እድሳት ያልፈፀመ መሆኑና ከ5 እስከ 6ዓመት የመድኃኒት እድሳት ሳያደርግ መድኃኒት እያስመጣ መሆኑ፣
- ✓ የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን ከባለስልጣኑ የአስመጪነት ፈቃድ ቢኖረውም በባለስልጣኑ ካለው መስፈርትና አሰራር ውጪ የእንስሳት መድኃኒቶችን ከውጭ ሀገር ለማስመጣት በባለስልጣኑ በኩል ምዝገባ ሳያከናውን ሌሎች አሰመጪ ድርጅቶች ባስመዘገቡት የመድኃኒት ምስክር ወረቀት ዓለም አቀፍ የግዥ ጨረታ በማውጣት ሀገር ውስጥ የሚያስመጡ ሲሆን ነገር ግን ሀገር ውስጥ መድኃኒቱን ላስመዘገበው ድርጅት ኮሚሽን የሚያስብለት መሆኑ፡
- ✓ ከዚህም በተጨማሪ በሀገሪቱ ካሉት 3 የመድኃኒት አምራች፤የእንስሳት ክትባቶችና የፀረ ተባይ ማዘጋጃ አክስዮን ማህበር ድርጅቶች ውስጥ ኢስት አፍሪካን ፋርማሲውቲካል ኃ.የተ.ድርጅት ሲሆን ለ9 ዓይነት መድኃኒቶች ለ5ዓመት ከቀድሞ የምግብ፣ጤና ክብካቤና መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ፈቃድ ያገኘ ሲሆን 6ቱ የፈቃድ ጊዜው ያበቃው በነሐሴ/2006 ዓ.ም ሲሆን 3ቱ ደግሞ በየካቲት/2007ዓ.ም ቢሆንም የመድኃኒት ምዝገባ ሴርተፍኬት ለማደስ ድርጅቱ በወቅቱ ቢያመለክትም ባለስልጣኑ ከ1ዓመት ከ8 ወር እስከ 2ዓመት ከ8 ወር ድረስ ሴርተፍኬት ሳይታደስላቸው ምርት በማምረትና ንግድ ሲፈፅም እንደቆየ ከድርጅቱ በተገኘው ማስረጃ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፤ እንዲሁም ከባለስልጣኑ የምዝገባ ሴርተፍኬት ሳይሰጠው ፈቃድ ለማውጣት በሂደት ላይ እያለ ድርጅቱ ሁለት ዓይነት መድኃኒት ማለትም(Tetracycline Hcl 500 12’ and Tetracycline Hcl 500 10’) በማምረት ላይ መሆኑን ከድርጅቱ በተገኘው ማስረጃ መሆኑና ይሄም በመሆኑ የመድኃኒት ምዝገባ ላይ ላብራቶሪ የለንም በማለት ጊዜ እየተጓተተባቸው መሆኑን የድርጅቱ የስራ ኃላፊዎች የገለጹ መሆኑ፣
- ✓ ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት ለሚያመርታቸው 21 ዓይነት የእንስሳት ክትባቶች በባለስልጣኑ በኩል እስካሁን ምዝገባ አለማከናወኑን እና ከነዚህም ውስጥ ለባለስልጣኑ 5 ዓይነት

መድኃኒቶችን ለማስመዝገብ ጥያቄ ቢያቀርብም እስካሁን ባለው ምዝገባው ተጠናቆ ሰርተፍኬቱን አለማግኘታቸውንና በስራቸው ላይ እንቅፋት እንደፈጠረባቸው የስራ ኃላፊዎቹ ቢገልፁም በድርጅቱ የሚመረቱ ክትባቶች በባለስልጣኑ ያልተመዘገቡና ድርጅቱም የማምረት ፈቃድ ያልያዘ መሆኑን እና መንግስታዊ ተቋም ስለሆነ ብቻ በመግባባት እየሰሩ መሆኑን የካቲት 2007ዓ.ም የተካሄደው የኢንስፔክሽን ሪፖርት የሚያሳይ መሆኑ፣

- ✓ በህዝብ ክንፍ በተደረገው ቃለ ጉባኤ ላይ ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት (NVI ) የመድኃኒት(የክትባት) አምራች ቢሆንም እንደአስመጪም በመስራት ላይ ያለ ሲሆን ይህም ድርጅት ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ እንዳልወሰደ እና በመንግስት አቅጣጫ በሀገሪቱ አጣዳፊ የበሽታ ክስተት እንዳይፈጠር ለመከላከለል የሚያስችል እንዲሁም ለምርምር ጉዳይ የሚውሉትንና በአጠቃላይ አስመጪዎች በብዛት የማያስገቧቸውን መድኃኒቶች እንደሚያስመጣ በአጠቃላይ ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት (NVI )የገበያውን ክፍተት ለመሙላት እየሰራ መሆኑን የባለስልጣን ዳይሬክተር የገለፁ መሆኑ ፣
- ✓ አዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ማዘጋጃ አክስዩን ማህበር በኢትዮጵያ ምግብ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ተመዝግቦ ቬታዚኖን(VETAZINON 60%) አምርቶ ለገበያ እያቀረበ የሚገኝ ሲሆን የሚዝገባ ጊዜው ያበቃው ሰኔ/2005 ዓ.ም ሲሆን ምዝገባው እንዲታደስላቸው የጠየቁት በመስከረም/2006ዓ.ም እና በድጋሚ ጥር/2006 ዓ.ም ላይ ቢሆንም የመድኃኒቱ ሰርተፍኬት ሳይታደስ መድኃኒቱን ሲሸጡ እንደነበሩ ከድርጅቱ በተገኘው ማስረጃ ታውቋል፡፡ ሆኖም ግን ባለስልጣኑ በሽያጭ ላይ ችግር ከገጠማችሁ እንፅፍላችኃለን በማለቱ ሴርተፍኬቱ ሳይታደስ እስከ 2008 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በዛው እንደቀጥሉ የስራ ኃላፊዎቹ የገለጹ መሆኑ፣

## አባሪ5- <u>በባለስልጣኑ ሳያስመዘግቡ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎች እንዲሁም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች ይዘው የተገኙ ድርጅቶችና ስለጉዳዩ የያዙ 12 ነጥቦች</u>

- ✓ ባለስልጣኑ በ2007 ዓ.ም 8 አዲስ የእንስሳት ክትባት ሰነድ ለመገምገም እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒት፣ የህክምና መገልገያ ለማስተዋወቅ የሚቀርብ 4 ማመልከቻዎችን ለመገምገም አቅዶ ስለመከናወኑ የዕቅድ አፈፃፀም ላይ ያልተገለፀ መሆኑ ፣
- ✓ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎችን በተመለከተ ኢስት አፍሪካ ፋርማስውሲትካል የእንስሳት መድኃኒት ድርጅት በባላስልጣኑ ነፃ የስልክ ጥሪ በ8083 ለባለስልጣን መስሪያቤቱ በተሰጠው ጥቆማ መሰረት ያመረተው ቴሊን የተባለ መድኃኒት በባለስልጣኑ ሳይመዘገብ ሲያከፋፍል የተገኘ ቢሆንም ጉዳዩን ወደ ህግ ቀርቦ በይቅርታ ከመታለፍ ውጭ ምንም ዓይነት እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፣
- ✓ በደብረ ብርሃን አካባቢ የሚገኙ 2 የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ድርጅቶች ማለትም በጥላዬ እና በቅዱስ ጊዮርጊስ የእንስሳት መደብሮች ውስጥ በባለስልጣኑ ያልተመዘገበ Calcium borogluconate (CALCIJECT) Norbrook merete Bach no. 41123-70

D.O.M03/2014 exp. Mar.2017 የሆነ ባለ 400 ሚ.ሊ መድኃኒት መገኘቱና ሁለቱም ድርጅቶች መድኃኒቱን የገዙት ጎጃም በረንዳ ከሚገኘው አዲስ ኢንተርናሽናል ከተባለው የእንስሳት መድኃኒት መደብር እንደሆነና የገዙበትም ደረሰኝ በእጃቸው አለመኖሩን መግለፃቸው በባለስልጣኑ የኢንስፔክሽን ቡድን የተረጋገጠ መሆኑ፣

- ✓ በኢስት አፍሪካ የእንስሳት መድኃኒት ችርቻሮ ድርጅት ውስጥ በተደረገው ድንገተኛ ኢንስፔክሽን KEPROMEC ORAL (Ivermectin) ባለ 1000ml Batch no. 1346714 man.date 11-213 exp.Date 11-2015 የሆነ በባለስልጣን መስሪያቤቱ ያልተመዘገበ መድኃኒት የተገኘ መሆኑና የድርጅቱ ባለቤትም መድኃኒቱን የገዙት ከጎጃም በረንዳ የምዕራብ ድርጅት ችርቻሮ ድርጅት ከሆነው ለሙከራ ብለው እንደሸጡላቸውና ደረሰኝ እንደሌላቸው የገለፁ መሆኑ፣
- ✓ Calciovet የተባለ በባለስልጣኑ ተመዝግቦ የማይታወቅ ምርት በትሮፒካል የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ በገበያ ላይ ተሰራጭቶ መገኘቱና የተባለውም ምርት በአስመጪ ድርጅቱ መጋዘን ውስጥ አገልግሎቱ ሊያልፍ 4 ወር የቀረው ሆኖ የተገኘ መሆኑ በባለስልጣኑ በኢንስፔክሽን ቡድን የተረጋገጠ መሆኑ፣
- ✓ ዕጌ የእንስሳት መድኃኒት ጅምላ አከፋፋይ የተባለ ድርጅት ውስጥ Calcium borogluconate+ sodium Hypophosphate(CALCIOVETS) batch no.G002 Man. Date 22/10/2012 የመጠቀሚያ ጊዜው እስከ 22/10/2015 የሆነ በትሮፒካል ፋርማ ትሬዲንግ የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት በኩል የገባ መድኃኒት ሁለት ብልቃጥ መድኃኒት የገዛች መሆኑ የታወቀ ቢሆንም መድኃኒቱ በባለስልጣኑ ስለመመዝገቡ ያልተጣራ መሆኑ ፤
- ✓ በብሄራዊ እንስሳት ጤና ኢንስትቲዩት/NVI/ የእንስሳት ክትባት ማምረቻ ድርጅት የሚያመርታቸው ምርቶች በባለስልጣኑ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
- ✓ እንዲሁም አዳማ ቱሉ የጸረ ተባይ ማዘጋጃ አክሲዮን ማህበር የእንስሳት የውጭ ጥገኛ መድኃኒቶችን ማለትም Ethiomiraze 12.5 Ec lit panch የተባለ መድኃኒት በባለስልጣኑ ሴርተፍኬት ከማግኘቱ በፊት እያመረተ ይሸጥ የነበረ መሆኑ፣
- ✓ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በተመለከተ በአዳማ አካባቢ ሀይከል የተባለ ድርጅት ካልሼም ፎስፌት የተሰኘ በባለስልጣኑ ያልተመዘገበ የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ሲያመርት መገኘቱና እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣ እንዲሁም ዳዊት ያዕቆብ የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት ለመድኃኒት አስመጪነት ባወጣው ፈቃድ ብቻ በመጠቀም በባለስልጣኑ ባለሞያዎች ቁጥጥር በተደረገበት ወቅት በመጋዘኑ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር የተከማቸበት ሁኔታ መኖሩን ያወቁ ሲሆን ለዚህም ባለስልጣኑ የወሰደው እርምጃ አለመኖሩ የክምችቱንም ብዛት ለግልፅ አለመቻሉ፤
- ✓ በኤል.ኤምፒክስ አስመጪና ላኪ ድርጅት ወደሀገር ውስጥ ከገባው የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነግር ውስጥ ባለስልጣኑ ወደሀገር ውስጥ ተለይተው ሊገቡ የሚችሉ የመኖ ተጨማሪ ንጥረነገሮችን ባለመለየቱ የተነሳ ባለ 1ሊትርና ባለ 500ሚ.ሊ ሊትር ማፅጃ(ድተሪጀንት) በመኖ ዝርዝር ውስጥ ተካቶ ወደሀገር ውስጥ መግባቱ፣

- ✓ ኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የግ/ማህበር የተባለ ድርጅት በባለስልጣኑ ተገምግሞ ሳያስመዘግብ እና ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳይሰጠው ወደ 17 ዓይነት የሚሆኑ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ከውጭ ሀገር ከባለስልጣኑ የግዢ መጠየቂያ በመጠየቅ የሚያስገባ ቢሆንም ካለ ምንም እርምጃ ፈቃድ የተሰጠው መሆኑ ታውቋል፡፡ይህም የሆነው ባለስልጣኑ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች ምዝገባ ባለመጀመሩ መሆኑን እና በዚህም ዙሪያ የኤልፎራ የስራ ኃላፊዎች ድርጅቱ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሩን ከውጭ ሀገር ማስመጣት ከጀመረ ከ30 ዓመት በላይ እንደሚሆነው ከባለስልጣኑም ፈቃድ ያገኙት በ2008ዓ.ም ሲሆን የግዥ ትዕዛዝ በመጠየቅ ብቻ ያስገቡ የነበረ መሆኑ የገለፁዋል ፣
- ✓ ኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ የእንስሳት መኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር አስመጪ ድርጅት 10 ዓይነት የመኖ ተጨማረ ንጥረ-ነገሮችን እያስመጣ ቢሆንም ባለስልጣኑ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮችን ገምግሞ መመዝገብ ባለመጀመሩ ምክንያት ምዝገባ እንዳላከናወኑና ባለስልጣኑን በግዥ ማዘዣ በመጠየቅ ከውጭ ሀገር እያስመጡ መሆኑን የድርጅቱ የስራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅና ባቀረቡት ማስረጃ መታወቁ፣

## አባሪ6፡ያለላብራቶሪ ፍተሻ ድርጅቶቹ በጠየቁት መሰረት በባለስልጣኑ ለመድኃኒቶቹ ጊዜያዊ እንስሳት መድኃኒት ሰርትፍኬት በመስጠት መድኃኒቶቹ ወደ ሀገር እንዲገቡና እንዲሰራጩ የተፈቀደላቸው ድርጅቶች ዝርዝር፡

| የድርጅቶቹ ዝርዝር | ለዳግም ምዝገባ ጊዜያዊ ሰርትፍኬት የተሰጠበት የእንስሳት መድኃኒት ዓይነት | በአዲስ መልክ ጊዜያዊ ሰርትፍኬት የተሰጠበት የእንስሳት መድኃኒት ዓይነት |
|---|---|---|
| ባዮቴክ እን/መ/የህ/መ/አስመጪ ድርጅት | በ2 | በ3 |
| ኤ.ኤች.ኤም ኢንተርፕራይዝ | በ3 | በ1 |
| ደጃዝማች ጎናፍርና ልጆቹ እን/መ/የህ/መ/አስመጪ ድርጅት | በ2 | - |
| ጂ.ሲ.ቲ እን/መ/የህ/መ/አስመጪ ድርጅት | በ2 | በ4 |
| ማርቆስ እን/መ/የህ/መ/አስመጪ ድርጅት | በ1 | በ8 |
| ራንግቬትኃ/የተ/የግ/ማ | በ2 | በ4 |
| ኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ እን/መ/የህ/መ/አስመጪ ድርጅት | - | በ2 |

## አባሪ7፡ <u>የአገልግሎት ዘመን ያለፈባቸውን የእንስሳት መድኃኒቶች፣ መኖዎች ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮች በመመሪያ መሰረት በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ ባለስልጣኑ ስለመቆጣጠሩ በተመለከተ 14 ነጥቦች</u>

- ✓ GCT የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት Deltamethrine 1%- pali መጠኑ 2154 ሊትር የሆነ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት የእንስሳት መድኃኒት ለባለሰልጣን መ/ቤቱ ያሳወቁ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ባለስልጣኑ ምላሽ አለመስጠቱን ለኦዲት ቡደኑ ባቀረቡት ማስረጃ ደብዳቤ ቁ.GCT/7089/08 ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች ሶስት ዓይነት መድኃኒቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው አልፎባቸው በድርጅቱ መጋዘን ውስጥ እንዳሉ የገለጹ መሆኑ፣
- ✓ ባዮቴክ ኃ/የተ/ የግ/ማ የመድኃኒት አስመጪ፣ እና አግሪን የእንስሳት መድኃኒት ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች በመለየት ያስቀመጡ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ባለስልጣኑ የመድኃኒት አወጋገድ መመሪያ ባለማውጣቱ የተነሳ ያልተወገደ መሆኑ፣
- ✓ በዛፍ ፋርማስሲትውቲካል ኃ/የተ/የግ /ኩባንያ AMPROLIUM Hcl 100mg ብዛቱ 5595 sachet ከረጥት የሆነው የእንስሳት መድሃኒት የመገልገያ ጊዜው አብቅቶ በድርጅቱ የሚገኝ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ ለባለስልጣኑ ያላሳወቀ ሲሆን ባለስልጣኑም ለማስወገድ ጥረት አለማድረጉ ፣
- ✓ ራንግቬት ኃ/የተ/የግ/ማ የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅት ራንግፌቤንዳ የተባለ ለጋማ ከብቶች የሚውል መድኃኒት መጠኑ 1762 ሳጥን የሆነ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ለባለስልጣኑ እንዲወገድለት ያሳወቀ ቢሆንም ባለስልጣን መ/ቤቱ ያለምንም ያወጋገድ መመሪያ ድርጅቱ አዳማ ማዘጋጃ ቤት አዘጋጀልኝ ባለው ቦታ ብቻ እንዲወገድ መደረጉ የታወቀ መሆኑ፣
- ✓ የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን 46 ዓይነት የእንስሳት መድኃኒቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ለብልሽት የተዳረጉ በመሆናቸው ምክንያት ለባለስልጣኑ በ2007 ዓ.ም በመመሪያው መሰረት እንዲወገድላቸው በደብዳቤ ቢያመለክቱም አስካሁን ድረስ ባለስልጣኑ የአወጋገድ መመሪየያ ባለማውጣቱ ምክንያት ምላሽ እንዳልሰጣቸውና መድኃኒቶችም አለመወገዳቸው፣
- ✓ አዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ማዘጋጃ አክስዮን ማህበር በአመራረት ችግር ምክንያት ጥቅም ላይ የማይውል የእንስሳት መድኃኒት እንዳላቸው በቃለ መጠይቅ ወቅት የስራ ኃላፊዎቹ የገለፁ መሆኑ፣
- ✓ ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን የእንስሳት ክትባቶች በራሳቸው የአወጋገድ መመሪያና የማሰወገጃ ቅፅ በየጊዜው እያሰወገዱ እንዳሉና ለባለስልጣኑም እንደማያሳውቁ ባቀረቡት ማስረጃና በቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ገልፀዋል፡፡

- ✓ ዳሽን ቢራ ፋብሪካ አክስዮን ማህበር የማርኬቲንግ ስራ አስኪያጅ የሆኑት ግለሰብ ከውጭ ሀገር ያስገቡት የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበት 5 ዓይነት የእንስሳት መኖ(የውሻ መኖ) በባለስልጣኑ አካባቢን እንደሚበክልና እንደማይበክል ሳያጠና ከጉምሩክ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ከጋዝና ከአፈር ጋር በመቀላቀል እንዲወገድ መደረጉ፣

በኦዲቱ ወቅት ከታዩት 7 የመኖ አምራች እና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪድርጅቶች ውስጥ 3ቱ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው የመኖ ንጥረ-ነገር እና መኖ ያላቸው ሲሆኑ እንዲሁም 4 ድርጅቶች ያስወገዱበት ሁኔታ ቢኖርም በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን ባለስልጣኑያልተቆጣጠረ መሆኑ ከነዚህም ውስጥ

- ✓ አለማ ፋርም በ2008 ዓ.ም የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት ቪታብሮን የተባለ የእንስሳት ክትባት ያጋጠማቸው ሲሆን የመጠቀሚየ ጊዜው ካለፈበት ገና ቅርብ ጊዜው ነው በማለት እስካሁን ድረስ ለባለስልጣኑ አለማሳወቃቸውንና አለመወገዱ፣
- ✓ ኢኳቶሪያል ቢዝነስ የእንስሳት ተጨማሪ መኖ ንጥረ-ነገር አስመጪ ድርጅት ብዛቱ 4373 ከረጢት እና 2000 ብልቃጥ (ቦትል) የሆነ ስድስት(6) ዓይነት የእንስሳት ተጨማሪ መኖ ንጥረ-ነገር የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ቢሆንም ባለስልጣኑ እንዲወገድ አለማድረጉ እና ለባለስልጣኑ ባለሙያዎችም በቃል የገለፁ መሆኑ፣
- ✓ ቃሊቲ የእንስሳት መኖ ማምረቻ ድርጅት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው የመኖ ቫይታሚን ከአስር ዓመት በላይ በድርጅቱ ውስጥ የሚገኝ መሆኑንና ለባለስልጣኑም በቃል እንዳሰሳወቁና እስካሁን ድረስ ምላሽ አለማግኘታቸው፣
- ✓ ኢትዮ ፊድ የእንስሳት መኖ ማደራጃ ኃ/የተ/የግ/ድርጅት የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት አጋጥሞአቸው ያስወገዱበት ሁኔታ እንዳለና የተበላሹትን ግብዓቶች ዲኮምፖስ በማድረግ ላይ እንደሆኑ ፣
- ✓ ቦራ የእንስሳት መኖ ማደራጃ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት አጋጥሞአቸው ያስወገዱበት ሁኔታ እንዳለና የተበላሹትን መኖዎች እንዲሁም ግብዓቶችን በራሳቸው ያስወገዱበት ሁኔታ መኖሩ፣
- ✓ በኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት የመኖ ተጨማሪ ንጠረ ነገሮች ቢኖሩም ይመለከተዋል ባሉት አካል /ለግብርና ሚ/ር/እንዳሳወቁ ሆኖም ግን ባለስልጣኑ ስለአወጋገዱ ሁኔታ ምንም ነገር እንዳላስገነዘባቸው በቃለ መጠይቅ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡

## አባሪ8፡ ከባለስልጣኑ የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይሰጣቸው የበርካታ ዓይነት መኖ ቅልቅል ፋጉሎ ወደ ውጭ ሀገር ስለመላኩ የሚያሳይ ዝርዝር ጉዳይ በ4 ነጥቦች

- ○ ባለስልጣን መ/ቤቱ ካስቀመጠው አሰራር ውጭ በገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን በኩል የኑመንዘር ፋጉሎ ከሀገር ውጭ እንዲሸጡ ፈቃድ የተሰጣቸው ድርጅቶች መኖራቸውና ባለስልጣን መ/ቤቱም በቅንጅት አለመስራቱ መታወቁ፤

- የእንስሳት መኖ ወደ ውጭ ሀገር መውጣት የለበትም ተብሎ በደብዳቤ ቁጥር እ/መ/አ/ቁ/ባ/527/06 ከታገደ በኋላ በባለስልጣኑ መኖው ጥራቱን ስለመጠበቁ የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይሰጥ ኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የግ/ማህበር የተባለ ድርጅት አልፋ አልፋ የተባለ የመኖ ምርት በማምረት ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የምርት ናሙና በመፈተሽ የፍይቶ ሳኒቶሪ ማለትም /መኖው በዓለም አቀፍ መስፈርት ደረጃ ከበሽታ ነፃ መሆኑ የሚታይበት/ ምስክር ወረቀት ስለማቅረቡ ሳይታወቅ 44.83 ቶን የሚሆን አልፍ አልፋ መኖን ወደ ጅቡቲ የተላከ ሲሆን፤ እንዲሁም በተለያየ ጊዜ ወደ ጅዳና ወደ ጅቢቲ የተላከ መሆኑ ከባለስልጣኑ ከመኖ ጥራትና ደረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በተሰጠው መግለጫ እና ከባለስልጣኑ በደብዳቤ ቁጥር 03/እ/መ/መ/አ/ቁ/ባ/43/480 በቀን 09/04/2007 እና 01/አ/እ/00/00/አ/ቁ/ባ/48/534 በቀን 21/04/2007 ዓ.ም ለግብርና ሚ/ር ለዕፅዋትና ጤናና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት የምርት ናሙናው በመፈተሽ የፋይቶ ሳኒተሪ ምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ እንዲገለፅልን እንዲሁም ምርቱ ወደ ውጭ ሀገር እንዲወጣ በዚያው እንዲስተናገዱ በማለት በፃፈው ደብዳቤ እና ኤልፎራ ለባለስለጣኑ በፃፈው ደብዳቤ ቁጥር ELFORA-MSL 2014-6039 በቀን 7/4/2007ዓ.ም ታውቋል፡፡
- በተጨማሪም የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚ/ር የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የጥራት ማረጋገጫ ሴሪትፍኬት መስጠት የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊነት እንዳልሆነ ሆኖም ግን የፍይቶ ሳኒቶሪ ሴሪትፍኬት ለኤልፎራ ሶስት ጊዜ እንደሰጡት የገለፁ መሆኑ፣
- እንዲሁም በጥቅምት 19/2000ዓ.ም ግብርና ሚኒስቴር ማንኛውም መኖ በንግድ ወደ ውጭ ሀገር እንዳይላክ ሰርኩላር ማስተላለፉ እየታወቀ በ21/02/2006ዓ.ም በቃሊቲ መግቢያና መውጫ ኬላ ላይ ለንግድ ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ የጎመን ዘር ፋጉሎ ፈቃድ ያወጡ ላከኪዎች በመገኘታቸው ባለስልጣኑ በህገ ወጥነት ተይዞ የነበረውን የእንስሳት መኖ ናሙና በመሰብሰብ የምርመራ ውጤት ሲደረግ የመኖ ዓይነት መለያ ምርመራ ተደርጎ የበርካታ ዓይነት መኖ ቅልቅል ፋጉሎ(የጎመን ዘር፣የኑግ፣የተልባ፣ ለውዝ፣እና የጥጥ ፍሬ ወዘተ) መሆኑ በባለስልጣኑ ባለሙያዎች በመረጋገጡ ከ27/3200/6 ዓ.ም ጀምሮ የጎመን ዘር ፋገሎ ወደ ውጭ ለሚልኩ የንግድ ድርጅቶች ኤልሲ እንዳይከፈት ለንግድ ሚ/ር ቢያሳውቅም ከዚህም የተነሳ ላኪዎች ቅሬታ በማቅረባቸው ምክንያት እግዱ የተወሰነው ከኤልሲ መከፈት በኃላ እንደሆነና ወደ ውጭ ሀገር ኤክስፖርት እንደማይደረግ የሚያደርግ ደብዳቤ ጊዜ ገደብ ተሰጥቶ የእገዳው ምክንያት ተጠቅሶ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሳቸው ባለመደረጉ በአሰራር ላይ ክፍተት ፈጥሯል በማለት ስለሆነም ኤልሲ ለከፈቱላቸው ሽያጭ ቢፈፀም ለሀገርና በስራው ለተሰማሩ ባለሀብቶች እንዲምታ ግምት ውስጥ በማስገባት ኤክስፖርት እንዲያደርጉ ከጠቅላይ ሚ/ር ፅ/ቤት በመፈቀዱ እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በደብዳቤ በመድረሱ ኤሊሲ የከፈቱት እንዲያወጡ ቢደረግም በድጋሚ በ23/05/06 ላልተወሰነ ጊዜ የውጪ ንግድ እንዲቆም ቢደረግም በሀገር ውስጥ ብዙ የጎመን ዘር ፋጉሎ ክምችት በሀገር ውስጥ አለ በመባሉ ባለሀብቶቹ በየመጋዝኖቻቸው ያከማቹትን ፋጎሎ ለማውጣት በጠየቁት መሰረት ባለሙያ በየመጋዝኖቻቸው ሄደው የጎመንዘር ፋጉሎ መኖሩን በማረጋገጣቸው በቀጣይም ሀገር ውስጥ እየተመረተ ያለው የጎመን ዘር ፋጉሎ በሀገር ውስጥ በስፋት መጠቀም እንዲቻል ግንዛቤ ማስጨበጥና የማብቃት ስራዎች በእንስሳት ልማት ዘርፍ በኩል እንዲከናወኑ ጊዜ የመስጠት

አስፈላጊነት በበላይ አመራር ጭምር ስለታመነበት እና በባለስልጣኑ መግባባት ላይ በመድረሱ እስከ ሰኔ30/2006 ዓ.ም የተፈቀደው ይህ ጎመን ዘር ንግድ በከፊል የውጭ ንግድ እንዲካሄድ በ14/12/2007 ዓ.ም ባለስልጣኑ ለንግድ ባንክ ያሳወቀ መሆኑ፣

አባሪ 9

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| ተራ ቁጥር | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria's) |
|---|---|
| 1. | ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒት ወይም መኖ ንግድ ስራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች ወይም ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊያዘጋጅና ሊሰጥ፣ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት በወቅቱ የምስክር ወረቀቱን ሊያድስ፣ሊያግድና ሊሰርዝ ይገባል፡፡ |
| 2. | ባለስልጣኑ ማንኛውም  የእንስሳት መድኃኒት ወይም የእንስሳት ህክምና መሳሪያእና መኖ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር  አስመጪ ፣ ላኪ፣  አከፋፋይ ወይም አምራች  ድርጅት ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው  በዘርፉ እንዳይሰማራ ለመቆጣጠር የሚስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግይገባል፡፡ |
| 3. | ባለስልጣኑ  በአገር ውስጥ የሚመረቱም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚመጡ የእንስሳት መድኃኒቶችንና የእንስሳት ህክምና መሳሪያዎች እና  የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ገምግሞ ሊመዘግብ፣በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ምዝገባውን ሊያድስ፣ ሊያግድና ሊሰርዝ ይገባል፡፡ |
| 4. | ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒት የምዝገባ የምስክር ወረቀት በምዝገባው መስፈርቶች መሰረት በየ5ዓመቱ ሊያዲስ ይገባል፡፡ |
| 5. | ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ጥቅም ላይ  የሚውለው አግባብ ያለው መድኃኒት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ ባለስልጣኑ በሚያወጣቸው የአሰራር መመሪያዎች መሰረት መሆን አለበት፡፡ |
| 6. | ባለስልጣኑ ከእንስሳት ሀኪም በተጨማሪ በሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ትዕዛዝ እና ያለመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶችን ዝርዝር በመመሪያ ሊወስን ይገባል፡፡ |
| 7. | ማንኛውም ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ መኖ በባለስልጣኑ የተሰጠ የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡ |
| 8. | ባለስልጣኑ ማንኛውም ሰው የሙያ ፈቃድ የተሰጠው የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በሌለበት የእንስሳት መድኃኒት ቤት ንግድ እንዳይካሄድ ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| 9. | ማንኛውም የመኖ ማምረቻ ድርጅት ቢያንስ የምርት ክፍል ዋና ኃላፊ  እና የጥራት ቁጥጥር  ክፍል ኃላፊነት እንዲሁም የመኖ ወይም መኖ ንጥረ ነገሮች ወይም ግብዓቶች አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ቢያንስ የመኖ ሽያጭ ክፍል ኃላፊ ወይም መጋዘን ሰራተኛ   መስፈርት የሚያሟሉ መኖ ባለሙያዎችን በመቅጠር  የቅጥር ደብዳቤውን ከብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻ |

| | |
|---|---|
| | ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡ |
| 10. | ባለስልጣኑ አግባብ ያላቸው የክልል አካላት ስለሰጧቸው፤ ስላገዷቸውና ስለሰረዟቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች እና የሙያ ፈቃዶች ለባለስልጣኑ መረጃ መተላለፉን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| 11. | ባለስልጣኑ ማንኛውም የመኖ ንጥረ ነገሮች ወይም ግብዓቶች ንግድ ድርጅት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ መኖ ወይም የመኖ ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| 12. | ባለስልጣኑ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸውን የእንስሳት መድኃኒቶች፣ መኖዎች ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮች አወጋገድን በተመለከተ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን መመሪያ ተከትሎና አከባቢን በማይበክል መንገድ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ መደረጋቸውን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| 13. | ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ የመረጃ አያያዝ፣ልውውጥ እና አጠቃቀም ስርዓት ሊዘረጋ እና መረጃዎቹን በዳታ ቤዝ አጠናክሮ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| 14. | ባለስልጣኑ ግልፅ የሆነ የአሰራር ስርዓት እና የስራ ሂደት ፍሰትን የሚያሳይ ፁሁፍ እና በስዕላዊ መግለጫ የተዘጋጀ ማስረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| 15. | ባለስልጣኑ በሀገር ውስጥ የተመረተም ሆነ ከውጭ ሀገር የገባ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት በወቅቱ ደህንነቱ፣ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተገምግሞ ወይም ተረጋግጦ ከተመዘገበ በኃላ ጥቅም ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 16. | ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው በእንስሳት መድኃኒት ወይም በመኖ ንግድ ስራ ላይ ስሰማራ ከተገኘ ባለስልጣኑ የንግድ ተቋሙን በማሸግ ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| 17. | ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ አግባብ ላላቸው አካላት ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| 18. | ባለስልጣኑ የላብራቶሪና የክሊኒካል ጥናት በማደረግ የባህላዊ መደኃኒቶችን ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንድውሉ ሊፈቅድ ይገባል፡፡ |
| 19. | ባለስልጣኑ የተመዘገበ የእንስሳት መድኃኒት ከተስራጨ በኋላ ያስገኘውን ጠቀሜታና ያስከተለውን ጉዳት ለማወቅ የድህረ-ገበያ ቅኝት በማድረግ በውጤቱ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| 20. | ባለስልጣኑ ወቅታዊ የሆኑ የእንስሳት መዲኃኒትና መኖ መረጃዎችን በመደበኛነት ለባለሙያዎችና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚያስተላልፍበትን ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| 21. | ማንኛውም የእንሰሳት መድኃኒት ወይም መኖ አምራች፣አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ፈቃድ ለሌለው ሰው መድኃኒት ወይም መኖ ካከፋፈለ ባለስልጣኑ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| 22. | ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| 23. | ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመሆን በክልል ተሻጋሪ የመድኃኒትና መኖ አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይ ባለፈቃዶች እና በችርቻሮ ንግድ እንዲሁም በህገ-ወጥ መድኃኒትና የመኖ ዝውውር ላይ የመግባቢያ ሰነድ (MOU) ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| 24. | ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 728/2004 ወይም ለአዋጁ አፈፃፀም የወጣውን ደንብ ቁጥር 272/2005 ወይም መመሪያዎች በመተላለፍ ሲሰራ የተገኘ ሰውን የምስክር ወረቀቱን ወይም የሙያ ፈቃዱን ማገድ ወይም መሰረዝ አለበት፡፡ |
| 25. | ባለስልጣኑ ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝርን ሊያዘጋጅ፣ መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በየዓይነታቸው ሊመድብ፣መዘርዝሩንም በየጊዜው ሊከልስ ይገባል ፡፡ |
| 26. | ባለስልጣኑ ክልል ተሻጋሪ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ለሚያመርቱ፣ለሚያከፋፍሉ፣ለሚያስተዋውቁ፣መድኃኒትና መኖ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገቡና ወደ ውጭ የሚልኩ አካላትን እና የጥራት ቁጥጥር ላብራቶሪዎችን ሊቆጣጠር  እና በተቆጣጠረውም ላይ ግብረ መልስ በማዘጋጀት እንዲያውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 27. | ባለስልጣኑ በእንስሳት ህክምና ጥቅም ላይ የሚውሉ ናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች  ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 28. | ባለስልጣኑ ለእንሰስሳት ለውጭ ጥገኛ ህክምና ወይም ለእንስሳት በሽታ አስተላላፊ ተባዮች መቆጣጠሪያ አገልግሎት የሚውሉ ንጥረ ነገሮችንና ውህዶችን ሊመዘግብ እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| 29. | ባለስልጣኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| 30. | ባለስልጣኑ የእንስሳት መኖና የመኖተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን ደኅንነትና ጥራት ደረጃዎች አዘጋጅቶ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| 31. | ባለስልጣኑ መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር  ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፤ መከማቸቱንና መጓጓዙን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| 32. | ባለሰልጣኑ ለእንስሳት መድኃኒትና ህክምና መሳሪያዎች፤ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ ባለሙያዎች፤ ለንግድ ማስታወቂያ፤ ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተቋማት ምዝገባና ፈቃድ ለመስጠት እንዲሁም በውጭ አገር አምራች ኩባንያዎች ለእንስሳት መድኃኒት የመልካም አመራረት ተሞክሮ ምልከታ ለማድረግ በደንብ ቁጥር 325/2006 በወጣው ተመን መሰረት በወቅቱ የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈፀም ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 33. | ባለስልጣኑ  ባለፈቃዶች በተሰማሩበት በእንስሳት መድኃነትና መኖ አምራችነት፣ጅምላ አከፋፋይነት፣ላኪነትነ አስመጪነት ዘርፍ ላይ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |